# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስት፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት


## የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# በቡድን መማር ስልት የኢ-አፍፈት ተማሪዎችን አንብቦ መረዳትና የማንበብ ተነሳሽነት ለማጎልበትያለውን ጠቀሜታ፤በዴራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት


በቀለሟ ታደሰ



2016ዓ.ም.

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# በቡድን መማር ስልት የኢ-አፍፈት ተማሪዎችን አንብቦ መረዳትና የማንበብ ተነሳሽነት ለማጎልበትያለውን ጠቀሜታ፤በዴራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት


አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስት፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን

ኮሌጅ

የአማርኛ  ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት


የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በአማርኛ ማስተማር ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት


በ

ቀለሟ ታደሰ

የጥናቱ አማካሪ

ጌታቸው እንዳላማው (ዶ/ር)


2015ዓ.ም.

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

# የሂዩማኒቲስት፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

# የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ክፍለ ትምህርት

# የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

በቡድን መማር ስልት የኢ-አፍፈት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የማንበብ ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለውን ጠቀሜታ፤ በዴራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ተተኳሪነት በሚል የጥናት ርዕስ በቀለሟ ታደሰ የቀረበ ነው፡፡

አማካሪ..............................................ፊርማ...............ቀን.............

የውጪ ፈታኝ..................................ፊርማ...................ቀን............

የውስጥ ፈታኝ..................................ፊርማ..................ቀን...........

# ምስጋና

የመምህርነት ሙያን ስማር ለሙያው ብቃት እንዲኖረኝ በምክርና በእውቀት ገንብተው እዚህ ደረጃ እንድደርስ ትልቅ አስተዋጽኦ ላደረጉልኝና በመጨረሻም ለዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ከትልመ ጥናቱ ጀምሮ አንድም ቀን ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ በመልካም ትህትናና አክብሮት ተገቢውን የአሰራር መንገድን በመጠቆም፣ለጥናቱ አጠቃላይ አስተያየት በመለገስ ለስህተቶች እርምት በመስጠት፣ለስራው መሰልቸት እንዳይኖር በማበረታታትና ክትትል በማድረግ፣ከሁሉም በላይ ሙያዊ ድጋፋቸውን ላልነፈጉኝና ለማከብራቸው አማካሪዬ ዶ/ር ጌታቸው እንዳላማው ምስጋናዬ እጅግ የላቀ ነው፡፡

ጥናቱን ለማካሄድ ሲታሰብ ወድ ሰዓቱን ሰውቶ ተገቢውን ስልጠና በትህትና በመውሰድ በስልጠናው መሰረት አንድም ሀሳብ ሳይዛነፍ ለጥናቱ መረጃ አስተማማኝነት ጥንቃቄ በማድረግና ለጥናቱ የተመረጡ ተማሪዎችን በማስተማር፣ በፈተና ጊዜ ከፍተኛ ትብብር በማድረግ ትልቅ እገዛ ላደረገለኝ ለመምህር ሁሴን ሰይድ፣ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡

ለጥናቱ የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን በምፈልግበት ጊዜ ሰለቸኝ ሳይል የስታስቲክስ ስሌቱን አሰራር በማሳየት የበኩሉን አስተዋጽኦ ለአበረከተልኝ መምህር አዲሱ ባጅራ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

ይህ ጥናታዊ ጽሑፍ በኮምፒውተር ተጽፎ ጽሑፍ ሆኖ እንዲዘጋጅ ባላቸው እውቀት ላገዙኝ እንዲሁም ሞራላዊ ድጋፍ ላደረጉልኝ ኤፍሬም አዲሱ፣ታምሩ በዳሳ ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

በመጨረሻም በዚህ ጥናታዊ ጸሑፍ ስራ ጫና ምክንያት ከናትነት የሚጠበቀውን ድርሻ ሳልወጣ በመቅረቴ ሳትከፋና መልካም ትህትና በማሳየት በኔ ፈንታ ሆናችሁ ጎዶሎዬን ሞልታችህ ድጋፍ ላደረጋችሁልኝ ቤተሰቦቼ በሙሉ ከልብ ላመሰግናችሁ እወዳለሁ፡፡

# አህፅሮተጥናት

የጥናቱ ዋና አላማ ቡድናዊ መማር የኢ-አፍፈት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለውን ጠቀሜታ በከፊል ፍትነታዊና አይነታዊ ንድፍ መመርመር ነው። ጥናቱ በጴራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ9ኛ ክፍል ደረጃ ተካሂዷል። ትምህርት ቤቱ በአመቺ ናሙና ዘዴ የተመረጠ ሲሆን የጥናቱ ተተኳሪዎች እንደየ ቋንቋቸው ተመድበው ከሚማሩ16 ምድብ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው ኦሮምኛ ቋንቋ የሆነ በመጀመሪያው ፈረቃ የሚማሩ ተማሪዎች መካከል 9ኛሀናለ ምድብ ናቸው። ጥናቱ ከፊል ሙከራዊ ጥናት እንደመሆኑ በቀላል የእጣ ናሙና አመራረጥ 9ኛሀ የሙከራና ለ የቁጥጥር ቡድን ሆነው በጥናቱ ተካተዋል። የሁለቱም ምድብ ቁጥር እኩል ሲሆን በ9ኛ ሀናለ 42 በድምሩ 84 ተማሪዎች በጥናቱ ተካተዋል። ጥናቱ የተካሄደው ለ12 ክፍለ ጊዜያት ሲሆን የክፍል ውስጥ ልምምዱ የተከናወነው የሙከራ ቡድኑ በቡድናዊ መማር ስልት፣የቁጥጥር ቡድኑ በተለምዷዊው ተምረዋል። የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ፈተና የጽሁፍ መጠይቅ፣ቡድን ተኮርና ምልከታ ናቸው። የመረጃዎቹ አስተማማኝነት በእኩል ክፋይ ዘዴና በክሮንባኽ አልፋ ተሰልቷል። መረጃዎች ከተጣሩ በኋላ SPSS.V20 በመጠቀም በስታስቲክስና በአይነታዊ መተንተኛ መንገድ ተተንትነዋል። ቁጥጥርና ሙከራ ቡድኖቹ በቅድመ አንብቦ የመረዳት ፈተና በገላጭ ስሌትና በቲ ቴስት ተፈትሾ(ፒ>0.05) በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የአማካይ ውጤት ልዩነት አለመኖሩ ተረጋግጧል። ነገር ግን በቅድመና ድህረ ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ (ፒ<0.05) ብልጫ ማሳየቱን ማወቅ ተችሏል። ሙከራ ቡድኑበቅድመ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ የሰጡትን ምላሾች አማካዩ ተወስዶ ሲታይ በድምሩ (66.8%)ቱ አለመስማማትን ሲገልጹ በአንጻሩ (33.2%) መስማማትን ገልጸዋል:: በድህረ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ ምላሽ ግን በድምሩ (73.9%)ቱ በጣም መስማማትን በአንጻሩ (39.3%) አለመስማማትን ገልጸዋል። በቡድን ተኮር ውይይቱ ከተማሪዎች የተገኘው ምላሽ የሚያሳየው ቡድናዊ መማር አንብቦ የመረዳትና የማንበብ ችሎታቸውን ለማጎልበት ጠቃሚ መሆኑንና በምልከታ የተገኘው መረጃም የሚያሳየው ቡድናዊ መማር ውጤታማ መሆኑን ነው። በመረጃው ውጤት ማረጋገጥ የተቻለው ቡድናዊ መማር ስልት ለኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሶትን ለማጎልበት ከፍተኛ ጠቀሜታ ያለው እንደሆነ ነው። በጥናቱ ግኝት መነሻነትም አስተያየት ተሰቷል።

# ማውጫ

**ይዘት** **ገጽ**

**ምስጋና** ............ i

***አህፅሮተጥናት*** ............ ii

ማውጫ ይዘት ............ iii

የሠንጠረዥ ማውጫ ............ vi

ምዕራፍአንድ ............ 1

መግቢያ ............ 1

_1.1. የጥናቱ ዳራ ............ 1

_1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት ............ 4

_1.3.የጥናቱ ዓላማ ............ 5

_1.4.የጥናቱ ጠቀሜታ ............ 6

_1.5.የጥናቱ ወሰን ............ 6

_1.6.የጥናቱ ውስንነት ............ 7

_1.7.የቁልፍ ቃላት ጽንሰ ሀሳባዊ ብያኔዎች ............ 8

ምዕራፍ ሁለት ............ 9

የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት ............ 9

_2.1.የቡድናዊ መማር ደራ ............ 9

_2.2.የቡድናዊ መማር ምንነት ............ 10

_2.3.ቡድናዊ መማርና ትውረታዊ አቅጣጫዎች ............ 11

_2.4.የቡድናዊ መማር ስልት አይነቶች ............ 12

_2.5.የቡድናዊ መማር ጠቀሜታ ............ 13

_2.6.በቡድናዊ መማር ሂደት የመምህርና ተማሪዎች ሚና ............ 15

_2.7.በቡድን ለመማር አስፈላጊ የሆኑ ተግባራት ............ 16

2.7.1.መማሪያ ክፍልን ማደራጀት ............ 16

2.7.2.ቡድን መመስረት (የክፍል ውስጥ ቡድን አመሰራረት) ............ 16

2.7.3 ትምህርቱን ማቅረብ ............ 18

_2.8.የቡድናዊ መማር ስልት መርሆች (መመሪያ) ............ 18

_2.9.ቡድናዊ መማር ስልት አንብቦ የመረዳት ክህል ጋር ያለው ግንኙነት ............ 19

_2.10.ተማሪዎች ከቡድናዊ መማር የሚያዳብሯቸው ክሂሎቶች ........ 20
_2.11. የቡድናዊ መማር ስልት ችግሮች ........ 22
_2.12.የተነሳሽነት ታሪካዊ ዳራ ........ 22
_2.13.የተነሳሽነት ምንነት ........ 23
_2.14.የተነሳሽነት አይነቶች ........ 24
_2.15.የቀደምት ጥናቶች ቅኝት ........ 25
_2.16 የኢ-አፍፊት ተማሪዎች የማነበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ........ 27
_2.17. የጥናቱ ንድፈ ሃሳባዊ ማሕቀፍ ........ 29
ምዕራፍ ሶስት ........ 31
የጥናቱን ንድፍና የአጠናን ዘዴ ........ 31
_3.1.የጥናቱ ንድፍ ........ 31
_3.2.የናሙና አመራረጥ ........ 31
3.2.1.ጥናቱ የሚካሄድበት ወረዳ አመራረጥ ........ 31
3.2.2. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ ........ 32
3.2.3. የክፍል ደረጃ ና የተጠኚ ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ ........ 32
3.2.4.የመምህራን አመራረጥ ........ 33
_3.3.የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ........ 34
3.3.1. አንብቦ የመረዳት ፈተና ........ 34
3.3.1.1.ለጥናቱ የክፍል ውስጥ ልምምድና ፈተና ምንባቦችና ጥያቄዎች አመራረጥ ........ 34
3.3.1.2.የቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና አዘገጃጀት ........ 35
3.3.1.3.የቅድመና ድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ተገቢነትና አስተማማኝነት ........ 35
3.3.1.4.ቅድመ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ........ 36
3.3.1.5. ድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ........ 37
3.3.2. የማንበብ ተነሳሽነት የጹሁፍ መጠይቅ ........ 37
3.3.2.1. ቅድመና ድህረ የማንበብ ተነሳሽነት የጹሁፍ መጠይቁ ተገቢነትና አስተማማኝነት ........ 38
3.3.3. ቡድን ተኮር ውይይት ........ 39
3.3.4. ምልከታ ........ 39
_3.4.የመረጃ አተና ተንዘዴ ........ 40
3.4.1.አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት አተናተን ........ 40
3.4.2.የማንበብ ተነሳሶት መጠይቅ መረጃ አተናተን ........ 40

3.4.3.ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች አተናተን ........ 41
3.4.4.ከቡድን ተኮር ውይይት የተገኙት መረጃዎች አተናተን........ 41
_3.5. የጥናቱ አተገባበር ቅደምተከተላዊ ሂደት ........ 41
_3.6.ከጥናቱ የተገኙ ተሞክሮዎች ........ 44
ምዕራፍአራት ........ 45
የጥናቱ መረጃ ትንተናና ውጤት ማብራሪያ ........ 45
_4.1 የጥናቱ መረጃ ትንተና ........ 45
4.1.1.አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ትንተና ........ 45
4.1.2. ከማንበብ ተነሳሽነት የጹሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና ........ 51
4.1.3.ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና ........ 56
4.1.4.ከሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ድህረ ቡድናዊ መማር የተሰበሰቡ ቡድን ተኮር ........ 59
ውይይት መረጃዎች ትንተና ........ 59
_4.2.የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ........ 60
ምዕራፍ አምስት ........ 66
የጥናቱ ማጠቃለያና አስተያየት ........ 66
_5.1.ማጠቃለያ........ 66
_5.2.አስተያየት ........ 70
ዋቢ ጽሑፎች........ 72
አባሪዎች........ 81

## የሠንጠረዥማውጫ

**ሰንጠረዥ** **ገጽ**


ሰንጠረዥ 1 የቁጥጥርና ሙከራ ቡድኖች ቅድመ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት ንጽጽርበገላጭስታትስቲክስ..........................................47

ሰንጠረዥ 2 የቁጥጥር ቡድኑና ሙከራ ቡድኑ ቅድመ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና የአማካይ ውጤት የጉልህነት ደረጃ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት......................48

ሰንጠረዥ 3 የቁጥጥርና ሙከራ ቡድኖቹ ድህረ አንብቦ የመረዳትአማካይ ውጤት ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ..........................................................................49

ሰንጠረዥ 4 የቁጥጥርና ሙከራ ቡድኑ ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት የጉልህነት ደረጃ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት..............................................50

ሰንጠረዥ 5 የሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ፈተና የአማካይ ውጤት የጉልህነት ደረጃ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት...................................51

ሰንጠረዥ 6 የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳትአማካይ ውጤት የጉልህነት ደረጃ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስሰት...................................................................52

ሰንጠረዥ 7 ከሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመ ቡድናዊ ልምምድ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ የተገኘመረጃ..........................................................................53

ሰንጠረዥ 8 የሙከራ ቡድኑ በድህረ ቡድናዊ ልምምድ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ የተገኘመረጃ..............................................................................55

ሰንጠረዥ 9 መምህሩ ሙከራ ቡድኑን በክፍል ውስጥ ሲያስተምር የተካሄደ ምልከታ........58

ሰንጠረዥ 10 መምህሩ የቁጥጥር ቡድኑን በክፍል ውስጥ በሚያስተምርበት ጊዜ የተካሄደ ምልከታ...............................................................................59

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ማንበብ ማለት አንድ ፀሀፊ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት ለማንበብ ያለ ተነሳሶትንና አንብቦ መረዳን የሚዝ ነው፡፡ የማንበብ ተነሳሽነት አንድን ነገር ለመስራት መምረጥ፣ አቋም መኖር፣ ለመጨረስ ጥረት ማድረግ፣ ከርዕሱ፣ ከድርጊቱና ከማንበብ ውጤቶች ጋር የተዛመደ አንድ የራስ አላማ ሀሳብ መኖር፣ ፍላጎትና ተማሪዎችን የሚያነቃቃ እጅግ ከፍተኛ ግፊት መሆኑን ያስረዳሉ (Dornye & Ema ushoda 2011፣ Guthre and Wigfield 2000) ፡፡

አንድን ጹሁፍ ከማንበባችን አስቀድሞ ለማንበብ ተነሳሽነት መኖሩ ጠቀሜታ አለው፡፡ ተነሳሽነት (motivation) አንድን ነገር ለማድረግ የሚገፋፋ ውስጣዊ ፍላጎት ሲሆን ሁለተኛ ቋንቋ ለመልመድ የሚፈልግ ሰው ከፍተኛ የሆነ ተነሳሽነት መኖሩ አስተዋጽኦ እንዳለውና ፍላጎት ካላቸው አላማቸውን ማሳካት እንደሚቻልና ማንኛውንም ተግባር ውጤታማ ለመሆኑ ወይም ለመክሰሩ ሁሉ አንደ ዋናነት ሆኖ የሚጠቀስ ነው (Brown 1992) ፡፡

አንድን ጹሁፍ አንብቦ ለመረዳት ተነሳሽነት አስተዋጽኦ እንዳለው Krashen (1987፣71-3) ሲያስረዱ ማንኛውም ውጤታማ የሆነ ሰው ለዚያ ተግባር ተነሳሽነት ስላለው መሆኑ መገመት ቀላል ነው፡፡ ተነሳሽነት ተማሪው ሌላ ተጨማሪ ጥቅም ለማግኘት ሳይሆን ቋንቋውን መማር እንደ ጥቅም አድርጎ በማሰብ ሲማር ነው፡፡

ማንበብ ማለት ውስብስብ አእምሯዊ ሂደት የሚንጸፀባረቅበት፣ በፀሀፊው የቀረበውን ጽሁፍ ሀሳብ መረዳት (መተርጎም፣መፍታት፣በስሜት መድረስ )፣መቀበል (መገንዘብ፣መለየትና መነጠል)፣ ድምጽን አውጥቶ መናገር ሲሆን በጥቅሉ ማስተዋል መቻል፣ለተነበበ ሃሳብ ፍቺ መስጠት፣ አንድን ሀሳብ መውሰድና መረዳት፣አካላዊ፣አእምሯዊና ስሜታዊ ጉዳዮችን ወይም መነሳሳትን የሚያካትት መስተጋብራዊ ሂደት ነው (Nuttal 1996)፡፡

እንደ ምስጋኑ (2011፣107) ብያኔ ማንበብ የአንባቢና ፀሀፊ ግንኙነት የሆነ፣ውስብስብ፣ በማንበብ የሚማሩት ማለትም በጽሁፉ ውስጥ ያሉትን ቃላት የምንለይበት፣ከጽሁፉ መልዕክት

የምንማርበት እና ጸሀፊው ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልእክት ለመረዳት የአንባቢውን ችሎታ የሚፈልግ ነው ብለው ይገልፃሉ።

በአንብቦ መረዳትና ተነሳሽነት መካከል ግንኙነት መኖሩን Kim and Kendeou (2020 በSnow 2002 እንደተጠቀሰው) ጹሁፉን ለመረዳት አንባቢው የግድ ሊያዘጋጅ የሚገባው ችሎታ፣ መነሳሳት፣ማንበብ፣እውቀት፣የስነልሳን እውቀት ትኩረት፣ማስታወስ፣መወሰን፣የማንበብ አላማ ወዘተ የሚያጠቃልል መሆኑን ይጠቁማሉ። Grellt (1981)፣Heaton(1975) በበኩላቸው አንብቦ መረዳት መቻል ማለት ከአንድ ጽሁፍ ውስጥ ባጠቃላይ መሰረታዊ ሀሳብን በሚገባ መረዳት መቻል ወይም ቃላትን መገንዘብ፣በይዘቱ የተላለፈን ሀሳብ ማስተዋል፣ የጹሀፉን አጠቃላይ መልእክት መረዳት፤ በአንድ ምንባብ ውስጥ በሚገኝ ቃላት፣ አረፍተነገሮችና አንቀጾች መካከል የሚኖር የመዋቅርና የሃሳብ አደረጃጀትን መመርመርና በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ፀሀፊው ሊገልፀው ያሰበውን መልዕክት በትክክል መረዳት ወይም መገንዘብ እንደሆነ ያስገነዝባሉ።

ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች መገንዘብ የሚቻለው አንብቦ የመረዳት ማለት አንድን ጹሁፍ ለማንበብ መነሳሳትና አንብቦ መልዕክቱን መረዳት መቻል ሲሆን ይህንን ክሂል በየደረጃው በማለማመድ ማበልጸግ ተገቢ ነው። ማንበብ ቃላትን የማስታወስ ችሎታ፣የቃላትን አገባባዊ ፍቺ መገመት፣ የጥያቄዎችን መልስ መፈለግ፣ የምንባቡን ሀሳብ አንድ ላይ ማቀናበር፣ይዘትን መገመት፣ የጸሀፊውን አመለካከት፣ አላማ፣ የአጻጻፍ ስልት፣የማንበብ ሂደት እና የሂደቱ ውጤት የሚፈተንበት፤ በአንባቢውና ጹሑፉ መካከል ያለ ግንኙነት ሲሆን አንባቢው ጹሁፉን መመልከት ብቻ ሳይሆን የሚያነበውን ጹሑፍ መልዕክት፣ ትርጉም፣ ጠቀሜታ የሚረዳበት፣ ጹሑፉ ከሌሎች ጹሑፎች ጋር ያለውን ግንኙነት በጥልቀት የሚመረምርበትና የጹሑፉን ቀጣይ ሀሳብ የሚገምትበት ነው (Alderson 2000)።

Bialystok and Hosenfeld (1983፣1981 በIstifci 2009 እንደተጠቀሱት) አንብቦ መረዳትን ሁለተኛ ቋንቋ ተማሪ እንዲያበለጽግ ተስማሚ አንብቦ የመረዳት ዘዴዎችን ተግባራዊ ማድረግ በስፋት እንዲመራመር፣ የበለጠ እንዲረዳ፣ በንቃት እንዲሳተፍ ያደርጋል። የማንበብ ስልት በመማሪያ ክፍል ውስጥ መተግበር ተማሪዎች የሚያነቡትን እንዲረዱ፣ የበለጠ እንዲረዱ፣ በማንበብ ዘና እንዲሉ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው አስገንዝበዋል። የተማሪዎችን ተነሳሽነት ማጣት ችግር በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ወቅት ተፅዕኖ የሚያሳድሩ ዋና ዋና ምክንያቶች ለመማር

የተማሪዎች መቀስቀስ ወይም ተነሳሽነት አለመኖር፣በራስ አለመተማመን፣ጭንቀት፣ፍራቻ ወዘተ በቋንቋ መማር ላይ ጫና የሚፈጥሩ መሆናቸውን አስገንዝበዋል (ብራውን 1994)።

የተለያዩ ተመራማሪዎች በጥናታቸው የተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ክሂል ምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ለማቅ ባካሄዱት ጥናት እንዳመላከቱት ተማሪዎች ለሀገርኛ ቋንቋ ለማንበብ ተነሳሽነት የሌላቸውና አንብቦ የመረዳት ችግር ያለባቸው መሆኑን ነው መኮንን (2000)፣ በረከት (2010)።

በመሆኑም የኢ-አፍ ፊት ተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ መረዳትን ለመሻሻል የተለያዩ አንብቦ የመረዳት ስልቶችን በመጠቀም ማስተማር አስፈላጊ እንደሆነ ምሁራን አስረድተዋል። ከነዚህም ስልቶች መካከል አንዱ ቡድናዊ መማር እንደሆነ የትምህርት ፈላስፋው Dewey (1931)፣ የአእምሮአዊ ስነ-ልቦና ምሁር Piagey፣Vygotsky (1988)፣የማህበራዊ ስነልሳን ምሁር Deutsch (1949) በተለያየ አቅጣጫ ሲያስረዱ በቡድን መማር ተማሪዎች አንዱ ሌላውን በመወዳደር በልጦ መገኘት ሳይሆን ጠንካራና ደካማ ተማሪዎች አንዱ ሌላውን በመመልከት ለመማር የሚነሳሳበትን ሁኔታ መፍጠር ነው።

እንዲሁም ማህበራዊ ግንባታዊነት ትውረት አተያይ ተማሪዎች ከአቻዎቻቸው ጋር በሚያደርጉት የእርስ በርስ ግንኙነት ይማማራሉ የሚልነው። የዚህ ትውረት አቀንቃኝ የሆኑት VYgotsky (1988) ተማሪዎች የአእምሮአቸው እድገት የሚመሰረተው ከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር በሚያደርጉት አብሮነትና ችሎታቸው፣አስተሳሰባቸው፣አመለካከታቸው የሚዳብረው ከሌሎችጋር በሚያደርጉት የሀሳብ ልውውጥ ነው። እንዲሁም ማነበራዊ ትውረት አተያይ ተማሪዎች ከአከባቢ ጋር በተሳሰረ መልኩ ርስ በርሳቸው አንዱ ከሌላው በመመልከት፣በማየት፣የተሰራን መልሶ በመስራትና ወደ ራስ በማምጣት ይማራሉ። ይህ ትውረት በዋናነት የሚያተኩረው አንዱ ሌላውን በማየት ለመማር ይበረታታል የሚል ነው።

በተጨማሪም የተነሳሶት ትውረትም አእምሮአዊ አወቃቀርን ለመተግበር ሚና የሚጫወት፣ የግለሰብን ስነ ምግባርና ባህሪ ማስተካከያ መሆኑን አምነን የምንቀበለው የተነሳሽነት መረጃ ትውረት ቢሆንም በተለያየ መንበራዊና ባህላዊ ምክኒያቶች በተማሪዎች መነሳሳት ላይ ተጽእኖ ሊያደርሱባቸው የሚችሉ ጉዳዮችን የሚቀንስ ወይም ትውረቱ አከባቢያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች በግለሰብ ተነሳሽነት ላይ የሚሳድሩትን ተጽእኖ የሚያስተካከልበት ነው።

ቡድናዊ መማር ከ1930ዎቹ ጀምሮ መታየት የጀመረ፣ ኢ-ቀጥተኛ ስልቶች ከሚባሉት አንዱ የሆነና የራሱ የሆኑ መመሪያዎች እንዳሉት Davis 1993፣147-51 በቅደም ተከተል አሰረድተዋል፡፡ አንዳንድ ጥናቶች እንደሚያመላክቱት የቋንቋ ትምህርት በመማር ማስተማር ሂደት ቡድናዊ መማር ጠቀሜታ ያለው መሆኑና ነገር ግን ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን ለዚህ ስልት ትኩረት የማይሰጡ እንደሆነ ነው (ዑመር 200)፡፡ ቡድናዊ መማር ዘዴ ተማሪዎችን በትምህርት ችሎታቸው በክፍል ውስጥ ከፋፍሎ ርስ በርስ አንዱ ከሌላው እንዲማር ማድረግና መቆጣጠርን፣ አላማን ከግብ ለማድረስ በግል ከመማር ይልቅ በጋራ አንዱ ከሌላው መማርን የሚያበረታታ፣ በርካታ ትናንሽ ቡድኖችን በውስጡ የሚያከትት በጋራ የመማር ወይም የመስራት ተግባር ነው (Fisher & Ellis 1990፣ springer1999 ፣ Richards 1985፣ Cohen 1994)፡፡

ከዚህ በላይ አንዳንድ ምሁራን ምንም እንኳ ቡድናዊ መማር ጠቀሜታ ያለው እንደሆነ ያመላከቱ ቢሆንም በተለያዩ ጊዜያት የተካሄዱ ጥናቶች በውጤታቸው እንደጠቆሙት ተማሪዎች ለሀገርኛ ቋንቋ የማንበብ ተነሳሽነትም ሆነ ፍላጎት እንደሌላቸውና መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች ለቡድናዊ መማር ትኩረት እንደማይሰጡ አመላክተዋል፡፡ በዚህ ጥናት መምህራን ስለ ቡድናዊ መማር የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖራቸው በማድረግ ወይም ስልጠና ላይ ተመስርተው እንዲሁም ለቡድናዊ መማር ትኩረት ሰተው ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ትምህርት ይዘትን እንዲተገብሩም ሆነ የማንበብን ተነሳሶት ለመፍጠር ቢችሉ ያለውን ለውጥ ለማረጋገጥ ሲባል ቡድናዊ መማር የኢ-አፍ ፈት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የማንበብ ተነሳሽነትን ለማጎልበት ያለውን ጠቀሜታ መርምሯል፡፡

## 1.2.የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

አንድ ጹሁፍ ሊያስተላልፍ የፈለገውን መልዕክት በሚገባ ለመገንዘብ የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ክሂል ችሎታ መኖር አከራካሪ አይደለም፡፡ የቋንቋ ትምህርት የሚሰጥበት አላማም ከዚህ ሀሳብ የተለየ ሆኖ አይታይም፡፡ ያውም የቋንቋ ክህሎትን ለማጎልበት ነው፡፡ ከነዚህ ክሂሎቶች መካከል ማንበብ አንዱ ሲሆን ተማሪዎች በመማር ሂደትም ሆነ በተፈላጊው ቦታ አንድን ጹሁፍ ለማንበብ መነሳሳትና አንብቦ መረዳት ችሎታ መኖር ከሚጠበቅባቸው ጉዳይ ዋናው ነው፡፡

በመሆኑም ለዚህ ጥናትም በዋናነት እንደ አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶች አንደኛ በተለያዩ ጊዜያት የተካሄዱ ጥናቶች ላይ በተደረገው ግምገማ ክፍተት መኖር፣ በአጥኚዋ የማስተማር ልምድ የተስተዋሉ ችግሮችና ከዚህ ቀደም ከደረጃው መምህራን ጋር በተለያዩ የስራ ልምድ ልውውጥ ጊዜ ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ለማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችግሮች መኖራቸውን በተጨባጭ መረጃ መገኘቱ ነው፡፡ ያውም ዑመር (2000) የቡድናዊ መማር አተገባበር በሚል የጥናት ርእስ መምህራን የቡድናዊ መማርን ውጤታማነት አምነው አለመቀበልን የመረመረ ነው፡ ይህ ጥናት በቡድናዊ ተግባራት ላይ ለተማሪዎች በቂ ክትትል በማድረግና መምህራን ምሁራን ስለ ቡድናዊ መማር ጠቀሜታ የሰነዘሩትን ሀሳብ መሰረት በማድረግ የተካሄደ አለመሆኑ ክፍተት ይታይበታል፡፡ እንዲሁም Behailu (2010) 10ኛና 11ኛ ክፍል ተማሪዎች ለሀገርኛ ቋንቋ ትምህርት ያላቸው አመለካከትና ተነሳሽነት የሌላቸው እንደሆነ በጥናታቸው ውጤት አረጋግ ጠዋል፡፡ ጥናቱ መምህራን ስለ ቡድናዊ መማር ምንነት፣ ጠቀሜታ፣ቡድናዊ አቀማመጥ፣ ተማሪዎችን በማንበብ ትምህት ይዘት በቡድን በማድረግ በፉክክር እንዲነሳሱ ማድረግ የሚሉትን የበለጠ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ስልጠና በመስጠት በስልጠናው ታግዘው ተማሪዎች ለማንበብ እንዲነሳሱ አለማድረጋቸውን አለመፈተሸሹ ክፍተት አለው፡፡

በተጨማሪም መምህራን የተማሪዎችን በቡድን እያነበቡ በነጻነት የማንበብ ክሂሎትንና አንብቦ መረዳትን እያጎለበቱ ለመምጣት የሚያደርጉትን ጥረት አለማገናዘባቸው፤ሁለተኛው አጥኚዋ ባላት የረጅም ጊዜ የማስተማር ልምድ በ9ኛ ክፍል ደረጃ ያሉ አማርኛ ቋንቋ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች አንብቦ መረዳትና የንባብ ተነሳሽነት አለመኖር ችግር መኖሩን መስተዋሉ ነው፡፡ እንዲሁም የክፍል ደረጃው መምህራን አማርኛ ቋንቋ ትምህርትን በመማር ማስተማር ሂደት ኢ-አፍ ፊት ተማሪዎች ለማንበብ ተነሳሽነት የሌላቸውና አንብበው ለመረዳት የሚቸገሩ መሆናቸውን በተጨባጭ መረጃ የሰጡ መሆኑ ለዚህ ጥናት እንደ አነሳሽ ምክንያቶች ናቸው፡፡

## 1.3.የጥናቱ ዓላማ

የጥናቱ ዋና ዓላማ ቡድናዊ መማር ዘዴ የኢ-አፍፊት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሶት ለማጎልበት ያለውን ጠቀሜታ የሚል ሲሆን ይህን አጠቃላይ አላማ መነሻ ያደረገው ጥናት በስሩ የያዛቸው ዝርዝር ዓላማዎች፡-

1. ቡድናዊ መማር ስልት የኢ- አፍፊት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂል ችሎታ በማዳበር

ረገድ ያለውን ጠቀሜታ ምንድነው?

2. ቡድናዊ መማር በኢ-አፍፈት ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ላይ የሚያሳድረውን ተፅእኖ ምንድነው?

## 1.4.የጥናቱ ጠቀሜታ

ይህ ጥናት ከዚህ ቀጥሎ ለሚጠቀሱት አካላት የጎላ ጠቀሜታዎች ይኖሩታል፡፡

- ለመምህራን ለኢ-አፍፈት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ትምህርት ይዘትን በማስተማር ሂደት ይበልጥ እንዴት ተግባራዊ ሊያደርጉ እንደሚችሉ ጥቆማ ይሰጣል፤
- ተማሪዎችን በቡድን መማር ስልት ተጠቅሞ ማስነበብ ምን ያህል  አንብቦ ለመረዳት ጠቀሜታ እንዳለው ግንዛቤ ይሰጣል፤
- ለተማሪዎች በቡድናዊ መማር ስልት ማስነበብ ለማንበብ ተነሳሽነታቸው እንዲጨምርና መኃበራዊ ግንኙነታቸው እንዲጨምር ያደርጋል፡፡
- ለቋንቋ መርሃ ትምህርት አዘጋጆች ስነ ትምህርተዊ እገዛ ሊያደርግላቸው ይችላል፡፡
- ለወደፊት አንብቦ በመረዳት ክሂል ማስተማሪያ ስልቶች ዙሪያ ምርምር ለሚያካሂዱ

  አካላት መነሻ ይሆናል፡፡

## 1.5.የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት የተካሄደው በኦሮሚያ ክልል፣አርሲ ዞን ዶዶታ ወረዳ በዴራ ከተማ በዴራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ውስጥ ነው፡፡ የጥናቱ ርዕስ ቡድናዊ መማር ዘዴ የኢ-አፍፈት ተማሪዎች ለንባብ ትምህርት ይዘት ያላቸውን ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ክሂል ችሎታ ለማጎልበት ያለውን ጠቀሜታ በመመርመር ላይ ያተኮረ ነው፡፡ ጥናቱ መጠናዊና አይነታዊ የምርምር ንድፍን የሚከተል ነው፡፡ ጥናቱ መጠናዊና አይነታዊ የምርምር ንድፍ ላይ ያተኮረበት ምክንያት የጥናቱ መረጃ የሚሰበሰበው እነዚህን ዘዴዎች መሰረት በማድረግና ጥናቱ የተካሄደባቸውን ሁለት ቡድን ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች በመማሪያ ክፍላቸው በተመደቡበት እንዳሉ በመውሰድ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖችን በመለየት ነው፡፡

ጥናቱ በዋናነት ትኩረት አድርጎ የመረመረው ከቋንቋ ክሂሎች መካከል ክሂል የሆነውን የማንበብ ክሂል ነው፡፡ ይኸውም ለኢ-አፍ ፌት ተማሪዎች በመማሪያ መጽሃፋቸው የቀረበላቸውን አንብቦ የመረዳት ትምህርት ይዘት በክፍል ውስጥ ብቻ በማስነበብ አንብቦ የመረዳት ችሎታንና ለማንበብ ምን አይነት ተነሳሽነት አላቸው የሚሉ ላይ በማትኮር እንጂ ከክፍል ውጪ አንብበው እንዲመጡ በማድረግ አይደለም፡፡ ጥናቱ ሌሎች የቋንቋ ንኡሳን ክሂሎችንናየማንበብ እውቀቶችን የሚመለከት አይደለም፡፡ አጥኚዋ ሌሎች የቋንቋ ክሂሎች ራሳቸውን ችለው መመርመር ያለባቸው መሆኑንና ተማሪዎች ሌሎች እውቀቶችን ከአንድ እስከ ስምንተኛ የክፍል ደረጃ በሚማሩበት ጊዜ የቋንቋችሎታዎችን በተመለከተ ግንዛቤ ይዘው 9ኛ ክፍል ደርሰዋል የሚል አመለካከት ያላት ስለሆነ ነው፡፡

ይህ ጥናት ቡድናዊ መማር ስልትን ተጠቅሞ ኢ-አፍፌት ተማሪዎችን ማንበብና አንብቦ መረዳትን ትምህርት ይዘት ማስተማር አንብቦ መረዳት ላይ ለውጥ ማምጣትና አለማምጣቱን መመርመርና የማንበብ ተነሳሽነትን መፍጠር መቻሉን ፈትሾ በማሳየት ላይ ያተኩራል እንጂ አንብቦ መረዳትን ከሌላ አንጻር አይመለከትም፡፡

## 1.6.የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት ምንም እንኳን ቡድናዊ መማር ስልትንተግባራዊ በማድረግ የኢ-አፍፌት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማጎልበትና የማንበብ ተነሳሽነት መፍጠር መቻሉን የመረመረ ቢሆንም የራሱ የሆነ ውስንነት አለው፡፡ ይኸውም በጥናቱ የተካተቱት ኢ-አፍፌት ተማሪዎች አንብቦ በመረዳትና ማንበብ ተነሳሶት ያመጡትን ለውጥ አጠቃላይ በሆነ መልኩ ያመላከተ እንጂ አንብቦ መረዳትን ከንኡሳን ክህሎች አኳያ ለያይቶ የሚያመላክት አለመሆኑ ነው፡፡

ቀሪው የጥናቱ ውስንነት በክፍል ውስጥ ቡድናዊ መማር ሂደትን ተግባራዊ ሲደረግ በማንበብ ደከም የሚሉ ተማሪዎች ያስመዘገቡትን መሻሻል በተናጥል ለብቻ ለይቶ አለማሳየቱ ነው፡፡ እንዲሁም በዚህ ጥናት በተመረጠው ቡድናዊ መማር ስልት ኢ-አፍ ፌትተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ትምህርት ይዘትን ከተመደበላቸው ክፍለ ጊዜ ባሻገር በተጨማሪረዘም ያለ ሰዓት በመውሰድ ማለማመድ አለመቻሉና በ12 ክፍለ ጊዜያት ብቻ ተምረው በዚህ አጭር ሰዓት ያመጡትን ለውጥ ወይም መሻሻል ብቻ ማሳየት መቻሉ ነው፡፡

በተጨማሪም የዚህ ጥናት ውስንነት ጥናቱ ቡድናዊ መማር ስልት የኢ-አፍ ፈት ተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ መረዳት ችሎታ ለማዳበር ያለውን ጠቀሜታ ብቻ መመርመሩና ሌሎች ስልቶች በስፋት የሚመረምር ባለመሆኑ ውስንነት አለው፡፡ እንዲሁም ጥናቱ የኢ-አፍፈት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሶት ብቻ በቡድናዊ መማር ስልት መመርመሩ የጥናቱ ውስንነቶች ናቸው፡፡

## 1.7.የቁልፍ ቃላት ጽንሰ ሀሳባዊ ብያኔዎች

**አፍ-ፈት**፡-አንድ ሰው ለመጀመሪያ ጊዜ የተጋለጠበት ቋንቋ ማለት ነው፡፡

**ኢ-አፍ ፈት**፡-ለመጀመሪያ ጊዜ ከለመዱት ቋንቋ ቀጥሎ በሁለተኛነት የሚለመድ

ቋንቋን መናገር ነው፡፡

**ቡድናዊ መማር**፡-ቡድናዊ መማር አንድን አላማ ከግብ  ለማድረስ በግል ከመማር

ይልቅ በጋራ አንዱ ከሌላው መማር የሚያበረታታና እርስ በርስ መማማር ነው፡፡

**አንብቦ የመረዳት ችሎታ**፡-ከሚነበበው ነገርየሚፈለገውን መረጃ ማውጣት መቻል

ሲሆን በጽሁፍ ውስጥ በግል የተቀመጠውን መልእክትለማጠናከር የገቡትን ዝርዝር

ጉዳዮች መረዳት መቻል ነው፡

**ተነሳሽነት** አንድ ነገር ለማድረግ የሚገፋፋ ውስጣዊ ፍላጎት ወይም ውስጣዊ ግፊት ነው፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# የተዛማጅ ጽሁፍ ቅኝት

## 2.1.የቡድናዊ መማር ደራ

የአሜሪካዊው የስነትምህርት ፈላስፋ Dewey ፍልስፍና ለቡድናዊ መማር ስልት ብቅ ማለት በቀደምትነት ተጠቃሽ ነው፡፡  በDewey ፍልስፍናም ቡድናዊ መማር ስልት በአውሮፓዊያን አቆጣጠር ከ27-30ዎቹ አከባቢ መታየት እንደጀመረ ተመላክቷል፡፡ ሆኖም ለቡድናዊ መማር መገኘትና አሁን ባለበት ደረጃ ድረስ እየተስፋፋ መሄዱ በዋናነት መነሳት ያለበት የDewey ፍልስፍና ነው፡፡ በDewey ፍልስፍና ትምህርት ማለት የተማሪዎችን የውስጥ ተነሳሽነት መነሻ አድርጎ መጀመርና እንደ ፍላጎታቸው እየተስፋፋ የሚሄድ መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ እንዲሁም በፍልስፍናው መምህራን ትምህርትን በመማር ማስተማር  ሂደቱ ሁኔታን ማስተካከል አለባቸው የሚለው ሀሳብ በዋናነት ተጠቃሽ ነው፡፡

የቋንቋ ትምህርትን በትክክል ለመስተማር በተለይ ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የተለያዩ ስልቶችን መጠቀምና አነስተኛ ተሳትፎ ያለቸውን ተማሪዎች ማለማመድ ለውጥ እንዲያመጡ ወይም እንዲሻሻሉ የሚያደርግ ነው (Istifci 2009፣Omalley1987)፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት በቡድን መማር ወይም መስራት ውጤታማ መሆኑን ከተሰበሰበው መረጃ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህንን ሀሳብ Sharan (1990) ቡድናዊ መማር ስልትን የትምህርት ባለሞያዎች አትኩሮት ሊያደርጉበት ና ለማስተማሪያ ዘዴነትም መዋል እንዳለበት አመላክተዋል፡፡

እንደ Agnihotri፣Ngorosh(2018) እምነት ተማሪዎችን በትናንሽ ቡድን ከፋፍሎ ማስተማር ከማስተማሪያ መንገዶች አንዱ ሆኖ በመምህር ተኮር ብቻ ተማሪዎችን ማስተማር ተማሪውን እንዳይሳተፍና አዳማጭ ብቻ እንዲሆኑ ያደርጋል፡፡ ከዚህ በተለየ መንገድ ቡድናዊ መማር ስልትን መጠቀም ለትምህርት ሳቢና ማራኪ በመሆኑ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው የሚገባው ነው፡፡ ምክንያቱም ቡድናዊ መማር ትምህርታዊና ሳይንሳዊ መማርን የሚከተል ነው፡፡ እንዲሁም በትናንሽ ቡድን ተማሪዎችን ከፋፍሎ ማስተማር ተማሪ ተኮር የሆነ አቀራረብና ሁሉንም

ተማሪዎች በእኩል ደረጃ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በመወያየትና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚጠቅም ነው፡፡

ቡድናዊ መማር ተማሪዎች ርስ በርሳቸው እንዲግባቡ፣ በጥልቀት እንዲያስቡ ፣በቡድን የመስራት ችሎታን ለማጎልበት፣ ውሳኔ ለመስጠትና አንዱ ከሌላው ዕውቀት እንዲያገኝ የሚያደርግ መሆኑን Dennick& Exley (1998)፣ Johnson እና Holubec (1994) አስረድተዋል፡፡ ይህ ጥናትም መምህራን የቡድን ስራ መስጠት ብቻ ሳይሆን ተማሪዎችን በቡድን በማዋቀርና ተገቢውን ክትትል በማድረግ ስልቱ ምን ያህል በተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳትና የማንበብ ተነሳሶትን ለመፍጠር ጠቀሜታ እንዳለው የመረመረ ነው፡፡

የቡድናዊ መማርን ስልት ጠቀሜታ Oxford (1990) በበኩላቸው የቋንቋ መማር ብለሀቶች ተማሪዎች የመማር ሂደታቸውን እንዲያፋጥኑ፣ትምህርቱን ለማቅለልና በቋንቋ ትምህርቱ ሂደት በቀጥታ ተሳታፊ የሚሆኑበትን ስልት የሚያሳድጉበት ባህሪ እንደሆነ አስረድተዋል፡፡

## 2.2.የቡድናዊ መማር ምንነት

የቡድናዊ መማርን ምንነት በተመለከተ አንድ ወጥ የሆነ ብያኔ መስጠት ባይቻልም በተለያዩ ጊዜያት የተሰነዘሩ ሀሳቦች እንደሚገልጹት በቡድን መማር ማለት ቁልፍ የሆኑ ጉዳዮችን ለቡድኑ አባላት ማካፈል ሲሆን ያውም የአንድን ተግባር አላማ፣ ክንውን የሆኑተን ጉዳዮች ርስ በርስ መለዋወጥ ነው፡፡ ቡድናዊ መማር ዘዴ ተማሪዎችን በትምህርት ችሎታቸው በክፍል ውስጥ ከፋፍሎ ርስ በርስ አንዱ ከሌላው እንዲማር ማድረግና መቆጣጠርን የሚያመላክት ነው፡፡ እንዲሁም አንድን አላማ ከግብ ለማድረስ በግል ከመማር ይልቅ በጋራ አንዱ ከሌላው መማርን የሚያበረታታና ርስ በርስ መማማር ነው፡፡ ቡድን በርካታ ትናንሽ ቡድኖችን በውስጡ የሚያከትት በጋራ የመማር ወይም የመስራት ተግባር ነው፡፡ (Fisher & Ellis 1990፣ springer1999 ፣ Richards 1985፣ Cohen 1994)፡፡

በተጨማሪም በቡድን መማር ሲባል ተማሪዎች በግል ያላቸውን እውቀት ይዘው ወደ ቡድን በማምጣት ሲማማሩ ውጤታቸው ይበልጥ እንዲሻሻል ወይም ከፍ እንዲል የሚያደርግ፣ መረጃን መለዋወጥንና ትምህርትን፣ ክህሎትንና እውቀትን ማግኘት፣ መሻሻልና መቻቻልን፣ ባህላዊ ግንኙነትን ማጠናከርን፣ ለመማር መነሳሳት፣ ስነልቦናዊ ጤናማነት፣የትምህርት ይዘትን በተመለከተ ጥሩ እይታ መኖርን፣ ቡድናዊ መማር ክህሎትንና፣ ችግሮችን ለመፍታት፣

ሀላፊፊነትን ለመውሰድ፣ ክህሎትን ለማዳበርና ለውጥ ለማምጣት እድል የሚሰጥ ነው (Slavin 1983፣ London 2005)።

እንደ Agnihotri፣Ngorosh (2018) ብያኔም ተማሪዎችን በትናንሽ ቡድን ከፋፍሎ ማስተማር ከማስተማሪያ መንገዶች አንዱ ሆኖ በመምህር መራሽ ብቻ ተማሪዎችን ማስተማር ተማሪውን ፍዝና አዳማጭ ብቻ እንዲሆን የሚያደርግ ሲሆን ከዚህ በተለየ መንገድ ቡድናዊ መማር ስልትን መጠቀም ለትምህርት ሳቢና ማራኪ በመሆኑ ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። ምክንያቱም ቡድናዊ መማር ትምህርታዊና ሳይንሳዊ መማርን የሚከተል ነው። አክለውም በትናንሽ ቡድን ተማሪዎችን ከፋፍሎ ማስተማር ተማሪ ተኮር የሆነ አቀራረብና ሁሉንም ተማሪዎች በእኩል ደረጃ በአንድ ርዕሰ ጉዳይላይ በመወያየትና ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ የሚጠቅም ነው።

በDennick & Exley (1998) እምነት በቡድን መማር የተግባቦትን ክሂል ለማጎልበት፣ጥልቅ አሳቢነትን ለመሆን፣ውሳኔ የመስጠት አቅምን ለማጎልበት፣የተለያዩ እውቀቶችን ለማዳበር እጅግ በጣም ጥሩ ስልት ነው። Davis (1993፣1)በበኩላቸው በቡድን መማር ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ የሚማሩበት በሂደቱ ላይ ንቁ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ነው።

## 2.3.ቡድናዊ መማርና ትውረታዊ አቅጣጫዎች

የሰው እድገት ከግለሰብ ይልቅ በማህበረሰባዊ ግንኙነት ላይ የተመሰረተ ነው(Gibbons 2002)። ይህጥናትም በዋናነት መሰረት ከሚያደርጋቸው ትውረቶች አንዱ ማህበራዊ ግንባታዊያን ትውረት ነው። የዚህ ትውረት አቀንቃኝ Vygotsky (1978) ሲሆን የትውረቱ ስያሜው አእምሮታዊ እድገት ማህበረ ታሪካዊ ትውረት በመባል ይጠራል።የትውረቱ ዋናውእይታ ተማሪዎችከሌሎች አቻዎቻቸው ጋር በሚያደርጉት ግንኙነት መስተጋብር ውስጥ ርስበርሳቸውይማማራሉ፣ተማሪዎች የጓደኞቻቸውን ባህሪ፣ አመለካከት፣ስሜት በመመልከት፣በመኮረጅና ሰርቶ በማሳየት ያንን ነገር ወደ ራሳቸው ባህሪ ሊያመጡ ይችላሉ።  ሰው ዕውቀት የሚያገኘው በማህበራዊ ተራክቦ አውድ ውስጥ ከሰዎች ልምድ በመቅሰምና በምልከታ ነው። አክለውም ሰዎች በማየትና ወደ ራሳቸው በማምጣት መተግበር ነው።

በVygotsky (1978) አባባል የልጆች አእምሮአዊ እድገት የተመሰረተው የበለጠውን ከሌሎች እውቀት ካላቸው ጓደኞቻቸው ጋር በጋራ ሲሆን መጀመሪያ በግልካላቸው እውቀት የበለጠ ይማማራሉ። በመሆኑም ይህ ትውረት በስፋት የሚያተኩርበት ዋና ነገር ሰዎች በግል

ከሚያከናውኗቸው ተግባራት ይልቅ በተሻለ ሁኔታ መማር የሚችሉት ሌሎችን እየተከተሉ ለመማር በሚያደርጉት ጥረት መሆኑን ያመላክታል፡፡

ሁለተኛው የጥነቱ ተተኳሪ አእምሮታዊ ግንባታዊትውረት ነው፡፡ በዚህ ትውረት አተያይ ተማሪዎች አንድን ጽሁፍ አንብበው ከመረዳት ጋር የተያያዘ በመሆኑና አንዱ አንብቦ ካገኘው እውቀት በሌሎች እርዳታ የሚያገኙት እውቀት የበለጠ የሚማር መሆኑን የሚያመላክት ስለሆነ ይህ ጥናትም ከአእምሮአዊ ግንባታ ትውረት ጋር ይያያዛል፡፡ Sheridan (1981) አገላለፅ አእምሮአዊ ንድፈ ሃሳብ ፅሁፍን አንብቦ የመረዳት ሂደት በፅሁፍና በአንባቢው ነባር እውቀት መካከል የሚደረግ ንቁ ተሳትፎ የሚፈጥር ነው፡፡

## 2.4.የቡድናዊ መማር ስልት አይነቶች

እንደ Davis (1993) አከፋፈል ቡድናዊ መማር ኢ-ቀጥተኛና ቀጥተኛ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ ኢቀጥተኛ ቡድናዊ መማር ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ሁለት ወይም ሶስት ሆነው አንድን ሀሳብ ለመረዳት ለሁለት ደቂቃ ባልበለጠ አጭር ጊዜ ጥያቄ የሚጠያየቁበትና ችግር ለመፍታት ጥረት የሚያደርጉበት ቡድናዊ መማር ነው፡፡ ሁለተኛው ቀጥተኛ ቡድናዊ መማር ስልት ሲሆን ዝርዝር ተግባራትን ለማከናወን የሚመሰረት ነው፡፡ ያውም አንድን ተግባር በአንድ ክፍለ ጊዜ ለመጨረስ የሚመሰረት፣አንድን ሀሳብ ለመዘገብ ሞዴል የሆኑ ተማሪዎችን በመመልከት ርስ በርሳቸው በመተጋገዝ ለረጅም ጊዜ የሚሰሩት ነው፡፡ ይህ ቡድናዊ አመሰራረትተማሪዎችን የሚያበረታታና ተማሪዎች ከቡድናዊ መማር የተለያዩ ክህሎትን እንዲያገኙ በማሰብ የሚመሰረት የቡድን አመሰራረት አይነት ነው፡፡

እንደ Edmunds & Brown (2010)፣Dennick&Exley (1998)የቡድናዊ መማር ስልትን አከፋፈል በተመለከተ ዝርዝርና አጠቃላይ ተብሎ ይከፈላል፡፡ ዝርዝር የሚባሉት ዘዴዎች ሲያስረዱ ደረጃን የተከተለ ውይይት(step by step discussion) አንዱ ሲሆን መምህሩ ቡድናዊ ተግባራትን ወይም ጥያቄዎችን በቅደም ተከተል የሚያቅድበት እና ቡድኑን ቁጥጥር የሚያደርግበትነው፡፡

ሌላው የቡድን መማር ነጻ ውይይት ሲሆን በዚህ መማር ስልት ተማሪዎች የሚያበረታቱበት፣ ተማሪዎች በነጻነት የሚወያዩበት፣መምህራን ቡድናዊ ውይይቱን የሚያጠቃልሉበት ዘዴ ነው፡፡ ሶስተኛ በነጻነት በጋራ ማሰብ፣ይህ ቡድናዊ መማር ዘዴ ሀሳብን በነጻነት መግለጽ፣ሀሳብን

ያለገደብ መግለጽ ነው። ቡድናዊ መማር ዘዴ ተማሪዎች ርስ በርሳቸው በሚያደርጉት ሚና ጨዋታ ውስጥ የተግባቦት ክሂላቸውን የሚያጎለበትበትና መምህራን ስለ ቡድናዊ ውይይቱ አስተያየት የሚሰጡበት ነው። አራተኛ በቡድን መማር (group learning) ተማሪዎች ያለ አንዳች መምህር ጣልቃ ገብነት ርስ በርሳቸው በነጻነት የሚማማሩበት ስልት ነው።

አጠቃላይ የሚባሉት ደግሞ የቡድናዊ መማር ዘዴዎችን ሲያስረዱ የማሰብ ጊዜ(thinking time)፣ በጋራ መማር(leanig group)፣የተለያዩ ተግባራትን ለተለያዩ የቡድን አባላት መስጠት(Jigsaw)፣ ስልጠና(workshops)፣ችግር ፈቺ ስልት ናቸው።

የቡድናዊ መማር አይነቶች ቀጥተኛና ኢ-ቀጥተኛ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ። ቀጥተኛ ብለሀቶች ስር የሚመደቡት ትውስታ፣ አእምሮታዊ ማካካስ ወዘተ ሲሆኑ ኢቀጥተኛ የንባብ ብለሀቶች የሚባሉት ልእለ አእምሮታዊ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ ወዘተ ሲሆኑ በማህበራዊ ብለሀቶች ስር ደግሞ ጥያቄና መልስ፣ከሌሎች ጋር በመተባበር መማር፣ በቡድን ተከፋፍሎ በመተጋገዝ መማር ወዘተ የሚባሉ ይካተታሉ (Oxford 1990) ።

## 2.5.የቡድናዊ መማር ጠቀሜታ

ይህ ጥናት በዋናነት ቡድናዊ መማር ለኢ-አፍፌት ተማሪዎች አንብቦ መረዳትና የማንበብ ተነሳሽነትን ለማጎልበት ያለውን ጠቀሜታ የመረመረ ነው። በመሆኑም የቡድናዊ መማርን ጠቀሜታ በተመለከተ Slavin (1983)፣ Burke (2011 ) ተማሪዎች በቡድን እንዲሰሩ ወይም እንዲማሩ ማድረግ እያንዳንዳቸው በግል የሚያውቁትን ይዘው በቡድን ሲወያዩ ወይም ሲማሩ ይበልጥ ውጤታቸው እንዲሻሻል ለውጥ እንዲኖራቸው ለማድረግ የሚጠቅም፤ ከግል መማር ይልቅ በቂ መረጃን ለማግኘት፣ ልምድን ለመለዋወጥ፣ ጥልቅ አሳቢነትን፣በከፍተኛ ደረጃ ለማስታወስ፣ የበለጠ ለመማር፣ ርስ በርስ ለመማማር ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው።

እነደ Johnson Johnson& Holubeck (1990) እምነትም በቡድን መማር ስልት ያለው ጠቀሜታ መሻሻልና መቻቻልን፣የተለያዩ ባህላዊ ግንኙነትን ማጠናከርን፣መረጃ መለዋወጥን፣ ትምህርታዊ አፈጻጸምን፣ክህሎትና እውቀት ማግኘትን፣የእውናዊ አለም ችግር ማቃለልን፣ ለመማር መነሳሳትን፣ለማህበራዊ ጉዳዮች በራስ መተማመንን፣ስነልቦናዊ ጤናማነትን እና ክትትልን የሚያስገኝ ነው። ዘዴዎች ተማሪዎች በትምህርት ሂደት ውስጥ እንዲገናኙና መምህር መራሽ የሆነውን በመጻፍ ብቻ የሚካሄደውን የማስተማር ስልት ያስቀረ ነው።

ጥናቱ ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት መምህር መራሽ በሆነ መንገድ ብቻ ማስተማር ተማሪውን ፍዝ አድማጭ ማድረግ በመሆኑ ከዚህ ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ቡድናዊ መማር በተለየ አይነት ሳቢና ከፍተኛ ትኩረት በመስጠት ትምህርታዊ እና ሳይንሳዊ የመማር ዘዴን በመከተል ማስተማር ማበረታቻና ትምህርታዊ ችግሮችን መፍቻ ነው Agnihotri፣Ngorosha2018)፡፡

ስለ ቡድናዊ መማር ስልት ውጤታማነት በተለያዩ ትምህርት ቤቶች መገምገም ተገቢ መሆኑን እንዲሁም በቡድን ማስተማር ተማሪ ተኮር የሆነ አቀራረብና ሁሉንም ተማሪዎች በአንድ ላይ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በመወያየትና በንቃት መማር ውስጥ እንዲገቡ የሚያግዝ፤ የርስ በርስ ተግባቦትን ለማጎልበት፣ጥልቅ አሳቢ ለመሆን፣አብሮ የመስራት ባህልን ለማጎልበት፣ውሳኔ ለመስጠት፣ከሌሎች ዕውቀትን ለማግኘት፣በክፍል ውስጥ ምቹ የመማር አከባቢን ለመፍጠር፣ ቀልጣፋና ንቁ የመማር ክንውንን የሚያመጣ፣የተማሪዎችን የርስ በርስ ግንኙነት የሚፈጥር በጣም ጥሩ የማስተማር ዘዴ ነው በማለት ተቀሜታው ተገልፀል (Meo 2013፤ Dennick ፣ Exley 1998) ፡፡

እንዲሁም ተማሪዎች የትምህርቱን ይዘት ከመጀመሪያው ጀምሮ በቡድን መማርን ተግባራዊ የማድረግ ስልት በሚለው ጽሁፋቸውንቁ መማር በሚገባ እንዲያውቁት፣በመካከላቸው ፍኩኩር አንዲኖር፣በጋራእንደወያዩ ርስበርስ እዲገማገሙ፣እንዲከራከሩ ጥልቅ አሳቢ እንዲሆኑ፣ ለሚጠየቁት ጥያቄ የተደራጀ ምላሽ እንዲሰጡ፣ጥሩ አድማጭ እንዲሆኑ፣ክሂሎትንና እውቀታቸውን በልምምድ እና በንባብ እንዲያጎለብቱ ያደርጋል(Kitchen 2012፣Brown 2010)፡፡
በዚህ ጥናትም የተማሪዎችን ለማንበብ ተነሳሽነት እንዲኖራቸው፣ርስ በርሳቸው እንዲፎካከሩና አንብቦ የመረዳት ክሂል ችሎታቸው እንዲጎለበት አስተዋጽኦ ከሚያደርጉ ስልቶች አንዱ ቡድናዊ መማር ነው፡፡ ንቁ መማር ከፍዝ መማር የበለጠ ተማሪዎች አንዱ ከሌላው የሚማርበትና ንቁ የሆን የመማር ማስተማር ሂደትን መገንዘብ የሚቻልበት እንጂ ፍዝ አድማጭ መሆን እንዳልሆነ ተማሪዎች በጋራ በመወያየት ሲማሩ አንዱ ከሌላው የበለጠ እውቀቱን እንዲያጎለብት ያደርጋል(Graffam 2007)፡፡
እንደ Johanson (1996) አተያይም ቡድናዊ መማር ስልት በቡድን ተከፋፍለው ለሚማሩ ተማሪዎች መምህራን ሁኔታን አመቻች የትምህርቱን ሂደት ተቆጣጣሪ መሆናቸው፣ተማሪዎችን ርስበርስ ሀሳብ እንዲለዋወጡ፣ሀላፊነት እዲወስዱ፣ርስ በርሳቸው እንዲቀባበሉ፣ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ፣እዲወያዩ ማድረጉ ቁልፍ ጉዳይ ነው፡፡

በቡድን መማር መቻቻልን፣ባህላዊ ግንኙነትን፣የመረጃ ልውውጥን፣አዳዲስ ዕውቀትና ክህሎትን ማግኘትን፣ችግር መፍታትን፣ለትምህርት ጥሩ አመለካከት መኖርን፣ለትምህርት መነሳሳትን፣ ማህበራዊ ግንኙነትን ማስፋፋትን፣በራስ መተማመንን፣ጥሩ አመለካከትን ማዳበርን እና ጥሩ ስነ ምግባርን የሚያመጣ ወይም ለማስገኘት የሚረዳ ነው (Johnson እና Holubec 1994)፡፡

Boruvkova& Emanovsky (2016) ቡድናዊ መማር ስልት በተማሪዎች ማህበራዊ ግንኙነት ላይ ያለው አዎንታዊ ጠቀሜታ በሚለው የጥናት ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናታቸው ውጤት ቡድናዊ መማር ስልት ተማሪዎችን በክፍል ወስጥ ወደ አንድነት ለማምጣት አዎንታዊ ጠቀሜታ አለው፡፡ ይኸውም በክፍል ውስጥ ራሳቸውን አግልለው ያሉ ተማሪዎች ከሌሎች ጋር በቡድን በማቀናጀት አብሮነት እንዲፈጥሩ ለማድረግ ይጠቅማል::

እንደ Slavin (1983) ፣Putnam (1997) ፣Johanson (1996) Davis (1993፣1) ቡድናዊ እይታ በቡድን መማር ተማሪዎች በግል ያላቸውን እውቀት ይዘው ወደ ቡድን በማምጣት ሲማማሩ ውጤታቸው ይበልጥ እንዲሻሻል ወይም ከፍ እንዲል፤ በአንድ ክፍል ውስጥ በርካታ ተማሪዎች ሲማሩ መምህራን በመፃፍ ብቻ ማስተማር በቂ አይደለም ይልቁንም በቡድን መማር ዘዴን በመጠቀም ማስተማር ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን፤ በቡድን ተከፋፍለው ለሚማሩ ተማሪዎች መምህራን ሁኔታን አመቻች የትምህርቱን ሂደት ተቆጣጣሪ መሆናቸው፣ተማሪዎችን ርስበርስ ሀሳብ እንዲለዋወጡ፣ሀላፊነት እዲወስዱ፣እርስ በርሳቸው እንዲቀባበሉ፣ቅድመ ዝግጅት እንዲያደርጉ፣እዲወያዩ ማድረጉ ቁልፍ ጉዳይና በቡድን መማር ተማሪዎች በተሻለ ሁኔታ የሚማሩበት በሂደቱ ላይ ንቁ ተሳታፊ የሚሆኑበት እንደሆነ አመላክተዋል፡፡

## 2.6.በቡድናዊ መማር ሂደት የመምህርና ተማሪዎች ሚና

በቡድን መማር ሂደት ውስጥ የመምርና ተማሪዎች ሀላፊነትና ሚና ትልቅ ጠቀሜታ አለው፡፡ ይኸውም ለመወያየት፣በጥልቅት ለማሰብና ለልምድ ልውውጥ አስፈላጊ ሲሆን በመምህርና ተማሪ መካከል ያለ ሀላፊነትና ሚና የተለያየ ነው፡፡ የመምህራን ሚና ቡድኑን ማስጀመርና ቡድናዊ ተግባራትን መቆጣጠር፣መምራት፣የመማር ሂደቱን ሁኔታ አመቻች፣የቡድኑን ውይይት እንደተጠበቀ ማስቀጠል፣መረጃን ማስተዋወቅ፣ተማሪዎች በጥልቀት እንዲያስቡ ማድረግ፣ቡድኑን በሃላፊነት መምራት፣አስተያየት ሰጪ፣ቡድኑን በበላይነት መቆጣጠርና ውይይቱን ማጠቃለል ነው፡፡ እንዲሁም መምህሩ በተጓዳኝ የትምህርት መሳሪያዎችን ማዘጋጀትና በመዋቅራዊ ሂደቱ

መሳተፍ፤ የተማሪዎችን ሀላፊነትና ሚና በተመለከተ ደግሞ ጥልቅ አሳቢነት፣የርስ በርስ ተግባቦትና በተግባራት ላይ ትኩረት መስጠት፣እርመት መውሰድ፣መሳተፍና መረዳት ጥያቄ መጠየቅ ነው (BJHM 2009)፡፡

## 2.7.በቡድን ለመማር አስፈላጊ የሆኑ ተግባራት

በቡድን ለመማር አስፈላጊ የሆኑ ተግባራት በመጀመሪያ ክፍል ማደራጀት፣ቡድን መመስረት፣ ትምህርት ማቅረብ፣የቡድን ተግባራትን መስጠት፣ቡድኑን መከታተል፣ሁሉም ቡድን መሳተፉን ማረጋገጥ ወዘተ ናቸው (Davis 1993፣Jacobs 2006)፡፡

### 2.7.1.መማሪያ ክፍልን ማደራጀት

የክፍል አደረጃጀትንDavis (1993) ሲያስረዱ በቡድናዊ መማር መጀመሪያ ሊደረግ የሚገባው የተማሪዎችን መማሪያ ክፍል ሊደራጅ የሚገባ ሲሆን ያውም የሚማሩበት ክፍል በጊዜ ተወስኖ ተማሪዎች ተገኝተው እንዲማሩበት ይደራጃል፡፡

### 2.7.2.ቡድን መመስረት (የክፍል ውስጥ ቡድን አመሰራረት)

የክፍል ውስጥ የተማሪዎች የቡድን አመሰራረትን በተመለከተ ተማሪዎችን በቡድን ለማስቀመጥ ተመሳሳይ ችሎታን ፣ቅይጥ ችሎታን፣የክህሎት ብቃትን፣ ዕድሜን፣ጾታን፣የክፍል ደረጃን ወዘተ መሰረት ያደረገ የቡድን አመሰራረቶች ያሉ እንደሆነና ቡድን ከሁለት አባላት ጀምሮ ይመሰረታል፣ ጥንዶች ቡድን ይሆናሉ በማለት Jacobs (2006) አስረድተዋል፡፡ አክለውም ተማሪዎች በራሳቸው በመመራረጥ ቡድን መመስረት እንዲወስኑ፣በእጣ በመመደብ ቡድን እንዲመሰርቱ፣ መምህራን በራሳቸው ተማሪዎችን የሚያስቀምጡት የቡድን አመሰራረት ተጠቅሞ ተማሪዎችን በተለያዩ መንገዶች ማቧደን እንደሚቻል ያስረዳሉ፡፡ የቡድን ቆይታ ጊዜን በተመለከተ ደግሞ ለአጭር እና ረጅም ጊዜ ቆይታ አቧድኖ መመስረት እንደሚቻል ያስገነዝባሉ፡፡

BJHM (2009) በበኩላቸው በቡድናዊ መማር ሂደት የክፍል ውስጥ የተማሪዎችን አቀማመጥ በተመለከተ በተለያየ መልኩ ተማሪዎች እንዲቀመጡ አድርጎ ማስተማር ይቻላል፡፡ ያውም በምክንያታዊ ጊዜ ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ በመማር ሂደት ማስቀመጥ ሲሆን የአቀማመጥ አይነቶቹ በመምህርና ተማሪዎች መካከል ያለ ትይዩ ቡድናዊ አቀማመጥ፣ የU ቅርጽ ቡድናዊ አቀማመጥ፣የፈረስ ኮቴ ቡድናዊ አቀማመጥ፣ መምህሩ አልፎ አልፎ የሚካተትበት ቡድናዊ አቀማመጥና መምህሩን ሙሉ በሙሉ በቡድኑ ያካተተ ቡድናዊ አቀማመጥ ናቸው በማለት ያስረዳሉ፡፡




ምስል1. በመማሪያ ክፍል ውስጥ የተማሪዎች ቡድናዊ አቀማመጥ ምንጭ፡- (BJHM, 2009)

ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡

ይህን ጥናት ለማካሄድም ከላይ የቀረበውን የቡድን አመሰራረጥ መሰረት በማድረግ በመጀመሪያ ለመምህሩ ስለ ቡድናዊ መማር አጠቃላይ ግንዛቤ ከተሰጠ በኋላ የሙከራ ቡድኑን በክፍል ውስጥ በቡድናዊ መማር ሲተገብር በተሸለ አንብቦ የመረዳት ክሂሎት ያላቸውን ተማሪዎች በያንዳንዱ ቡድን በማንበብ ደከማ ከሆኑ ተማሪዎች ጋር በመመደብ በአንድ ቡድን ውስጥ ከአምስት እስከ ስድስት ተማሪዎች በ (U) ቅርጽ እንዲያስቀምጥ ተደርጓል፡፡

ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በምስል አንድ የተቀመጠው ስዕላዊ መግለጫ የሚያሳየው ተማሪዎች በክፍል ውስጥ በቡድናዊ መማር ሂደት እንዴት በተለያዩ መንገድ ተቀምጠው መማር እንደሚችሉ ነው፡፡ ሆኖም ትይዩ ቡድናዊ አቀማመጥ፣ በምስሉ እንደተመላከተው ተማሪዎቹ ፊትና ኋላ በመሆን ጎን ለጎን ከመምህሩ ትይዩ ተቀምጠው በቡድን የቀረበላቸውን ትምህርት ይዘት የሚከታተሉበትን ሁኔታ የሚያሳይ ነው፡፡

በሁለተኛው ምስል የተቀመጠው የክፍል ውስጥ ቡድናዊ አቀማመጥ የU ቅርጽ ቡድናዊ አቀማመጥ የሚባለው ሲሆን ተማሪዎች ጎን ለጎንና ከኋላ ተቀምጠው በመምህሩ በኩል ክፍተት የሚኖርበትና ቡድናዊ ተግባራትን የሚያከናውኑበትና መምህሩ በፍለፊት በኩል ባለው ክፍተት በኩል ሆኖ የሚያስተምርበት ነው፡፡ በሶስተኛው ምስል የሚታየው የፈረስ ኮቴ የሚባለው ቡድናዊ አቀማመጥ ሲሆን ተማሪዎቹ ክብ ሰርተው በመቀመጥ የቀረበላቸውን ተግባር ሲያከናውኑ መምርሩ ከቡድኑ ወጣ ብሎ ተማሪዎቹን የሚከታተልበትና የሚያስተምርበትን ቡድናዊ አቀማመጥ የሚያመላክት ነው፡፡ አራተኛው ቡድናዊ አቀማመጥ ተማሪዎቹ በጠረጴዛና መምህሩ ፊት ለፊት ሆነው በመቀመጥ የቀረበላቸውን ተግባራት በቡድን የሚያከናውኑ መሆኑን የሚያመላክት ነው፡፡ በመጨረሻው ምስል ላይ የተመላከተው ቡድናዊ አቀማመጥ ተማሪዎች ክብ

ሰርተው የቀረበላቸውን ተግባራት ሲያከናውኑ መምህሩም ከተማሪዎቹጋር በመሆን ተግባራትን ለተማሪዎቹ በመስጠትና ማከናወናቸውን በቅርበት የሚከታተልበትን ሁኔታ የሚያመላክት ነው።

በመሆኑም ይህን ጥናት ለማካሄድ ለተመረጠው መምህር ተማሪዎችን በክፍል ውስጥ እንዴት ቡድናዊ መማርን ማስቀመጥ እንደሚገባው በማሰልጠን ልምምዱ እንዲቀጥል ተደርጓል። መምህሩም ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው የክፍል ውስጥ ቡድናዊ አቀማመጥ ውስጥ የሙከራ ቡድኑን ተማሪዎች እንደ ክፍሉ አመቺነት በየU ቅርጽና አልፎ አልፎ የፈረስ ኮቴ አቀማመጥን ተጠቅሞ ተማሪዎች ርስበርሳቸው በመተያየት እንዲነሳሱ በማድረግና አንብቦ የመረዳት ትምህርት ይዘትን በቡድን እየተጋገዙ እንዲያነቡ በማድረግ የማስተማር ሂደቱን ተግብራዊ አድርጓል።

### 2.7.3 ትምህርቱን ማቅረብ

እንደ Davis (1993፣147-51) አገላለጽ መማሪያ ክፍል ከተደራጀና ተማሪዎች እንደየ ፍላጎታቸው በተመጣጣኝ ቁጥር ቡድን እንዲመሰርቱ ተደርጎ በየቡድኑ ተከፋፍለው ከተቀመጡ በኋላ ለቡድኑ የሚሆን የቡድን ተግባራትን መስጠትና ተማሪዎቹ በታቀደው ዕቅድ መሰረት በየቡድናቸው ተግባራቱን ማከናወናቸውንና አለማከናቸውን መከታተል ይገባል።

በዚህ ጥናትም ከላይ በተነሱት የሙሁራኑ ሀሳቦች መሰረት ቡድናዊ ትምህርትን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ ለሙከራ ተማሪዎቹ ትምህርቱን ከመስጠቱ አስቀድሞ በመማሪያ ክፍልን በማደራጀት፣ቡድን የመመስረት፣ተማሪዎችን በቡድን የማስቀመጥ ትምህርትን የማቅረብ ተግባራትን ተከናውኗል።

## 2.8.የቡድናዊ መማር ስልት መርሆች (መመሪያ)

ተማሪዎችን በመማሪያ ክፍል ውስጥ በቡድን ለማስተማር በቅደም ተከተል የቡድናዊ መማር መመሪያዎችን ተግባራዊ ማድረግ ተገቢ ነው(Davis 1993፣147-51)። ይኸውም፡-

1. ቡድን መመስረት፤
2. በቡድኑ የሚከናወኑ ተግባራትን ማዘጋጀት፤
3. በመማሪያ ክፍል ውስጥ ምን ያህል ቡድን እንደተመሰረተ በትክክል ማወቅ፤
4. ለያንዳንዱ ቡድን መለያ ወይም መጠሪያ ስም መሰየም፤
5. ቡድኑ በምን አይነት ስልት የተሰጠውን ተግባር ሊያከናውን እንደሚችል መወሰን፤

6.አጠቃላይ የቡድኑን የአሰራር ስልት ማወቅ፤

7.ቡድናዊ ትምህርት መስጠት፤

8.ትምህርቱ በስረዓተ ትምህርት የሚካተት ወይም ከስረዓተ ትምህርት አንጻር ማስተካከያ የሚደረግበት መሆኑን ማረጋገጥ፤

9. ለትምህርቱ ምን አይነት መርጃ መሳሪያ ተገቢ ነው? የሚለውን መገንዘብ፤

10.የትምህርት ይዘቱ መምህሩ በቀጥታ ከማስተማሩ ባሻገር ለቡድኑ ቢቀርብ ተገቢ ነው? የሚለውን መለየት ናቸው፡፡

ይህ ጥናትም ቡድናዊ መማር ምን ያህል የኢ-አፍ ፈት ተማሪዎችን አንብቦ መረዳትን ለማጎልበትና የማንበብ ተነሳሽነትን ሊፈጥር እንደሚችል ከዚህ በላይ የተዘረዘሩትን ሀሳቦች መሰረት በማድረግ ከተጠኚዎች ቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳትና የጹሁፍ መጠይቅ በማዘጋጀት እንዲሁም ድህረ ቡድን ተኮርን በመማር ሂደት ምልከታ በማድረግ የተገኘውን መረጃ በመሰብሰብና በመተንተን የተገኘውን መረጃ ውጤት ለማወቅ ተችሏል፡፡

## 2.9.ቡድናዊ መማር ስልት አንብቦ የመረዳት ክህል ጋር ያለው ግንኙነት

አንብቦ የመረዳት ብልሀቶችን ምንነትና አከፋፈል በተመለከተ የተለያየ ብያኔ ያላቸውና በተለያየ መንገድ የሚከፈሉ ናቸው፡፡ አንብቦ የመረዳት ብለሀቶች ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ oxford (1990)፡፡ ቀጥተኛ ብለሀቶች ስር የሚመደቡት ትውስታ፣ አእምሮታዊ ማካካስ ሲሆኑ ኢቀጥተኛ የንባብ ብለሀቶች የሚባሉት ልእለ አእምሮታዊ ፣ማህበራዊ፣ ስሜታዊ ናቸው፡፡ በማህበራዊ ብለሀቶች ስር ደግሞ ጥያቄና መልስ፣ ከሌሎች ጋር በመተባበር መማር፣በቡድን ተከፋፍሎ በመተጋገዝ መማር ወዘተ የሚባሉ ይካተታሉ፡፡ ከማህበራዊ ብለሀቶች ውስጥ በቡድን ተከፋፍሎ መማር አንዱ ሲሆኑ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ትምህርት ይዘትን በተናጥል ከመማር ይልቅ አንዱ ሌላውን በማገዝ ወይም ርስ በርስ በመተጋገዝ መማር የሚል እሳቤን የሚያመላክት ነው፡፡

Davis (1993) በበኩላቸው የቡድንን አከፋፈል በተመለከተ ተማሪዎች በትናንሽ ቡድን ሆነው ሲማሩ በይበልጥ እደሚማሩና የተማሩትንም የትምህርት ይዘት ለረዥም ጊዜ ትውስታ ይሆናቸዋል፡፡ እንዲሁም በቡድን መማራቸው የበለጠ በክፍል ውስጥ ደስተኛ እንደሚሆኑ በቡድን ከፋፍሎ ማስተማር ዘዴ የተለያዩ መጠሪያዎች የተሰጠውና ከልዩነቱ ውስጥ ውስኑን ብንመለከት ትብብራዊ መማር፣ በጥቅል መማር፣በጋራ መማር፣ ማህበራዊ መማር፣ የቢጤ ቡድናዊ መማር፣ ቡድናዊ መማር ዘዴ፣ የጥናት ቡድን፣ በጋራ መስራት፣ ክበባዊ ቡድን ወዘተ ናቸው፡፡ ቡድናዊ መማር ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ተብሎ በሁለት ሲከፈል ኢቀጥተኛ የሆኑት ተማሪዎችን

በክፍል ውስጥ ተከፋፍለው ጥያቄ በመጠያየቅና በመወያየት ችግሮቻቸውን እንዲፈቱና ለውጥ ለማምጣት ጥረት ማድረግን ያመላክታል በማለት ያስረዳሉ፡፡

በመሆኑም ይህ ጥናትም በቡድን ተከፋፍሎ መማር ዘዴን የሚተገብር እንደመሆኑ መጠን በዋናነት የOxfrdን አንብቦ የመረዳት ብለሀቶች አከፋፈልን መሰረት ያደረገ ነው፡፡ ጥናቱ ከማንበብ ብለሀቶች ውስጥ አንዱ የሆነውን ቡድናዊ መማር ዘዴን የሚመረምር በመሆኑ ዘዴውና አንብቦ የመረዳት ክሂል ብለሃት ተዛምዶ ወይም ግንኙነት ያለው መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ብለሀቱም በቀጥታ ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ግንኙነት አለው፡፡

## 2.10.ተማሪዎች ከቡድናዊ መማር የሚያዳብሯቸው ክሂሎቶች

ተማሪዎች በቡድናዊ መማር የሚያጎለብቷቸው ዋና ዋና ክሂሎች የሚባሉት በቡድን ውይይት ጊዜ ርስበርሳቸው ጥያቄ መጠያየቅ፣የቡድን አባላቱ ርስ በርስ መደማመጥ፣መልስ መስጠት፣ በቀረበው ሀሳብ ላይ ገለጻ ማድረግ፣በሀሳቡ ላይ ዝግጅ መሆን፣በጋራ እንዲሰሩና ለወጥ ለማምጣት ወይም ተሻሽለው ለመገኘት፣ርስ በርሳቸው በመተጋገዝ አንዱ ከሌላው እንዲማር፣በመካከላቸው መግባባት እንዲኖር፣ተወዳዳሪነት ወይም በመካከላቸው ፍክክር እንዲፈጠር፣አእምሮአዊ ግንዛቤ እንዲያገኙ፣ጥልቅ አሳቢ፣ምክንያታዊ፣ችግር ፈቺና ፈጣሪ እንዲሆኑ እንዲሁም ርስ በርሳቸው መወያየት እንዲችሉ ይረዳቸዋል፡፡

ቡድናዊ መማር ለመምህሩም በቡድናዊ ማስተማር ሂደት የቡድኑን አባላት በቀላሉ ለመቆጣጠር ናዝግጅት ለማድረግ፣ቡድናዊ ውይይትን ለማስጀመርም ሆነ ለማጠቃለል፣ጥያቄእንዲጠይቅ፣ እንዲያዳምጥ፣ቡድናዊ ውይይቱን እንዲያስጀምርና የውይይቱን ዋና ዋና ሀሳብ በመጥቀስ እንዲያጠቃልል ያግዘዋል (Edmonds and Brown 2010)፡፡

እንደ Dickson and Harige (2004)፣Brown and Atkins (1988) አባባል በቡድናዊ መማር ማስተማር ሂደት ጥያቄ መጠያየቅ ያለውን ጠቀሜ ሲያስረዱ፣ተማሪዎች ርስ በርሳቸው ጥያቄ ሲጠያየቁ በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ፍላጎት እንዲኖራቸው፣ችሎታቸውን ከጓደኞቻቸው ጋር በማነጻጸር በምን ደረጃ ላይ እንዳለ እንዲገመግሙ፣ትምህርታቸውን በጥልቀትእንዲማሩ ለማድረግና እንዲበረታቱ፣እንዲነሳሱ፣በመካከላቸው የሀሳብ ልውውጥ እንዲኖር ያደርጋል፡፡

በቡድን መማርን በትክክል ለማስተማር ሊጠየቁ የሚገባቸው የጥያቄ አይነቶች ትክክለኛ መልስ ያለውና ግልጽ ጥያቄ፣የትውስታ ጥያቄ፣ተያያዥነት ያላቸው ጥያቀዎች፣የሚያበረታታቸውና የሚያሰራቸው ጥያቄ፣ፍንጭ የሚሰጡ ጥያቄዎች፣በጋራ እንዲመራመሩ ወይም አወያይ ጥያቄ ለመጠየቅ እገዛ ያደርጋል(Watts and Pedrus 2006፣broocfield and Preskill 2005)፡፡

የትውስታ ጥያቄዎች እንደ Anderson and kratwohl (2000)፣ Bloom (1956) ቡድናዊ ትምህርትን ለማስጀመር፣የተማሪዎችን የቀደመ ዕውቀት ለመፈተሽ፣ የቡድኑ አባላት ተገቢ ሀሳብ እንዳላቸው የሚጠቅም ነው፡፡ ተያያዥነት ያላቸው ጥያቄዎች ለቡድኑ አባላት መጠየቅ ሀሳቡን በቀላሉ እንዲረዱ ለማድረግ ይጠቅማል፡፡

ለቡድን አባላት አበረታች ጥያቄዎችን መጠየቅ ማለት በተቻለ መጠን ተማሪዎችን ሊያበረታቱ የሚችሉ ነገር ግን በጣም ቀላል ያልሆኑ ሊሆኑ ይገባል፡፡ ፍንጭ ሰጪ ጥያቄዎች ተማሪዎች ፍንጭ የማይሰጡ ጥያቄዎችን ከመጠየቅ ይልቅ ለቡድን አባላት አመራማሪ ጥያቄዎችን መጠየቅ ተማሪዎቹ ይበልጥ ስለ ርዕሰ ጉዳዩ መረጃን ለማግኘት በቡድን እንዲወያዩ፣እንዲጠይቁ የሚያደርግ መሆኑን ለመገንዘብ ይጠቅማል (Edmonds 2010፣Bligh 2000)፡፡

ተማሪዎች በቡድን መማር ሂደት ሊያጎለብቱት የሚገባው ክሂል ርስ በርስ መደማመጥ ሲሆን ከቡድኑ ውይይት በግልጽ የተባለውን ጉዳይ ካልተባለው ለመለየት መደማመጥ ተገቢ ነው፡፡ በቡድናዊ መማር መደማመጥ የሁሉም ሀላፊነት ቢሆንም መምህሩ በበላይነት መከታተል አለበት(Edmonds 2010)፡፡ አክለውም የማዳመጥ ደረጃዎች በፍጥነት ማዳመጥ፣በጽኑ ማዳጥ፣ ለመለየት ማዳመጥ፣ፍተሻዊ ማዳመጥና ጥናታዊ ማዳመጥ አሉ፡፡

ተማሪዎች በቡድናዊ መማር ለያጎለብቱት የሚገባ ክሂሎት መልስ መመለስ ሲሆን ይህ ክሂሎት ለተማሪዎቹ ከባድ የሆነ ክሂሎትና መምህሩ በቡድን ውይይቱ መካከል ጣልቃ በመግባት ማበረታታት ይገባዋል Hattie and Timperley (2007)፡፡ መምህሩ በጽሁፍ ተጨማሪ የሆኑ ጽብረቃዊ፣ማረጋገጫ፣ ሀሳቡን በሌላ መንገድ የመመለስ መልሶችን መመለስና ቡድኑን መቆጣጠር አለበት፡፡ ይህም ለተማሪዎቹ መበረታታትን፣የሀሳብ ግልጽነትን፣በራስ መተማመንን፣በቡድን ለመሳተፍ ጥረት ማድረግን፣ርስ በርሳቸው መተቻቸትን፣ፉክክርን እንዲፈጥሩ ስለሚያደርግ መልስ መመለስ ለቡድናዊ መማር ዘዴ በጣም ጠቃሚ ነው፡፡

እንደBrown 2006 አባባል ተማሪዎች በቡድን ከመማር የሚያጎለብቱት ክሂል ሀሳብን መግለጽ ሲሆን ገለጻ ችግሮችን ከሁኔታዎች እንዲረዱ የሚያግዝና ተማሪዎች ክሂሉን በልምምድ እንዲያዳብሩት ያደርጋል። በጥቅሉ ምሁራኑ ከዚህ በላይ እንደገለጹት ተማሪዎችም ሆኑ መምህራን በቡድናዊ መማር ማስተማር ሂደት ውስጥ በርካታ ክሂሎችን እያጎለበቱ የሚሄዱ መሆኑን መገንዘብ ተችሏል።

## 2.11. የቡድናዊ መማር ስልት ችግሮች

አንብቦ የመረዳት ክሂልን ከማስተማሪያ ስልቶች መካከል አንድም ፍጽም የሆነ ብቃት አለው የሚባል ስልት የለም (በድሉ ዋቅጅራ1996)። ማለትም ቡድናዊ መማር ምንም እንኳን ተማሪዎች ሌሎችን በመመልከት ለማንበብ የሚነሳሱና የቀረበላቸውን ጹሁፍ በውይይት ለመገንዘብ ጥረት ማድረጋቸውን የሚያመላክት ቢሆንም ከላይ ለመጠቆም እንደተሞከረው ቡድናዊ መማር ሙሉ በሙሉ  ከችግር የጸዳ ነው ማለት አይቻልም። እንደ Beebe Masterson (2003) በቡድናዊ መማር ሂደት በዋናነት የሚያጋጥሙ ችግሮች የሚባሉት በቡድናዊ መማር ሂደት ተማሪዎች ርስ በርሳቸው አለመግባባት፣ለቡድን ስራ የሚሰጡ ተግባራት በጋራ ያለመስራት ችግር መኖሩ፣በተሰሩ የተግባር ስራዎች ሁሉም ተማሪ አለመርካትና በቡድናዊ ክንውን የጊዜ እጥረት ናቸው። ሆኖም ቡድናዊ መማር በትምህርታቸው ደከም ለሚሉ ተማሪዎች በተሻለ ከሚሰሩ ተማሪዎችጋር በቡድን በማለማመድ ተማሪዎቹ በነጻነት በተሸለ ከሚያነቡ ተማሪዎች ጋር እንዲወያ ያደርጋል።

## 2.12.የተነሳሽነት ታሪካዊ ዳራ

እንደ Dornyei (2011) አገላለጽ የተነሳሽነት ታሪካዊ ዳራበ1960ዎቹ በኡጋንዳ የሁለተኛ ቋንቋ ተነሳሽነት በማህበረሰቡ ውስጥ እንደነበር ወይምእንደ ተጀመረ አመላክተዋል። የተነሳሽነት ሳይንሱ ይበልጥ እየታወቀና እየተሸሻለ የመጣው በ20ክፍለ ዘመን አጋማሽ አከባቢ (1990) ወዲህእንደሆነም ጠቁመዋል። እንደ አእምሮታዊያን አመለካከት ደግሞ ተነሳሽነት በ21ኛ ክፍለ ዘመን መጀመሪያዎቹ ጀምሮ እየተስፋፋመምጣቱን አመላክተዋል። እንደ ስነልቦናዊ ምሁራን አመለካከት የሰው ልጅ ተነሳሽነት በተፈጥሮ በሚመለከተው፣በሚፈልገውና በሚሰማው ነገር ላይ የሚያተኩር እንደሆነ ይገልጻሉ። እንደ Dornye &Emaushoda (2011) የተነሳሽነት ትውረቶች የሚባሉትን እንደሚገልጹት የተለያዩ የተነሳሽነት ትውረቶች አሉ። እነዚህም፡-አእምሮታዊ

የተነሳሽነት ትውረት፣አላማዊ የተነሳሽነት ትውረቶች፣ጥቅምን መሰረት ያደረገ የተነሳሽነት ትውረት (Expectancyvalue theories) እናየራስን እድል በራስ የመወሰን የተነሳሽነት ትውረት(selfe determination theory) ናቸው፡፡

በአእምሮታዊ ትውረት እይታ ተነሳሽነትከ (1990) ወዲህ እየተስፋፋ የሚገኝና አእምሮአዊ አወቃቀርን ለመተግበር ሚና የሚጫወት፣የግለሰብን ስነ ምግባርና ባህሪ ማስተካከያ መሆኑን አምነን የምንቀበለው የተነሳሽነት መረጃ ትውረት ቢሆንም በተለያ መኀበራዊና ባህላዊ ምክኒያቶች በተማሪዎች መነሳሳት ላይ ተጽእኖ ሊያደርሱባቸው የሚችሉ ጉዳዮችን የሚቀንስ ነው፡፡ ትውረቱ አከባቢያዊና ማህበራዊ ሁኔታዎች በግለሰብ ተነሳሽነት ላይ የሚሳድሩትን ተጽእኖ የሚስተካከልበት በመሆኑና በውስጡ ባህሪያዊ፣ራስን ውጤታማ የማድረግን፣ግምታዊነትንና ተግባራዊ ትውረቶችን ያካተተ በመሆኑ ለቡድናዊ መማር ዘዴ መሰረት ሊሆን ችሏል፡፡ አእምሮአዊ ተነሳሽነት ትኩረት ሊሰጠው የሚገባና ለጥልቅ አሳቢነት ሚና የሚጫወት መሆኑ ነው(Dornye & Ema ushoda 2011)፡፡

አላማዊ የተነሳሽነት ትውረቶች አላማን መሰረት ያደረገ የተነሳሽነት ትውረት ይህ ትውረት የግለሰብን አላማዊ ባህሪ ብቃት ልዩነትን ለመግለጽ የሚሞክር የሚልን እሳቤ ያለው ሲሆን ልዩነቱ አላማዊ ክብደት እና ዝግጅት ልዩነት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ አላማዊ ገለጻን መሰረት ያደረገ የተነሳሽነት ትውረት ይህ ትውረት አላማዊ መነሻን በማይመሳሰል መልኩ ተማሪዎች በትምህርት ቤት መማርንና ውጤታቸውን ማሻሻልን የሚገልጽ ነው፡፡ አላማን መሰረት የደረገ ይዘት ይህ ትውረት ግለሰባዊ አፈጻጸምንና ውጤት ላይ የሚያተኩር ሲሆን የተማሪዎች ተነሳሽነት በኣላማ የሚስተካከል መሆኑን አመላክቷል(Dornye&Emaushoda 2011)፡፡ ጥቅምን መሰረት ያደረገ የተነሳሽነት ትውረት ግለሰባዊ ተነሳሽነት አንድን ተግባር የማከናወን ብቃት እና በዚያ ተግባር ምን ያህል ውጤታማ እንደሚኮን ተገንዝቦ መስራት ነው የሚል ተነሳሽነት ነው፡፡

የራስን እድል በራስ የመወሰን የተነሳሽነት ትውረት ትውረቱ በጣም የሚታወቅ አጠቃላይና አስፈላጊ የተነሳሽነት ትውረት ሲሆን ከአካታች ይልቅ አግላይ ተነሳሽነትን የሚያሳይ እና ደስታን፣ እርካታን፣በራስ ስራ መዝናናትን እንዲሁም በአንድ ስራ ለመርካትና ጥሩ ውጤት ለማምጣት የሚደረግ ተነሳሽነት ነው (Dornye & Emaushoda 2011)፡፡

## 2.13.የተነሳሽነት ምንነት

ማንኛውም ውጤታማ የሆነ ሰው ለዚያ ተግባር ተነሳሽነት ስላለው መሆኑ ይታወቃል፡፡ እንደ Brown (1992) ብያኔ ተነሳሽነት (motivation) አንድ ነገር ለማድረግ የሚገፋፋ ውስጣዊ ፍላጎት

ወይም ውስጣዊ ግፊት ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡ እንዲሁም መቀስቀስ ቋንቋን ለመማር ቁልፍ ነገር መሆኑን የሚያመላክቱ ጥናቶች ስህተት የሌላቸው ናቸው በማለት ጠቅሰዋል፡፡

Walkerና Symon(1997)ን ጠቅሰው ተነሳሽነት የማይታይ ወይም የማይጨበጥና ብዙ ትርጓሜ ያለው ሆኖ ብዙዎቹ ተመራማሪዎች እንደሚስማሙበት የሰዎችን ባህሪና አቅጣጫ አመልካች መሆኑን የሚስማሙበት ሲሆን ያውም አንድን ተግባር ለመስራት መምረጥ፣በተግባሩ ጸንቶ መገኘት፣ተግባሩን ለመጨረስ መትጋት ወይም አንድን ተግባር እስከ ፍጻሜው መስራት፣ ተግባራትን በፍቃደኝነት መስራት፣ተነሳሶት መኖር ማለት ነው በማለት ገልጸዋል፡፡

Dornyei & Ushioda (2011) እንደገለጹት ተነሳሽነት የሰዎችን ተነሳሶት፣ምሪት፣ቅንጅት፣ ጉልህነትን፣ማጠናቀቅ የሚያመጣና የመገምገም እንዲሁም የመነሳሳት ፍላጎት ሂደት እና ፍላጎት የሚመረጥበት፣ቅድሚያ የሚሰጥበት እና ተግባርን ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ማድረግ ነው በማለት ያስረዳሉ፡፡

እንደ Krashen (1987) እምነት ብዙጊዜ ሁለተኛ ቋንቋን ለመልመድ የሚፈልግ ሰው ከፍተኛ ተነሳሽነት ካለው ቋንቋውን ለመልመድ ትልቅ አስተዋጽኦ አለው:: Brown(1994) በበኩላቸው ተነሳሽነት ውስጣዊና ውጫዊ በመባል በሁለት ይከፈላሉ በማለት ሲገልጹ አንድ ተማሪ ቋንቋ በመማር ረገድ ውስጣዊ ተነሳሽነት አለው የሚባለው ሌላ ተጨማሪ ጥቅም ለማግኘት ሳይሆን ቋንቋን መልመድን እንደጥቅም በማሰብ ሲማር ነው፡፡

ውጫዊ ተነሳሽነት ግን ተማሪው ቋንቋ ከመልመዱ በኋላ የሚያስገኘውን ሌላ ተጨማሪ ጥቅሞች በማሰብ ሲማር ነው:: በአንድ እንቅስቃሴ ላይ የሰዎችን ምርጫ፣ስሜት፣ጥረት የሚያሳይ በተለያዩ ግፊቶች የሚገኝና አንድ ነገር እንዲሰራ የሚያደርግ ባህሪ ነው፡፡

## 2.14.የተነሳሽነት አይነቶች

በሁለተኛ ቋንቋ ለመዳ ሂደት ውስጥ ከፍተኛ መቅስቀስ ያላቸው ተናጋሪዎች የተሻለ ይሰራሉ፡፡ እንዲሁም የመቀስቀስ (የተነሳሽነት) አይነቶች ተዋህዷዊ መቀስቀስና መሳሪያዊ መቀስቀስ ሲሆኑ ተዋህዷዊ መቀስቀስ ቋንቋውን ከሚናገሩ ማህበረሰቦች ጋር ለመግባባትና ከባህላቸውም ጋር ራስን ለማዋሀድ ወይም ተሳታፊ ለመሆን የሚመነጭ መነሳሳት ነው፡፡ መሳሪያዊው መነሳሳት ደግሞ የተለያዩ ጥቅማጥቅሞችን ለማግኘት ሲባል ቋንቋን የመልመድ ፍላጎት ወይም መነሳሳት ነው (ጌታቸው 2011)፡፡

እንደ Guthre and Wigfield (2000) በጥናታቸው እንዳመላከቱት ከተነሳሽነት አንዱ የንባብ ተነሳሽነት ሲሆን የማንበብ ተነሳሽነት ከርዕሱ፣ ከድርጊቱና ከማንበብ ውጤቶች ጋር የተዛመደ

አንድ የራስ አላማ፣ሀሳብና ፍላጎት ሲሆን ተማሪዎችን የሚያነቃቃ እጅግ ከፍተኛ ግፊት ነው፡፡ ተነሳሽነት እውቀትን ያጠናክራል፣ለመማር መነቃቃት ወይም መነሳሳት ዋናውና መሰረታዊ ነገር ሲሆን ሊደረስበት ከተፈለገው አላማ ለመድረስ ተግባራትን በተነሳሽነት እንዲፈጽሙ የሚረዳ ጥበባዊ ሂደት ነው፡፡

እንደ Guthre& Wigfield (1997) አገላለጽ ተነሳሽነት ሲባል ለማንበብ ማነሳሳት፣በማንበብ ውጤታማነትና የማንበብ ችሎታንለማግኘት ጥረት ማድረግ፣ ስለሚነበበው ሀሳብ የማንበብ ተነሳሽነት መኖር የማንበብ አላማ መኖር፣ የማንበብን ጠቀሜታ መገንዘብና በሚነበበው ርዕሰ ጉዳይ ላይ ትኩረት የመስጠትና በማንበብ ውጤታማ መሆን ማለት ነው፡፡

## 2.15. የቀደምት ጥናቶች ቅኝት

አጥኚዋ ይህን ጥናት ለማካሄድ የተለያዩ ቀደምት ጥናቶችን ለመዳሰስ የሞከረች ሲሆን ከነዚህም መካከል በረከት (2010) በአማርኛ ቋንቋ የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ፍጥነትተዛምዶ በሚለው ርዕስ ባቀረቡት ጥናታቸው ውጤት እንደሚያስረዱት የተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ በጣም ዝቅተኛ ደረጃ ላይ አንዳለ ባካሄዱት ጥናት ጠቁመዋል፡፡ መኮንን (2000) የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂል ችሎታ መፈተሽ በሚለው ርእስ ባካሄዱት ጥናታቸው ውጤት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ዝቅተኛ በሚባል ደረጃ ላይ እንደሆነ አመላክተዋል፡፡ ብርሀን(1989) የአንብቦ መረዳት ክሂል ችሎታ ተዛምዶ ጥናት በሚል ርዕስ ባካሄዱት ጥናት መረጃ መሰረት የተገኘው ውጤት እንደተገለፀው ተማሪዎች በአንብቦ መረዳት ክሂላቸው ችሎታ ላይ የጎላ ችግር እንደሚታይ የጥናቱ ውጤት ያመለክታል፡፡

ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች ከዚህ ጥናት የሚለዩት ይህ ጥናት ቡድናዊ መማር የኢ-አፍፈት ተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ መረዳትን በመጠናዊና አይነታዊ ንድፍ ሂደትን በመከተል የመረመረ ሲሆን የዑመር (2000) ጥናት ከዚህ ጥናት የሚለየው አይነታዊ የምርምር ንድፍን የተከተለ መሆኑና መረጃውንም በአይነታዊ ብቻ መተንተኑ፣ እንዲሁም መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች በቡድን ለሚከናወኑ ተግባራት ላይ በዝርዝር የማቀድ ሁኔታ የሌለ እና መምህራን የቡድን ተግባራትን ከመስጠት በዘለለ የቡድኑን አባላት ችሎታ፣ ተሳትፎ፣ተግባብቶ መስራት፣በቡድኑ ለክሰቱ የሚችሉ ችግሮችን የመከታተል ሁኔታ ፈጽሞ ትኩረት ያልተደረገበት መሆኑ ነው፡፡

በተጨማሪም አብዛኛዎቹ የቋንቋ መምህራን ቡድናዊ መማርን በተግባር ማከናወን ውጤታማ አይደለም የሚል አስተሳሰብ ወይም እይታ ያላቸው መሆኑ፣ በብዛት ዘዴውን ተጠቅመው የማስተማር እና የተማሪዎችን በቡድን እያነበቡ በነፃነት የንባብ ችሎታቸውን ለማሻሻል የሚያደርጉትን ጥረት ያላገናዘቡ ናቸው (Girma 2003)።

Behailu (2000) ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ምንም እንኳን የተማሪዎችን የሀገርኛ ቋንቋ መማር ተነሳሽነትን በመመርመሩ ተመሳሳይነት ቢኖረውም በአጥኚዋ ግምት የBehailu ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር የጎላ ልዩነት እንዲኖረው ያደረገው በስልጠና ያልታገዘ ጥናት በመሆኑ ነው። ምክንያቱም ተማሪዎች ለሀገርኛ ቋንቋ ለመማር ተነሳሽነትም ሆነ ለመማር ፍላጎት እንዲኖራቸው ያልታገዙ ሲሆን ይህ ጥናት ግን የማንበብ ተነሳሶትና አንብቦ የመረዳትን ችሎታን በስልጠና በመታገዝ የመረመረ በመሆኑ ልዩነት አለው። እንዲሁም ተማሪዎች ሀገርኛ ቋንቋ ለመማር ያላቸው አመለካከት እና ተነሳሽነት ተማሪዎች ለኦሮምኛም ሆነ አማርኛ ቋንቋ ትምህርት ዝቅተኛ ግምት እንደሚሰጡና ለውጪ እንግሊዘኛ ቋንቋ ከፍተኛ ግምት እንዳላቸው አመላክተዋል። የBehailu ጥናት ከዚህ ጥናት ጋር ምንም እንኳን የተማሪዎች ሀገርኛ ቋንቋ ተነሳሽነት ላይ መጠናቱ ተመሳሳነት ቢኖረውም በክፍል ደረጃ፣ ጥናቱ የተካሄደበት ቦታ፣ በአጠናን ዘዴው፣ የተለየ ነው። እመቤት (2011)አንብቦ የመረዳት እና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ አቀራረብ ትንተና በ7ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ተተኳሪነት። የእመቤት ጥናት በመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ምልከታና መጠይቅ ከዚህ ጥናት ጋር የሚመሳሰል ቢሆንም በመማሪያ መጽሀፉ ውስጥ ያለውን አንብቦ የመረዳትና የጽሀፊት ክሂልን አቀራረብ የሚገመግምና በአይነታዊ ንድፍ መረጃን የሰበሰበ ነው። የተገኘው ውጤትም ለተማሪዎች የሚዘጋጅ መማሪያ መጽሃፍ ሲዘጋጅ የይዘት ተገቢነት፣ የተማሪውን እውቀትና አከባቢ ያገናዘበ ቢሆን፣የማንበብና ጽህፈት ክሂል ተቀናጅተው ቢቀርቡ ተማሪዎች ይዘቱን በቀላሉ ለመረዳት ይችላሉ። እንዲሁም መምህራን ሁለቱን ክሂል አቀናጅተው ቢያቀርቡ ተማሪዎች በቀላሉ ክሂሎቶቹን ያጎለብታሉ የሚል በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር የሚለይ ነው።

የኔ ሰው (1990) ሞዴሎች ላይ በኦሮምኛ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማረኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳት ክሂላቸው ማዳበር ተራክቧአዊ የንባብ ማስተማሪያ ሞዴልን በክፍል ውስጥ ማስተማር ያለው አስተዋጽኦ በሚለው ጥናታቸው የተገኘው ውጤት የሚያመላክተው ሞዴሎችን ተጠቅሞ የቋንቋ ክሂሎትን ማስተማር ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው አመላክተዋል። የኔ ሰው ጥናት ከዚህ

ጥናት የሚለየው ሞዴልን ተጠቅሞ የማንበብ ክሂልን ማጎልበትን የመረመረ በመሆኑና መረጃውን አይነታዊ የምርምር ንድፍን የተከተለ በመሆኑ የተለየ ነው፡፡

ይህ ጥናት ከበረከት (2010) ፣መኮንን (2000)ና ብርሀን (1989) ጥናቶች የሚለየው የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ በአይነታዊ የምርምር ንድፍ መፈተሸና መረጃውንም በዚሁ ሰብስቦ መፈተሽ መቻሉና መምህራን የቡድናዊ መማርን ውጤታማነት በስልጠና በመታገዝና ስለ ቡድናዊ መማር ጠቀሜታ ይበልጥ ግንዛቤ ተሰቷቸው አለመተግበሩና ለተማሪዎች ተገቢ ክትትልና ድጋፍ ቢያደረጉ ሊመጣ የሚችለውን ለውጥ አለመመርመሩ ነው፡፡ የመምህራንን ቡድናዊ መማር አተገባበር እንጂ ቡድናዊ መማር ምንጠቀሜታ እንዳለው አልፈተሸም፡፡ እንዲሁም ለተማሪዎች ስለ ሀገርኛ ቋንቋ ጠቀሜታ በቂ ግንዛቤ በመምህራን አማካይነት አለመሰጠቱና ተማሪዎች እያንዳንዳቸው የየራሳቸውን ሚና ሊኖራቸው ይገባል የሚል እንጂ ከመካከላቸው በተሻለ የሚያነቡ ተማሪዎችን እንደሞዴል በመውሰድ ማስነበብ በማንበብ ደከም የሚሉ ተማሪዎችን ለመቀስቀስ ያለውን አስተዋጽኦ ያልመረመረ መሆኑ ነው፡፡

## 2.16 የኢ-አፍፊት ተማሪዎች የማነበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ችግሮች

የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ችግርና የማንበብ ተነሳሽነት ማጣት  መኖሩን ማረው (1998) እንደሚገልጹት ተማሪዎች ዳራዊ እውቀታቸውን ተጠቅመው አንድን ጽሁፍ አንብበው የመረዳት እንዲሁም ዝርዝርና አጠቃላይ ሀሳቦችን ከምንባቡ አንብበው የመለት ችግር ስላለባቸው የተለያዩ አንብቦ የመረዳት ስልቶችን በመታገዝ ማስተማር ትኩረት ሊሰጠው የሚገባ ጉዳይ ነው፡፡ በተማሪዎች የንባብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ላይ ተጽዕኖ ሊያመጡ የሚችሉ ጉዳዮች የመምህራን ትምህርት አሰጣጥ ሂደት፣የብለሃቶች አጠቃቀምና ከተማሪው ፍላጎት ጭምር ብዙ ችግሮች መኖራቸውን በተለያየ ጊዜያት የተካሄዱ ጥናቶችና ምሁራን ያመላክታሉ፡፡

ሰለሞን (1990) ለማስተማሪያነት በሚቀርቡ መርሃ ትምህርቶችና በነሱ መነሻነት በተዘጋጁ መማሪያ መፅሀፍት ውስጥ ከተጠቀሱት አላማዎች መካከል የተማሪዎችን ክሂል ማዳበር መቻል ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ ክሂሉን በተሻለ መንገድ ለማዳበር የተለያዩ የማስተማሪያ ስልቶችን በተግባር ላይ ባለመዋላቸው የተማሪዎቹን የአንባቦ መረዳት ክሂል ችሎታ ዝቅተኛ እንደሆነ

በአማርኛ ማስተማሪያዎችና በክፍል ውስጥ ትምህርት አቀራረብ ላይ የተደረጉ ጥናቶች እንደሚጠቁሙ ይገልፃል፡፡

ማስተዋል (1989) የከፍተኛ 2ኛ ደረጃ ተማሪዎች በአማርኛ አንብቦ መረዳት ችሎታ በአዲስ አበባ በሚገኙ በአራት ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ በተካሄደጥናት ርዕስ የተገኘው ውጤት መሰረት እንደተገለፀው ተማሪዎች የአንብቦ መረዳት ችሎታ በጣም ዝቅተኛ እንደሆነ ተስተውሏል፡፡

በአንጻሩ ሌሎች አጥኚዎች ደግሞ ባደረጉት ጥናት እንዳመላከቱት በላይነሽ (2010) የቃላትመማር ብለሀቶችን በግለጽ ማስተማር ለሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች የቃላት ችሎታ መዳበር በሚለው ሙከራዊ ጥናታቸው በብለሃት የሚማሩተማሪዎች በተለምዶ ያለብለሀት ከሚማሩ ተማሪዎች ይልቅ የቃላት ችሎታን ለማጎልበት የላቀ ድርሻ ያለው እንደሆነ በጥናታቸው ውጤት አመላክተዋል፡፡ ሆኖም ጥናቱ ከዚህ ጥናት ጋር የሚለየው በቃላት ብለሃቶች ላይ መካሄዱ ሲሆን በሁለተኛ ቋንቋ ተማሪዎች ላይ መካሄዱ ተመሳሳይነት አለው፡፡

Boruvkova፣Emanovsky (2016) ቡድናዊ መማር ስልት በተማሪዎች ማህበራዊ ግንኙነት ላይ ያለው አዎንታዊ ጠቀሜታ በሚል ጥናት አካሂደዋል፡፡ የጥናታቸው ውጤት ቡድናዊ መማር ስልት ተማሪዎችን በክፍል ወስጥ ወደ አንድነት ለማምጣት አዎንታዊ ጠቀሜታ አለው የሚል ነው፡፡እንዲሁም በክፍል ውስጥ ራሳቸውን አግልለው ያሉ ተማሪዎች ከሌሎች ጋር በቡድን በማቀናጀት አብሮነት እንዲፈጥሩ ለማድረግ ይጠቅማል በማለት በጥናታቸው ውጤት አረጋግጠዋል፡፡ ጥናቱ ምንም እንኳን ከዚህ ጥናት ጋር በተማሪዎች ማኃበራዊ ግንኙነት ላይና በተገኘው ውጤት ተማሪዎችን ወደ አንድነት ማምጣቱ ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ቢኖረውም ይህ ጥናት ግን ቡድናዊ መማር ስልት አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነትንለማጎልበት ያለውን አስተዋጽኦ መመርመሩ በአጠናን ሂደቱ የተለየ ነው፡፡

Springre፣Stanne፣Donovan (1999) በቡድን መማር በከፍተኛ ተቋማት ትምህርት ለሚማሩ የተፈጥሮ ሳይነስ ተማሪዎች ላይ በሚል የጥናት ርዕስ ጥናት አካሂደዋል፡፡ መርምረው የገኙት ውጤትም ቡድዊ መማር ለሳይነስ ተማሪዎች አስፈላጊ እንደሆነና አዎንታዊ ጠቀሜታም ያለው መሆኑ ነው፡፡

## 2.17. የጥናቱ ንድፈ ሃሳባዊ ማሕቀፍ

ለዚህ ጥናት ተገቢ በሆነ ሁኔታማስተካከያ ተደርጎበት የተወሰደው ጽንሰ ሀሳባዊ ማእቀፍየSlavin (2011)ን ስራ እንደ መነሻ በማድረግ ነው፡፡ሞዴሉቡድናዊ አላማን መሰረት ያደረገ መማር፣መኃበራዊ ግንኙነት፣የመጣው ለውጥ የሚሉትን የያዘ ሲሆን ቡድናዊ ስልጠናን፣የመምህር ተግባርን፣የተማሪን ተግባር፣ቡድናዊ መማር ክትትልን፣ለቡድናዊ መማር እርምት መስጠትን በውስጡ የያዘ አይደለም፡፡ ሆኖም ሞዴሉ ለዚህ ጥናት እንደ መነሻ ይሆናል ብላ አጥኚዋ አምናለች፡፡ቀጥሎ ይህ ጽንሰ ሀሳባዊ ማእቀፍ በምስል ቀርቧል፡፡




ምስል 2.የጥናቱ ንድፈ ሀሳባዊ ማሕቀፍ (ምንጭ:-ከSlavin 2011) ተሻሽሎ የተወሰደ፡፡

ከላይ የቀረበው ምስል ስዕላዊ መግለጫ የሚያመላክተው የዚህን ጥናት ጽንሰ ሀሳባዊ ማእቀፍ ሲሆን የያዛቸው ሀሳቦች ቡድናዊ መማር መሰረት ያደረገ ስልጠና፣ቡድናዊ መማርን አላማ መሰረት ያደረገ መማር፣መኀበራዊ ግንኙነት፣የመምህሩ ተግባር፣የተማሪ ተግባርና ከቡድናዊ መማር በኋላ የመጣው ለውጥ የክህሎት መጎልበትወይም መሻሻል ጋር ያለውን ግንኙነት የሚያመላክት ነው፡፡

ሞዴሉ በጥቅሉ ትኩረት ያደረገባቸው የቡድናዊ መማር መነሻ ዋና ነገሮች ቡድንን መሰረት ያደረገ ስልጠና መስጠት፣የመምህሩ ተግባር፣የተማሪዎች ተግባር፣ከቡድናዊ መማር በኋላ የመጣው ለውጥ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መጎልበትና ለማንበብ ተነሳሽነትን መፍጠር ናቸው፡፡ ሞዴሉ በዝርዝር ያካተታቸው ነጥቦች ደግሞ ለመምህሩ ቡድናዊ ስልጠና መስጠት ሲሆን ቡድናዊ አላማን መሰረት ያደረገ መማርን ለመተግበር በቡድናዊ ግንኙነት መምህሩ ቡድናዊ

መማርን በማነሳሳት በክፍል ውስጥ ሞዴል የሆኑ ተማሪዎች እንደ ማሳያ በመውሰድ አንዱ ከሌላው ጋር ግንኙነት በማድረግ ርስበርሳቸው እንዲረዳዱ ማድረግ፣ቡድናዊ መማርን ማገዝና መከታተል እንዲሁም እርምት መስጠት ናቸው፡፡

ተማሪዎችም እየተረዳዱ ማንበብና መነሳሳት፣የምንባቡን ሀሳብ መገንዘብ፣ በቂ ግንዛቤ ማግኘት ናቸው፡፡ በመጨረሻም የመጣው ለውጥ የሚያሳየው ዝቅጠኛ የማንበብ ችሎታ ያላቸው ተማሪዎች በቡድናዊ መማርና ልምምድ በመታገዛቸው ምክንያት አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን መጎልበትና ለማንበብ መነሳሳት መቻላቸውን የሚያሳይ ነው፡፡

# ምዕራፍ ሶስት

# የጥናቱን ንድፍና የአጠናን ዘዴ

## 3.1.የጥናቱ ንድፍ

የጥናቱ ትኩረት በ2015ዓ.ም.9ኛ ክፍል በመማር ላይ የሚገኙ ኢ-አፍፊት ወይም አማርኛ ቋንቋ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎች ቡድናዊ መማር ስልት አንብቦ መረዳትን ለማጎልበትና ለማንበብ ተነሳሽነትን ለመፍጠር ያለውን ጠቀሜታ መፈተሽ ነው፡፡ እንደ ያለው (2009፣39) እምነት የምርምር ንድፍ የሚባለው ምርምሩ ይዞት የሚነሳውን ጥያቄ ለመመለስ ወይም መላ ለመምታት የሚያስችልን መረጃ ለመሰብሰብ፣ ምን ያህል ቡድኖች በምን አይነት መንገድ በጥናቱ ውስጥ መሳተፍ እንዳለባቸው፣ መረጃው እንዴት መሰብሰብና በምን መልክ መተንተን እንዳለበት ለመወሰን የሚያስችል የምርምሩን አካሄድ ስረዓትና እቅድ የሚወስን መሆኑን አመላክቷል፡፡ በጥናቱ የተካተቱት በመጀመሪያው ፈረቃ የተመደቡ 9ኛሀናለ ክፍል ኢ-አፍፊት ተማሪዎች ላይ ሲሆን ጥናቱ ሌላ ክፍልን(የክፍል ደረጃን) አይመለከትም፡፡

እንደ አለም (1997፣162) የአንድ ጥናት ዘዴ ማለት በአጠቃላይ የጥናቱ የአሰራር ስልትን የሚመለከት ሲሆን በጥናቱ ውስጥ አገልግሎት ላይ የዋሉ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎችንና የመረጃ መተንተኛ መንገዶችን በዋናነት በውስጡ መያዙን ተጠቃሽ እንደሆነ አስገንዝበዋል፡፡ ይህ ጥናትም ተግባራዊ የሚሆንበት የአጠናን ዘዴ ከፊል ፍትነታዊና አይነታዊ የምርምር ንድፍ ዓይነቶች ናቸው፡፡ ጥናቱ እነዚህን የምርምር አይነቶች የሚከተልበት ምክንያት በሁለት ቡድኖች ላይ የሚያተኩርና ተማሪዎቹን በተመደቡበት ክፍል እንዳሉ በመውሰድ የመረመረ ስለሆነ ነው፡፡ እንዲሁም መረጃዎቹም በመጠናዊና በተወሰነ ደረጃ በአይነታዊ የሚሰበሰቡና በዚያው መንገድ የሚተነተኑት በመሆኑ ምክንያት እነዚህን ዘዴዎች የሚከተል ነው፡፡

## 3.2.የናሙና አመራረጥ

### 3.2.1.ጥናቱ የሚካሄድበት ወረዳ አመራረጥ

ይህ ጥናት በኦሮሚያ ክልል አርሲ ዞን ስር በሚገኘው በዶዶታ ወረዳ በዴራ ከተማ ተካሂዷል፡፡ አጥኚዋ በዚህ ወረዳ ጥናቷን ያካሄደች ሲሆን ይህን ወረዳ የመረጠችበት ምክንያት በዚህ ወረዳ

በማስተማር ላይ የምትገኝ በመሆኗ ለጥናቷተገቢ መረጃን ለማግኘት አመቺ ሆኖ ስለተገኘ በዞኑ ከሚገኙ ሌሎች ወረዳዎች መካከል ይህን ወረዳ በአመቺ ናሙና አመራረጥ ዘዴ መርጣለች፡፡

### 3.2.2. የትምህርት ቤት ናሙና አመራረጥ

በዶዶታ ወረዳ ውስጥ 28 አንደኛ ደረጃናሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚገኙ ሲሆን በከተማውዴራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤትና በአከባቢዋ ደግሞ አሙዴ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በአጠቃላይ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች አሉ፡፡ አጥኚዋ ጥናቷን በወረዳው ከሚገኙ ሁለት ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች መካከል በዴራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ያካሄደች ሲሆን ይህን ትምህርት ቤት በአመቺ ናሙና አመራረጥ ዘዴ መርጣለች፡፡ ትምህርት ቤቱ የተመረጠበት ዋና ምክንያት አንደኛ በዚህ ትምህርት ቤት ለብዙ ጊዜ በ9ኛ ክፍል ደረጃ ያሉ ተማሪዎችን ታስተምር በነበረበት ጊዜ ኢ-አፍፌት ተማሪዎች በክፍል ደረጃቸው ተዘጋጅቶ የቀረበላቸውን የማንበብ ትምህርት ይዘት አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት አለመኖር ችግር መኖሩን መታዘቧ እንዲሁም የቡድናዊ መማር ክፍተት መኖሩን በመታዘቧ ነው፡፡

### 3.2.3. የክፍል ደረጃ ና የተጠኚ ተማሪዎች ናሙና አመራረጥ

ለጥናቱየተመረጡት በዴራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ትምህርታቸውን በመማር ላይ የሚገኙ 9ኛ ክፍል ኢ-አፍ ፌት ተማሪዎች ናቸው፡፡ትምህርት ቤቱ ለስረዓተ ትምህርት ማረጋገጫ የተመረጠ በመሆኑ ተማሪዎቹን እንደየ አፍመፍቻ ቋንቋቸው መድቧቸው በማስተማር ላይ የሚገኝ ሲሆን ይህ ጥናትም የሚካሄደው አማርኛ ቋንቋ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ 9ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ ብቻ ነው፡፡

በትምህርት ቤቱ በ2015 ዓ.ም ትምህርታቸው በመከታተል ላይ የሚገኙ 9ኛ ክፍል በአጠቃላይ 16 ምድብ ኢ-አፍፌትና 4 ምድብ አፍ-ፌት በድምሩ 20 ምድብ 9ኛክፍል ተማሪዎች ናቸው፡፡ ጥናቱን ለማካሄድ ከኢ-አፍፌት ተማሪዎች መካከል በመጀመሪያ ፈረቃ በአንድ መምህር ከሚማሩ 12 ምድብ ተማሪዎች መካከል 9ኛሀና ለን በቀላል የእጣ ናሙና ተመርጠዋል፡፡ በ9ኛሀ ምድብ 42 ተማሪዎች ተመድበው ሲገኙ 23 ሴቶችና 19ወንዶች በክፍሉ በመማር ላይ ያሉ ሲሆን በ9ኛ ለ ምድብም42 ተማሪዎች 20 ሴቶች እና 22 ወንዶች ይገኙበታል፡፡ እነዚህ ተማሪዎች በጥናቱ የሚካተቱ ሆነው ጥናቱ ከፊል ሙከራዊ እንደመሆኑ መጠን የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኖቹ ተቀራራቢ የሆነቅድመ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት በማስመዝገባቸው

ምክንያት እኩል እድል በመስጠት በቀላል እጣ ናሙና  ምድብ ሀ የሙከራ ቡድን ተደርጎ ሲመረጥ ምድብ ለ ደግሞ የቁጥጥር ቡድን ተደርጎ ተለይተዋል፡፡

### 3.2.5.የመምህራን አመራረጥ

በዴራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት አማርኛ ቋንቋ ትምህርትን ከ9-12 ክፍል በማስተማር ላይ የሚገኙ መምህራን ብዛት ሁለት ሴት እና ሶስት ወንድ በድምሩ አምስት ናቸው፡፡ ካሉት መምህራን ለዚህ ጥናት ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎችን ለማስተማር ትምህረት ቤቱ መድቦት ያለ አንድ መምህር በስራ ልምድና በማስተማር ብቃት ለጥናቱ ተመራጧል፡፡ ጥናቱ ከፊል ሙከራዊ እንደመሆኑ መጠን ሁለት ቡድኖች አሉት፡፡መምህሩ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖችን ለማስተማር የተመረጠበት ምክንያት አጥኚዋ ጥናቷን ለማካሄድ መምህሩ በዚያው ክፍል ደረጃ በማስተማር ላይ የሚገኝና ተገቢውንእገዛ ለማድረግ በቂ ችሎታና ልምድ አለው የሚል እምነት ስላላት ነው፡፡ ይህን ሀሳብ Seid(2012)Jacobs and Sorensen (2010)ን በመጥቀስለጥናት የሚመረጡ ቡድኖች በአንድ መምህር መማራቸው የጥናቱ ተገቢነትና አስተማማኝነት ለመቆጣጠር እገዛ ያደርጋል፡፡

ወደ ልምምዱ ከመግባቱ በፊት ጥናቱ ሁለት ቡድኖች ላይ ስለሚያተኩር ሁለት ክፍል ቡድኖች በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርጓል፡፡ አጥኚዋ ጥናቱን ለማካሄድ ለመረጠችውና በዚያ ክፍል ደረጃ በመደበኛነት አማርኛ ቋንቋ ትምህርትን እንዲያስተምር ለተመደበው መምህር በአማርኛ ቋንቋ ክፍለ ትምህርት ውስጥ መምህሩ በሚያመቸው ከትምህረት ነጻ በሚሆንበት ክፍለ ጊዜን በመጠቀም ለአንድ ሳምንት በቀን  ለአንድ ሰዓት ስልጠና ሰታለች፡፡ ስልጠናው የቡድን አመሰራረትን፣የቡድናዊ ማስተማር ዘዴዎችን፣ቡድናዊመማር ስልት መመሪያዎችን፣የመምህርና ተማሪዎችን ሚና፣ቡድናዊ መማር ጠቀሜታና ሌሎችም ጉዳዮችን በተመለከተ የምሁራንን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ለመምህሩ ግንዛቤ የሚሰጡ ናቸው፡፡

ቀጥሎም ለሁለቱም ቡድኖች እኩል እድል በመስጠት በቀላል እጣ ናሙና አመራረጥ ስልት ከተለየ በኂላ የሙከራ ቡድኑን በቡድናዊ መማር ዘዴ የቁጥጥር ቡድኑን ደግሞ ያለ ዘዴው ወይም ቡድን ሳይመሰርት በተናጥል እንዲያስተምር ተደርጓል፡፡

## 3.3.የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች

የጥናቱን ዓላማ ከግብ ለማድረስና ተገቢውን መረጃ ለመሰብሰብ ሲባል በአገልግሎት ላይ የዋሉት የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አንብቦ የመረዳት ፈተና፣የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ፣ቡድን ተኮር ውይይትና ምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ናቸው፡፡

### 3.3.1. አንብቦ የመረዳት ፈተና

ይህ ጥናት በዋናነት ለመረጃ መሰብሰቢያነት የተጠቀመው አንብቦ የመረዳት ፈተና ነው፡፡ ጥያቄዎቹ ሲዘጋጁ ወጥነት ባለው መንገድ የተፈታኞችን አእምሯዊ ችሎታ፣ስነ ባህሪያዊ ሁኔታ አስመልክቶ መረጃ ለመሰብሰብ የሚረዳ መለኪያ እንደሆነ ያለው (2009፣189)ያስረዳሉ፡፡ አክለውም ፈተናዎች በጥንቃቄ ተቀናጅተው አስፈላጊውን መረጃ ለመሰብሰብ ጉልህ ስፍራ ይዘው እንደሚገኙ ያስገነዝባሉ፡፡ እንዲሁም Brown(2010፣725)ፈተና በቡድን ተከፋፍሎ የመማር ሂደትን መገምገሚያ መንገድ ነው፡፡

#### 3.3.1.1.ለጥናቱ የክፍል ውሰጥ ልምምድና ፈተና ምንባቦችና ጥያቄዎች አመራረጥ

ለጥናቱ የክፍል ውስጥ ልምምድና ፈተና የተመረጡት ምንባቦች ከ9ኛ ክፍልአዲሱ መማሪያ መጽሐፍ ሲሆን ምንባቦቹና ጥያቄዎቹ ከመጽሀፉ የተመረጡበት ምክንያ ትለክፍል ደረጃው መረሀ ትምህርትን መሰረት በማድረግ የመስኩ ባለሞያዎች ያዘጋጇቸው መሆናቸውን በመገንዘብ ነው፡፡ ለቅድመና ድህረ ፈተና ከምንባቡ የወጡ ጥያቄዎች የተዘጋጁት የመስኩ ባለሙያዎች ያሰጡትን ሀሳብ መነሻ በማድረግ ነው፡፡ ለጥናቱ የተመረጡት ምንባቦች ከተማሪዎቹ መጽሀፍት በመውሰድና ለፈተና በሚያመች መንገድ ማሻሻያዎችን በማድረግ ነው፡፡ ምንባቦቹና ጥያቄዎቹ የምንባቡን ጽንሰ ሀሳብ ሳይለቁ ባጭሩ በማስቀመጥ፣ የምንባቡን ጽንሰ ሃሳባዊ አረዳድ እውነት ወይም ሀሰት በል፣ የቃላት አገባባዊ ፈቺ፣ ምርጫ፣ ክፍት ቦታ ሙሉ የሚሉትን የሚያካትቱ ቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ተዘጋጅተዋል፡፡ አባሪ ‹ሐ›ን ይመልከቱ፡፡

ሆኖም በቅድመ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተናና የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅን ተዘጋጀተው አስተማማኝነታቸው በጥናቱ በማይካተቱ ተማሪዎች እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ በማስከተልም መረጃውን በመመዝገብ ተጣርቷል፡፡ መረጃው ከተረጋገጠ በኋላ ቡድናዊ መማርን መሰረት ያደረገ ስልጠና ለመምህሩ ተሰቷል፡፡ አባሪ (ሰ)ን ይመልከቱ፡፡

ለቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና በምዕራፍ ዘጠኝና አስር ላይ የሚገኙ ተማሪዎቹ ያልተማሯቸው ነገር ግን ወደፊት የሚማሯቸው ናቸው፡፡ ለክፍል ውስጥ ልምምድ የሚሆኑ

ምንባቦችና መልመጃዎች ደግሞ በምዕራፍ ስድስት፣ሰባትና ስምንት ላይ የሚገኙ ናቸው። አባሪ (ቀ)ን ይመልከቱ። አጥኚዋ እነዚህን በተማሪዎቹ መጽሀፍ ላይ ያሉትን ምንባቦች የመረጠችበት ምክንያት ተማሪዎቹ በተመደቡበት መደበኛ ክፍላቸው የሚማሩ መሆናቸውናለጥናት የበለጠ አስተማማኝነው የሚል እምነት ስላላት ነው:: ጥናቱን ለማካሄድም የትምህርት ዕቅድ በማዘጋጀትና ከመምህሩ ጋር በመወያየት ልምምዱ እንዲቀጥል ተደርጓል። አባሪ (ሸ)ን ይመልከቱ።

### 3.3.1.2.የቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና አዘገጃጀት

አስቀድሞ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተናዎች የGrellet (1981)& Nuttal (1996) የሚከተሉትን አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች አቀራረብ ያውም አንብቦ የመረዳት ጥያቄየምንባብ ይዘት፣ዓለማ፣አይነትና አደረጃጀትን መሰረት በማድረግ ነው። ጥያቄዎቹ የተዘጋጁት የመስኩ ባለሙያዎች ያሰጡትን ሀሳብ መነሻ በማድረግነው። ለጥናቱ የተመረጡት ምንባቦች ከተማሪዎቹ መጽሀፍት ውስጥ በመውሰድ ተዘጋጅተው ለተማሪዎቹ ቀርበዋል። ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተናም ከቅድመ አንብቦ የመረዳት ፈተና ጥያቄዎች ጋር ተመሳሳይ ይዘትና አጠያየቅ ያለውና የተለየ ርዕሰ ጉዳይኖሮት ተጠኚ ተማሪዎች በድህረ ልምምድ እንዲሞሉ ተዘጋጅቷል። አባሪ ‹ሐ›ን ይመልከቱ።

### 3.3.1.3.የቅድመና ድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ተገቢነትና አስተማማኝነት

ፈተናተዘጋጅቶ ለተጠኚ ቡድኑ ከመቅረቡ በፊት ተገቢነቱን እና አስተማማኝነቱን ማወቅ አስፈላጊ ነው (አለም1997)። ፅንኡነት (validity) እንዲለካ የታለመለትን ጉዳይ መለካት የቻለ መለኪያ ሲሆን አስተማማኝነት (Reliability) በመለኪያነቱ የሚጠቀስ መሳሪያ ነው። አስተማማኝነት ያለው ሁኔታ ከአንዱ ወደ ሌላ አይለያይም፣አይዋዥቅም።

አጥኚዋ ለጥናቱ የተዘጋጁትን ምንባቦችና በስሩ የሚካተቱ ጥያቄዎችን ተገቢነት ለማረጋገጥ ለክፍሉ ደረጃ ሁለት መምህራን ያስገመገመች ሲሆን የክፍሉ ደረጃው መምህራን አንደኛው 25 ዓመት የስራ ልምድና ሁለተኛ ድግሪ ያለው ነው። ሁለተኛው መምህር ደግሞ 32 አመት የስራ ልምድና አንደኛ ድግሪ ያለው ነው። መምህራኑ ለጥናቱ የወጡ ቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎቹን ገምግመዋል።ባደረጉት ግምገማም ጥያቄዎቹ የዐረፍተ ነገር እርዝማኔ፣የጥያቄ ቁጥር 3ና11 ድግግሞሽ ወይም ተመሳሳይነት የሚታይባቸው መሆኑ፣ጥያቄ 24 ና 25 ከክብደት አንጻር

እንዲወገዱ አስተያየት የሰጡ ሲሆን ጥያቄዎቹ ታይተው ማስተካከያ የሚፈልጉ ማስተካከያ ተደርጎባቸውና ሁለቱ ጥያቄዎችም ከፈተናው ተወግደው ቀሪዎቹ ጥያቄዎች ለፈተና ቀርበዋል፡፡ ሁለቱም ፈተና በአጠቃላይ ሃያ ሃያ የጥያቄ ብዛት የያዙ ሆነው በኣጥኚዋ የተዘጋጅ ሲሆን አንብቦ የመረዳት ፈተናዎቹም አንዱ ለቅድመ ሌለኛው ደግሞ ለድህረ ፈተና እንዲቀርቡ ተደርጓል፡፡

ቅድመ አንብቦ የመረዳት ፈተናው ለተጠኚ ተማሪዎቹ ከመቅረቡ በፊት አስተማማኝነቱን ለማረጋገጥ በጥናቱ ለማይካተቱና የክፍል ደረጃቸው ተመሳሳይ ለሆኑና ይህንኑ መጽሀፍ ለሚማሩ በሁለተኛው ፈረቃባሉ ሌሎች 40 ተማሪዎች ተሰቷል፡፡ ፈተናውን ተማሪዎቹ ከተፈተኑናከታረመ በኋላ ውጤቱ ተመዝግቦ የፈተና አስተማማኝነት መገመቻ ዘዴ በሆነው በእኩል ክፋይ ዘዴ(split half method) የስፒርማን-ብራውን የትንበያ ፎርሙላ (Spearman-Brown prophecy Formula)ን የሂሳብ ስልት ተግባራዊ ሆኗል፡፡

የቅድመ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤትም (.754) ሆኖ በመገኘቱ አስተማማኝነት ያለው መሆኑ ተረጋግጧል፡፡ በስሌቱ የተገኘው የፈተናው ውጤትም ከ0.7 በላይ በመሆኑ ፈተናው አስተማ ማኝነት እንዳለው ታውቋል፡፡ አባሪ ‹ሀ›ን ይመልከቱ፡፡

የክፍል ልምምዱ ከተጠናቀቀ በኋላ የድህረ አንብቦ የመዳት ፈተና አስተማማኝነትን ለማረጋገጥ ከቅድመአንብቦ የመረዳት ፈተናጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና ተዘጋጅቶ በጥናቱ በማይካተቱና የክፍል ደረጃቸው ተመሳሳይ ለሆኑ በዚያው መማሪያ መጽሃፍ ለሚማሩ ተማሪዎች በድጋሜ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ፈተናው ከታረመ በኋላ የፈተናውን አስተማማኝነት ለማወቅ በፈተና አስተማማኝነት መገመቻ ዘዴ እኩል ክፋይ ዘዴ (split half method) የስፒማን-ብራውን የትንበያ ፎርሙላ (Spearman-Brownprophecy Formula)ን የሂሳብ ስልት ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ የድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተናው አስተማማኝነት በእኩል ክፋይ ዘዴ የሂሳብ ስሌት ተሰልቶ (0.71)በመሆኑ አስቀድሞ ለመግለጽ እንደተሞከረው ከ 0.7በላይ በመሆኑ አስተማማኝነቱ ተረጋግጧል፡፡ አባሪ ‹ቸ›ን ይመልከቱ፡፡

### 3.3.1.4.ቅድመ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና

ቅድመ አንብቦ የመረዳት ፈተና ተሰልቶ አስተማማኝነቱ ከተረጋገጠ በኋላ በጥናቱ ለተካተቱ ቁጥጥርና ሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ቅድመ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ዋነኛ አላማው ጥናቱ ከመካሄዱ በፊት ተማሪዎቹ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ምን እንደሚመስል ወይም በምን ደረጃ ላይ እንደሚገኝ

ለመገንዘብ ነው።እንዲሁም በሁለቱ ቡድኖች መካከል ምን አይነት አንብቦ የመረዳት ችሎታ እንዳለ ለይቶ ለማወቅ ወይም እርግጠኛ ለመሆን ነው። አባሪ ‹ሠ›ን ይመልከቱ።

አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤቱ ያለበትን ደረጃ ታውቋል። አባሪ (ኘ)ን ይመልከቱ። ውጤቱ ከታወቀ በኋላ ለሁለቱም ቡድን እኩል እድል በመስጠት በቀላል እጣ ናሙና ዘዴ በመጠቀም 9ኛ ሀ የሙከራ ቡድን 9ኛለ ደግሞ የቁጥጥጥር ቡድን ሆነው ተለይተዋል። አስቀድሞ ለመጠቆም እንደተ ሞከረው ተማሪዎቹ በየቋንቋቸው ተከፋፍለው የሚማሩ በመሆኑ ሁለቱም ቡድኖች በመደበኛነት ተመድበው በሚማሩበት ክፍል መደበኛ ትምህርቱ ሳይናጋ በየክፍላቸው የክፍል ልምምዱን እንዲቀጥሉ ተደርጓል።

### 3.3.1.5. ድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና

ተማሪዎቹ በሁለት ተከፍለው ለስድስት ሳምንታት ያህል (25/ 07/ 2015 _4/ 09/ 2015)የክፍል ልምምዱ ሲጠናቀቅ ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና በአጥኚዋ ድጋሚ ተዘጋጅቶ ለሌሎች በጥናቱ የማይካተቱ ተመሳሳይ የክፍል ደረጃና ይህንኑ መጽሀፍ በሚማሩ ተማሪዎች ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና እንዲፈቱ ተደርጓል። ፈተናው ተጣርቶ ከታረሙና ውጤታቸው ከተመዘገበ በኋላ ከላይ ለማሳየት እንደተሞከረው አስተማማኝነታቸው ተረጋግጧል። አባሪ (ቸ)ን ይመልከቱ። በማስከተልም ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተናው ለቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ አንብቦ የመረዳት ፈተናውን እንዲፈተኑ ተደርጓል። አባሪ ‹ኦ› ፣ ‹ወ›ን፣(ዐ)ን ይመልከቱ።

### 3.3.2. የማንበብ ተነሳሽነት የጹሁፍ መጠይቅ

ለዚህ ጥናት መረጃ መሰብሰቢያነት ያገለገለው የማንበብ ተነሳሽነት የጽሁፍ አንዱ ነው። የመጠይቁ አላማስለ ቡድናዊ መማር ለመምህሩ ስልጠና ከመሰጠቱ በፊትና ለመምህሩ ስልጠና ተሰቶ የመማር ማስተማር ሂደቱ በስልጠናው መሰረት ተግባራዊ ከተደረገ በኋላ በተማሪዎች ላይ የመጣውን ለውጥ ለማወቅ ነው።

ያለው(2009) የጽሁፍ መጠይቅ ጥያቄዎች አዘገጃጀትን በተመለከተ መረጃ ለመሰብሰብ የጹሁፍ መጠይቅ ጥያቄዎች ሲዘጋጁ አጥኚዎች ከተጠኚዎቹ ልምድ ወይም ነባራዊ ሁኔታ በመነሳት ከምርምሩ ችግር ርዕሰ ጉዳይ፣መሪ ጥያቄና ዓላማ ጋር የሚዛመዱ ጥያቄዎችን ማዘጋጀት እንደሚችል አመላክተዋል።

አጥኚዋ ይህንኑ ሀሳብ መሰረት በማድረግ ከተማሪዎቹ መረጃ ለመሰብሰብ ከርዕሱ አላማና ከተማሪዎች ነባራዊ ሁኔታ ከታዘበቸው ሀሳብ ጋርየሚዛመዱ የማንበብ ተነሳሽነት የጽሁፍ

መጠይቅ አዘጋጅታለች፡፡ መጠይቆቹም አራት አማራጮች ያላቸው ሲሆኑ እነዚህም በጣም እስማማለሁ፣እስማማለሁ፣አልስማማምና ፈጽሞ አልስማማም የሚሉ አማራጮችና ተመሳሳይ ይዘት ያሏቸውን 20 መጠይቆች የሙከራ ቡድኑ በቅድመና ድህረ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡ የሙከራ ቡድኑ መጠይቆቹን ከሞሉ በኋላ ተገቢውን ማጣራት ተደርጎ በቅደም ተከተል ተተንትነው ቀርበዋል፡፡ ለቅድመ መጠይቅ የተዘጋጀውን አባሪ ‹መ› እና ለድህረ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ ደግሞ አባሪ ‹ነ›ን ይመልከቱ፡፡

### 3.3.2.1. ቅድመና ድህረ የማንበብ ተነሳሽነት የጽሁፍ መጠይቁ ተገቢነትና አስተማማኝነት

የመጠይቆቹ ተገቢነትን በተመለከተ የደረጃው መምህራን እንዲገመግሙ ተደርጎመጠይቆቹ ብዛት ስላላቸው በተጠኚዎቹ ከተሞሉ በኋላ ለጥናቱ በቂ ምላሽ ሊሰጡ የሚችሉትን  መጠይቆች ብቻተመርጠው ለትንተና መቅረብ እንዳለባቸው በደረጃው መምህራንና አማካሪ አስተያየት ተሰቷል፡፡ ይህንኑ ሀሳብም በመቀበል ተግባራዊ ተደርጓል፡፡ መጠይቆቹ ለሙከራ ቡድኑ ከመቅረባቸው በፊት በተመሳሳይ የክፍል ደረጃ የሆኑ20ተማሪዎች ለመጠይቁ ምላሽ እንዲሰጡ ተደርጓል፡፡ መጠይቁም በተማሪዎቹ ተሞልቶ ውጤቱ ከተመዘገበ በኋላ የመጠይቁን አስተማማኝነትም ለማረጋገጥ በክሮንበኽ አልፋ ስሌት ተሰልቷል፡፡ የተገኘው ውጤትም (.74)ሆኖ በመገኘቱና ውጤቱ ከ0.7 በላይ በመሆኑ አስተማማኝነቱ ተቀባይነት አግኝቷል፡፡ አባሪ ‹ረ› ይመልከቱ፡፡ የመጠይቁ አስተማማኝነት ከተረጋገጠ በኋላ በጥናቱ ለተካተቱ የሙከራ ቡድኑ ቅድመ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ የሙከራ ቡድኑ በመጠይቁ የሰጡት ምላሽም ተመዝግቦ ተቀምጧል፡፡ አባሪ ‹ረ›ን ይመልከቱ፡፡

የቅድመ መጠይቆቹ ውጤቱ ከታወቀ በኋላ መምህሩ የክፍል ልምምድ ቀጥሏል፡፡ አጥኚዋ የክፍል ልምምዱ ከተጠናቀቀ በኋላ በቅድመ የማንበብ መጠይቁ ጋር ተመሳሳይ ይዘት ያላቸውን ድህረ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቆች በማዘጋጀት የሙከራ ተማሪዎቹ ከመሙላታቸው በፊት ተመሳሳይ የክፍል ደረጃ ባላቸው ተማሪዎች በድጋሜ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ መጠይቁም ታርሞ ውጤት ከተመዘገበ በኋላ አስተማማኝነቱን ለማረጋገጥ በክሮንባኽ አልፋ ስሌት ተሰልቶ(.71) አስተማማኝነቱ ተረጋግጧል፡፡ አባሪ ‹ኃ› ይመልከቱ፡፡

በማስከተልም አንብቦ የመረዳት ፈተናን የቁጥጥርና ሙከራ ቡድኑ እንዲሞሉ ከተደረገ ቀጣይ ቀናትየሙከራ ቡድኑ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ እንዲሞሉት ተደርጓል፡፡ የተገኘው ምላሽም ተመዝግቦ ተተንትኗል፡፡ አባሪ ‹ከ›ን ይመልከቱ፡፡

### 3.3.3. ቡድን ተኮር ውይይት

ለዚህ ጥናት እንደ አጋዥ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ያገለገለው ቡድን ተኮር ውይይት ሲሆን ዘዴው ጥልቅና ዝርዝር መረጃ ለማግኘት የሚረዳ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ እንደሆነና ለምርምሩ የውሳኔ ሃሳብ ለማፍለቅ ያግዛል ያለው(2009)፡፡ አክለውም ተማሪዎች በቡድን ተኮር ውይይቱ ጊዜ በነጻነት ሀሳባቸውን እንዲገልጹ እድል በመስጠት፣ የመወያያ ጥያቄውን ግልጽ በማድረግ፣ በቡድኑ መካከል ልዩነት የሚታይ ከሆነ በመቆጣጠርና ስልታዊ በሆን መንገድ ለማስተካከል በመሞከር፣ የቡድኑ አባላት በሙሉ እየተወያዩ ሀሳብ እንዲሰጡ በማድረግና የተስማሙበትን ሀሳብ በቃል እዲናገሩ ወይም ሀሳብ እንዲያቀረቡ ማድረግ ተገቢ ነው፡፡

በመሆኑም የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በቡድናዊ መማር ዘዴ ከተማሩ በኋላ ዘዴው የማንበብ ተነሳሽነትንና አንብቦ የመረዳት ችሎታን ማሻሻልና አለማሻሻሉን ለማረጋገጥ ነው፡፡ አባሪ (ዘ) ይመልከቱ፡፡ አጥኚዋ የድህረ ልምምዱ ከተጠናቀቀ በኋላ የሙከራ ቡድኑን የውሳኔ ሀሳብ ለማወቅ የሚያስችሉ ለቡድን ተኮር ውይይት የሚሆኑ ጥያቄችን በማዘጋጀት በቡድናዊ መማር ስልት ከተማሩት የሙከራ ቡድን ተማሪዎች የተወሰኑትን በማሳተፍ ቡድን ተኮር ውይይት በማድረግ መረጃ ሰብስባለች፡፡ አባሪ ‹ኸ›ን ይመልከቱ፡፡

### 3.3.4. ምልከታ

በዚህ ጥናት መረጃን ለመሰብሰብ ካገለገሉ ዘዴዎች አንዱ ምልከታ ነው፡፡ አጥኚዋ ይህንን የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ስልት መጠቀም የፈለገችበት ምክንያት የጥናቷ ርዕስ እንደሚያመላክተው ቡድናዊ መማር በክፍል ውስጥ በሚተገበርበት ጊዜ መምህሩ የተሰጠውን ስልጠና ምን ያህል ተግባራዊ እንዳደረገ ለጥናቷ አስተማማኝነት ሲባል መከታተል አስፈላጊ ነው ብላ ስላመነች ነው፡፡ ያለው(2009) የክፍል ውስጥ ምልከታን በተመለከተ በድግግሞሽ የተካሄዱ ክንውኖችን ብዛት ቅጽ አዘጋጅቶ ለስንት ጊዜያት እንደተከናወነ መመዝገብ እንደሚቻል አስገንዝበዋል፡፡ በመሆኑም አጥኚዋክትትሉን ለማካሄድ የክፍል ውስጥ ክንውን መገምገሚያ የሆኑትን የትምህርት አላማን ማሳወቅ፣አላማን ማስገንዘብ፣ተማሪዎችን በቡድን ማስቀመጥ፣መርሆችን ማስገንዘብ፣ምንባቦችን ማቅረብና ማስነበብ፣ተማሪዎች ርስ በርስ መተጋገዛቸውን መከታተል፣አንብበው መረዳታቸውን መገምገም የሚሉ የመገምገሚያ ቅጾችን አዘጋጅታለች፡፡ አባሪ (በ)ን ይመልከቱ፡፡ ማዘጋጀት መምህሩ ሲያስተምር ምልከታ በማድረግ መተግበር አለመተግበሩን በዝርዝር ሀሳቦቹ መሰረት በቅደም ተከተል ተመልክታለች፡፡ አባሪ ‹ዠ›ን ይመልከቱ፡፡

## 3.4.የመረጃ አተና ተንዘዴ

ይህ ጥናት በዋናነት ይዞት የተነሳው አላማ ቡድናዊ መማር ዘዴ ለ9ኛ ክፍል ኢ-አፍፊትተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ክሂል ችሎታ ለማጎልበት ያለውን ጠቀሜታ መፈተሽ የሚል ነው፡፡ ለጥናቱ የመረጃ መሰብሰቢያነት ተግባራዊ የሆኑት አንብቦ የመረዳትፈተና፣የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ፣ቡድንተኮር ውይይት፣ምልከታ ናቸው፡፡ በነዚህ የመረጃመሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በመጠናዊና በዓይነታዊ የተሰበሰቡት ሲሆንመረጃዎች በየ ምድባቸው እንዲደራጁተደርጓል፡፡ ለጥናቱአንብቦ የመረዳት ፈተና መረጃዎች በSPSS.V20 (version.20) ስሌት የተተነተኑ ሲሆን የማንበብ ተነሳሽነት የጹሁፍ መጠይቆች በፐርሰንት ስሌት ተቀምጧል፣ ቡድን ተኮር ውይይት ደግሞ በገለጻናምልከታ በተዘጋጀው ቅጽ መሰረት ተሞልቷል፡፡ በነዚህ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የተሰበሰቡት መረጃዎች በመጠናዊና በዓይነታዊ ተለይተው ተተንትነዋል፡፡

### 3.4.1.አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት አተናተን

የሙከራና ቁጥጥር ቡድኖቹ በቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ያስመዘገቡት መረጃዎች አማካይ ውጤት በገላጭ ስታትስቲክስ የተተነተኑ ሲሆን አማካይ ውጤትን በገላጭ ስታትስቲክስ ብቻ መተንተን በቂ ባለመሆኑና አማካይ ውጤት ምን ያህል የጉልህነት ደረጃ እንዳለው ለማረጋገጥ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት መፈተሽ ተገቢ ነው (ያለው 2009)፡፡

በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ አንብቦ የመረዳት ፈተናና ሙከራ ቡድኑ ቅድመ አንብቦ የመረዳት ፈተና መካከል ያለውን የአማካይ ውጤት ተቀራራቢነት ፣በሙከራና ቁጥጥር ቡድኑ መካከል ያለውን ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት ልዩነት፣በቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና ሙከራ ቡድኑና ቁጥጥሩ ቡድኑ መካከል ያለውን አመካይ ውጤት በገላጭ ስታትስቲክስ ስሌት ተሰልቷል፡፡ በድጋሜ ሙከራና ቁጥጥር ቡድኑ ቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤትና የጉልህነት ደረጀ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተፈትሿል፡፡

### 3.4.2.የማንበብ ተነሳሶት መጠይቅ መረጃ አተናተን

ይህ መጠይቅ ከጥናቱ ርዕሰ ጉዳይ ጋር ተያያዥነት ያላቸውና ከተማሪዎቹ ነባራዊ የማንበብ ተነሳሶት ጋር በማያያዝ በጽሁፍ መልክ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መጠይቆቹን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ተጠኚዎች ከሰጡት ምላሽ ለጥናቱ ይበልጥ ጠቃሚ የሆኑትንና በቂ መረጃ ሊሰጡ

ይችላሉ  ብላ አጥኚዋ ያመነችባቸውን መጠይቆች ካሉት መጠይቆች በመውሰድ በፐርሰንት ስሌት (መቶኛ) ተሰልተው ተቀምጠዋል፡፡

### 3.4.3.ከምልከታ የተገኙ መረጃዎች አተናተን

ምልከታ አስቀድሞ ለመግለጽ እንደተሞከረው መምህሩ በክፍል ውስጥ ቡድናዊ መማርን ተግባራዊ ሲያደርግ በተሰጠው ስልጠና መሰረት የቁጥጥር ቡድኑን በተለመዷዊና የሙከራ ቡድኑን በቡድናዊ መማር ስልት ማስተማሩን ለማረጋገጥ የሚደረግ ምልከታ ነው፡፡ ሆኖም መምህሩ የሙከራና ቁጥጥር ቡድኖቹን ተማሪዎች በክፍል ሲያለማምድ የተገበራቸውንና ያልተገበራቸውን ዝርዝር ነጥቦች ለመለየት በክፍል ውስጥ በተከታታይ ምልከታ ተደርጓል፡፡ መረጃ ለመሰብሰብ በተዘጋጁት ዝርዝር  ነጥቦችመሰረትበሙከራና ቁጥጥር ቡድኑ መካከል ያለውን የማስተማር ሂደት ልዩነትተመዝግቧል፡፡ የሁለቱን ቡድኖች ልዩነትም በምልከታ ከተገኘው መረጃበመነሳትበተዘጋጀውቅጽ መሰረት የተሞላው ነጥብበሰንጠረዥ  ተደምረው ተቀምጠዋል፡፡

### 3.4.4.ከቡድን ተኮር ውይይት የተገኙት መረጃዎች አተናተን

ቡድን ተኮር ውይይት ለመረጃ መሰብሰቢያነት መጠቀም የተፈለገበት ምክንያት ሙከራ ቡድኑ በቡድናዊ መማር ስልት የማንበብና አንብቦ የመረዳት ትምህርት ይዘትን መማራቸው ያበረከተውን አስተዋጽኦ ከተማሪዎቹ መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ሆኖም ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው በቡድናዊ መማር ከተማሩት ተማሪዎች ውስጥ ጥቂት ተማሪዎች ተወስደው የሰጡት ሀሳብ በገለጻ መልክ ተብራርተው ቀርበዋል፡፡

## 3.5. የጥናቱ አተገባበር ቅደምተከተላዊ ሂደት

ይህ ጥናት ዋና አላማው ቡድናዊ መማር የኢ-አፍ ፈት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የማንበብ ተነሳሶት ለማጎልበት ያለው ጠቀሜታ መፈተሽ የሚል ነው፡፡ አጥኚዋ ይህን ጥናት ለማካሄድ አስቀድማ በዚህ ርዕሰ  ላይ ጥናት እንድታደርግ የሚያሳየውን ደብዳቤ በመያዝ ለትምህርት ቤቱ ርዕሰ መምህር፣ መምህር.፣ ተማሪዎችና  አስተዳደር ሰራተኞች ለጥናቷ አካሄድ ያመቻት ዘንድ በጥናቷ እገዛ ለሚያደርጉላት አካላት የትብብር ጥያቄ አቅርባለች፡፡ ጥያቄው የቀረበላቸው አካልም ጥናቱ በሚካሄድበት ትምህርት ቤት የሚገኙ ርዕሰ መምህራን፣ የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ ተማሪዎች  ለጥናቱ ለሚየደርጉት እገዛ ፍቃደኛ መሆናቸውን አረጋግጣለች፡፡

በማስከተልም  አጥኚዋ የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች የሆኑትን አንብቦ የመረዳት፣ የጹሁፍ መጠይቅ፣ ቡድን ተኮር ውይይትና የምልከታ ቅጽ አዘጋጅታለች፡፡ ትምህርት ቤቱ ለስረዓተ ትምህርት ማረጋገጫ እንደ ዞኑ የተመረጠ ብቸኛ ትምህረት ቤት በመሆኑ ለስረዓተ ትምህረቱ በተዘጋጀ መማሪያ መጽሀፍ ለማስተማር የተመረጠ ሌላ ትምህርት ቤት እንደ ዞኑ አልተገኘም፡፡ በመሆኑም አጥኚዋ ጥናቱን ለማካሄድ የመረጠችው  ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም በስረዓተ ትምህርቱ አፈጻጸም መሰረት 16 ምድብ ኢ- አፍ ፊት ተማሪዎችንና 4 ምድብ አፍ-ፊት 9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ለየብቻ መድቦና ሁለት ቦታ በመክፈል በተለያየ ፈረቃ ለይቶ በማስተማር ላይ ይገኛል፡፡

ሆኖም አጥኚዋ ለጥናቷ ትክክለኛነትና አስተማማኝነትም አንብቦ የመረዳት ፈተናና የጹሁፍ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ ለጥናቱ ከተመረጡ ተማሪዎች ተመሳሳይ የክፍል ደረጃና በዚያው የስረዓተ ትምህርት ማረጋገጫ የተዘጋጀውን መማሪያ መጽሀፍ ነው፡፡ ጥናቱ ከሚካሄድበት ፈረቃ ተቃራኒ በሚማሩና ፍቃደኛነታቸውን ለገለጹ 40 ተማሪዎች በመምህራኖች እገዛ አንብቦ የመረዳት ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ በቀጣዩቹ ጊዜያትም20 ተማሪዎችን በመውሰድ ቅድመ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቁን ሞልተዋል፡፡ ፈተናው ከታረመና ውጤቱ ከተመዘገበ  በኂላ አንብቦ የመረዳት ፈተናና የማንበብ ተነሳሽነት መጥይቆቹ አስተማማኝነት ተረጋግጧል፡፡

ቀጥሎም  በፈተናው ለተካተቱት ተማሪዎች ቅድመ  አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተናና የማንበብ ተነሳሽነት የጹሁፍ መጠይቅ በተለያዩ ጊዜያት እንዲሞሉ በማድረግና በደረጃው መምህር ታርሟል፡፡ ውጤቱ ተተንትኖ ከተለየ በኂላ  ለሁለቱም ቡድን እኩል እድል በመስጠት በቀላል እጣ ናሙና አመራረጥ 9ኛሀ የሙከራ ቡድን 9ኛ ለ የቁጥጥር ቡድን ተደርጎ በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርገዋል፡፡

በማስከተልም ለጥናቱ ለተመረጠው መምህር በአጥኚዋ ስልጠና ተሰቷል፡፡ ስልጠናው የተሰጠው በምዕራፍ ሁለት ላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የተለያዩ ምሁራን ቡድናዊ መማርን አስመልክቶ የገለጽትን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ያውም Dennic፣ Exley (1998)ና Graffam (2018)፣ Burke (2011) እንዲሁም ሌሎች ምሁራን የሰጡትን ሀሳብ መሰረት በማድረግ የትምህርት ሰዓት በማይነካ መልኩ ለአንድ ሳምንት በቀን ለአንድ ሰዓት በተከታታይ ቀናት ለመምህሩ ስልጠና ሰታለች፡፡

ቅድመ ፈተናዎች ከተሰጡ በኂላ በክለሳ ድርሳኑ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ቀጣዩ ተግባር መምህሩ የክፍል ውስጥ ልምምድን ከመጀመሩ በፊት መምህሩ የተሰጠውን ስልጠና መሰረት

በማድረግ የBJHM 2009፣ Jaquos 2006ን የቡድን አመሰራራትን እንደ መነሻበ ማድረግ ሙከራ ቡድኑንቡድን የመመስረት ተግባር ተከናውኗል፡፡ ተማሪዎቹ ቡድን እንዲመሰርቱ ከተደረገ በኋላመምህሩ ትምህርቱን እንዲቀጥል ስምምነት ላይ ተደርሷል፡፡
መምህሩ ለተማሪዎቹ የሚያስተምረው የክፍል ደረጃ ይመጥናል ተብሎ በባለሙያዎች ተዘጋጅተው በ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ከቀረቡት የትምህርት ይዘቶች መካከል በምዕራፍ ስድስት፣ሰባትና ስምንት ላይ የተሰጡትን ምንባቦችና መልመጃዎች ሲሆን በምዕራፍ ዘጠኝና አስር የቀረቡት ምንባቦች ለቅድመና ድህረ ፈተና ተገቢው መሻሻል ተደርጎባቸው ቀርበዋል፡፡
ከምዕራፍ ስድስት ጀምሮ ለሁለቱም ቡድኖች በተሰጠው ስልጠና መሰረት ለቡድናዊ መማር ትምህረት የትምህርት ዕቅድ መዘጋጀት እንዳለበት Johnson and Johnson (1999) የተለያዩ ምሁራንን ጠቅሰው የሰጡትን የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት መሰረት በማድረግ የትምህረት ዕቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ ተማሪዎቹ በመደበኛ ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት መደበኛ መማሪያ ክፍል በ25/07/2015 እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ አቀማመጣቸውን በተመለከተ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ስድስት ስድስት አልፎ አልፎ አምስት ተማሪዎችን እንደተገለጸው በማቧደንና በቡድናዊ አቀማመጥ በማስቀመጥ በቡድናዊ መማር ፣የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ በተለምዷዊው ያለ ቡድን ትምህርታቸውን እንዲጀምሩ ተደርጓል፡፡
አጥኚዋም መምህሩ በተሰጠው ስልጠና መሰረት የቁጥጥር ቡድኑን በተለምዷዊው መማር፣ የሙከራ ቡድኑን ደግሞ በቡድናዊ መማር በክፍል ውስጥ ልምምዱን ማከናወን አለማከናወኑን በተከታታይ በሁለቱም ቡድኖች ላይ ምልከታ አድርጋለች፡፡ መምህሩም የክፍል ውስጥ ልምምዱን በመደበኛው ክፍል ሰጥቷል፡፡ በመደበኛው ክፍል እንዲሰጥ የተደረገበት ምክንያት ትምህርት ቤቱ ለስራዓተ ትምህርት ማረጋገጫ የተመረጠ በመሆኑ ተማሪዎቹን በየአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መድቦ በማስተማር ላይ የሚገኝ ስለሆነ መደበኛ ትምህረቱን የሚያናጋ ባለመሆኑ ምክንያት ነው፡፡
የክፍል ውስጥ ልምምዱ በተከታታይ እስከ 4/09/2015 ዓ.ም ለስድስት ሳምንታት በሳምንት ሁለት ሁለት ክፍለ ጊዜ በየምዕራፉ የቀረቡትን ምንባቦችና መልመጃዎች በአጠቃላይ ለ12 ክፍለ ጊዜ በተከታታይ የክፍል ውስጥ ልምምዱ ተከናውኗል፡፡ በክፍል ልምምዱ ሂደትም አጥኚዋ በሁለቱም ቡድኖች ክፍል በመዘዋወር መምህሩ ሲያስተምር ተገቢውን ምልከታ አድርጋለች፡፡
የክፍል ልምምዱ ከተጠናቀቀ በኋላ ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተናና የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ ተገቢነትናአስተማማኝነት ለማረጋገጥ በደረጃው መምህራን ከተገመገመና አስፈላጊው

ማስተካካያ ከተደረገ በኂላ ቀድሞ የፈተናው አስተማማኝነት በተሰጠበት ክፍል ፈተናውን እንዲፈተኑና መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡

የአንብቦ መረዳቱና መጠይቁ አስተማማኝነት ከተረጋገጠ በኂላ አንብቦ የመረዳት ፈተናውን የሙከራና ቁጥጥር ቡድኖቹ በተከታታይ ፍቃደኛ በሆኑ መምህራን አማካይነት ተሰቷል፡፡ ቀጥሎም የሙከራ ቡድኑ የተነሳሽነት መጠይቁን ሞልተዋል፡፡ በቀጣይ ጊዜያትም ከ 42 ሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል አምስት ተማሪዎችን በመውሰድ ድህረ ልምምድ ቡድን ተኮር ውይይት ከአጥኚዋ ጋር ተካሂዷል፡፡

በጥናቱ አላማ ላይ የተነሱትን ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት ለጥናቱ በተመረጡት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካይኝነት የተሰበሰቡትን መረጃዎች ተመዝግበው ተገቢው ማጣራት ከተደረገ በኂላ የተገኘው ውጤት በቅደም ተከተል ተተንትኖ ቀርቧል፡፡

## 3.6.ከጥናቱ የተገኙ ተሞክሮዎች

ጥናቱ በሚካሄድበት ጊዜ ከጥናቱ ሂደት የተገኙ ተሞክሮዎች መካከል የመጀመሪያውየማንበብ ተነሳሽነትን አስተማማኝነት ለማረጋገጥ የተዘጋጀው የጽሁፍ መጠይቅ ብዛት ያለው መሆኑና ለሙከራ ቡድኑ በቅድመና ድህረ መጠይቅ ሲቀርብ ተማሪዎች እንዲሞሉ ከተደረገ በኂላ ለጥናቱ ይበልጥ ምላሽ ሊያስገኙ የሚችሉትን ተራ ቁጥሮች ተመርጠው ለትንተና መቅረብ እንዳለበት ግንዛቤ ተገኝቷል፡፡ሁለተኛ በቅድመልምምድ አንብቦ የመረዳት አስተማማኝነት ፈተና በተወሰደው ልምድ ለፈተናው በተሰጠው ሰዓት ባለመጠናቀቁ ምክንያት የተወሰነ ሰዓት ጭማሬ መደረግ እንዳለበት ግንዛቤ ተገኝቷል፡፡

# ምዕራፍአራት

## የጥናቱ መረጃ ትንተናና ውጤት ማብራሪያ

በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች ከሆኑት አንብቦ የመረዳት ፈተና፣ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ፣ቡድን ተኮር ውይይትና ምልከታ አማካይነት ከተጠኚዎች የተሰበሰቡትን ውጤቶችና መረጃዎች የውጤት መተንተኛ ዘዴዎችን በመጠቀም በቅደም ተከተል ተተንትነው በዝርዝር ቀርበዋል፡፡

### 4.1 የጥናቱ መረጃ ትንተና

#### 4.1.1.አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት ትንተና

1. ቡድናዊ መማር ለኢ- አፍ ፈት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጎልበት ያለው አስተዋጽኦ ምንድነው?

የሚለው በዚህ ጥናት አላማ የቀረበ ዋና ጥያቄ ሲሆን ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት ከቅድመ ልምምድ አስቀድሞና በኋላ በጥናቱ ለተካተቱት ተጠኚዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለውጥ መምጣቱንና አለመምጣቱን ለማረጋገጥ አንብቦ የመረዳት ፈተናዋና የመረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያ ሆኖ ቀርቧል፡፡ ፈተናዎቹ የGrellet (1981)& Nuttal (1996) የሚከተሉትን አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች አቀራረብን መሰረት በማድረግ ሲሆን ያውም አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎቹ የምንባቡን ይዘት፣ዓለማ፣አይነትና አደረጃጀትን መሰረት በማድረግ ተዘጋጅተው የቁጥጥርና ሙከራ ቡድኑ ፈተናውን እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ ለፈተናዎቹም ተገቢው ማጣራት ተደርጎ የተገኘው ውጤትም በገላጭ ስታስቲክስናበጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት በቅደም ተከተል ተሰልቶ ቀርቧል፡፡

ሰንጠረዥ1.የቁጥጥርና ሙከራ ቡድኖች ቅድመ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ

| ፈተና | ቡድን | አማካይ ውጤት (Mean) | መደበኛ ልይይት (Std Deviation) | ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| ቅድመ | ቁጥጥር | 12.95 | 2.49 | 42 |
| | ሙከራ | 13.16 | 2.30 | 42 |

ሰንጠረዥ1.የቁጥጥርና ሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በቅድመ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ያስመዘገቡትን አማካይ ውጤትና መደበኛ ልይይት የሚያሳይ ነው፡፡ በሰንጠረዡ ላይ ከቀረበው ስታትስቲክስአዊ ስሌት መገንዘብ የሚቻለው የቁጥጥር ቡድኑ አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤት 12.95 መደበኛ ልይይት 2.49 የቁጥጥር ቡድኑ አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤት ደግሞ 13.16 መደበኛ ልይይት 2.30 ነው፡፡ ይህ መረጃ የሚያመላክተው በቁጥጥር ቡድኑና ሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት መካከል ያለው አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤት ተቀራራቢነት ያለው መሆኑን ነው፡፡ የመደበኛ ልይይቱም ውጤት ሲታይ ተቀራራቢነት መኖሩን ያመላክታል፡፡

በገላጭ ስታስቲክስ ለማሳየት የተሞከረው አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤት ምንም እንኳንተቀራራቢነት ያለው መሆኑን የሚያመላክት ቢሆንም አማካይ ውጤታቸውን በመመልከት ብቻ የጎላ ልዩነት በመካከላቸው መኖሩን ማረጋገጥ አይቻልም፡፡ ስለዚህ ጉልህ የሆነ ልዩነት ወይም ተቀራራቢነት መኖር አለመኖሩን የበለጠ ለማረጋገጥ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ፍተሻ ስሌት ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡

ሰንጠረዥ2. የቁጥጥር ቡድኑና ሙከራ ቡድኑ ቅድመ አንብቦ የመረዳት ችሎታፈተና የአማካይ ውጤት የጉልህነት ደረጃ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት

| ፈተና | ቡድን | ብዛት | አማካይውጤት (M) | መደበኛልይይት(S.D) | የአማካይልዩነት(M.D) | 95% የስህተት ይሁንታመጠን CI of Difference | | የቲ ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነትደረጃSiG(2-tailed) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ | | | |
| ቅድመ | ቁጥጥር | 42 | 12.95 | 2.49 | -.214 | -1.14 | .713 | -.46 | 41 | .643 |
| | ሙከራ | 42 | 13.16 | 2.30 | | | | | | |

T>0.05

በሰንጠረዥ2. እንደሚያሳየው የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመ ልምምድ የአንብቦ መረዳት አማካይ ውጤት 12.95 መደበኛ ልይይት 2.49 የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት 13.16 መደበኛ ልይይት ሲሆን የሁለቱ ቡድኖች የአማካይ ውጤት ተቀራራቢ መሆኑ ከላይ ለማሳየት

እንደተሞከረው በገላጭ ስታትስቲክስ ተሰልቶ ተረጋጧል። ሆኖም በገላጭ ስታትስቲክስ ብቻ በማስላት ማረጋገጥ ስለማይቻል በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተሰልቶ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው የአማካይ ውጤት ልዩነት ሲታይ .214 ሆኖ በመገኘቱ በመካከላቸው ብዙ ልዩነት እንደሌለና ተቀራራቢነት ያለው መሆኑን አሳይቷል። የቡድኖቹ የጉልህነት ደረጃ የፒ ዋጋ .643 ከመቁረጫ ነጥብ (0.05) በልጦ በመገኘቱ በቡድኖቹ መካከል ጉልህ የሆነ ቅድመ አንብቦ የአንብቦ መረዳት ችሎታ እንደሌለ አመላክቷል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው በሁለቱ ቡድኖች ቅድመ አንብቦ የመረዳት ችሎታ የአማካይ ውጤት ተቀራራቢነት ያለው መሆንና የጉልህነት ደረጃው.643 ከመቁረጫ ነጥብ ከ0.05 በልጦ መገኘቱ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ጉልህ የሆን ልዩነት አለመኖሩን ማረጋገጥ ተችሏል።

በገላጭ ስታትስቲክስ ቅድመ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና የተገኘውየሙከራ ቡድኑና የቁጥጥር ቡድኑ አማካይ ውጤት ተቀራራቢነት ያለው መሆኑና የጉልህነት ደረጃው ከተሰላ በኋላ ቀጥሎ በድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና ወደ ማስላት ተገብቷል። የክፍል ክንውኑ የቁጥጥር ቡድኑ ያለ ቡድናዊ መማር ዘዴ፣የሙከራ ቡድኑ ደግሞ በዘዴው እንዲማሩ ከተደረገ በኋላ ልምምዱ ሲጠናቀቅ ሁለቱም ቡድኖች አስተማማኝነቱ በእኩል ክፋይ ዘዴ የተረጋገጠ ድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና እንዲወስዱ ተደርጓል። የቁጥጥር ቡድኑና የሙከራ ቡድኑ የተገኘው ድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤትና የጉልህነት ደረጃም በቅደም ተከተል ቀጥሎ በሰንጠረዥ ቀርቧል።

ሰንጠረዥ3. የቁጥጥርና ሙከራ ቡድኖቹ ድህረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት ንጽጽር በገላጭ ስታትስቲክስ

| ፈተና | ቡድን | አማካይውጤት (M) | መደበኛ ልይይ (SD) | ብዛት |
|---|---|---|---|---|
| ድህረ | ቁጥጥር | 13.23 | 2.36 | 42 |
| | ሙከራ | 17.07 | 1.56 | 42 |

ሰንጠረዥ3. የቁጥጥር ቡድኑና ሙከራ ቡድኑ ተጠኚዎች በድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ያገኙትን አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤት ምን እንደሚመስል የሚያሳይ ነው። ከላይ በቀረበው ሰንጠረዥ የተመዘገበው ውጤት የቁጥጥር ቡድኑ በገላጭ ስታትስቲክስ ስሌት

ያስመዘገበው አማካይ ውጤት 13.23 መደበኛ ልይይት 2.36 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ ያስመዘገበው ደግሞ 17. 07 መደበኛ ልይይት 1.56 ነው፡፡የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኖቹ በድህረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ካስመዘገቡት አማካይ ውጤት መረዳት የሚቻለው በሁለቱ ቡድኖች መካከል በድህር አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና ልዩነት መኖሩን ነው፡፡ ያውም የሙከራ ቡድኑ ያስመዘገበው ድህረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ወጤት በልጦ መገኘቱን አመላክቷል፡፡ ከተመዘገበው ውጤት መገንዘብ የሚቻለው ሁለቱ ቡድኖች በድህረ ልምምድ የአንብቦ መረዳት ችሎታ ፈተና መካከል ልዩነት መኖሩን የሚያሳይ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ቡድኖቹ በድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና አማካይ ውጤጥ በገላጭ ስታትስቲክስ ብቻ ተሰልቶ ልዩነት መኖሩ የተመላከተ ቢሆንም የጉልህነት ደረጃው ምን ያህል እንደሆነ ለማረጋገጥ ከላይ ለመጠቆም እንደተሞከረው የአማካይ ውጤት ልዩነቱን የጉልህነት ደረጃ ለማረጋገጥ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ማፈተሽ ተገቢ ነው፡፡

ሰንጠረዥ4. የቁጥጥርና ሙከራ ቡድኑ ድህረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት የጉልህነት ደረጃ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት

| ፈተና | ቡድን | ብዛት | አማካይ ውጤት(M) | መደበኛልይይት(S.D) | የአማካይልዩነት(MD) | 5%የስህተትይሁንታ መጠን CL0f Difference | | የቲ ዋጋ(t) | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነት ደረጃ (P)(Sig(2-talled) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ | | | |
| ድህረ | ቁጥጥር | 42 | 13.23 | 2.36 | -3.84 | -4.71 | -2.95 | -8.78 | 41 | .000 |
| | ሙከራ | 42 | 17.07 | 1.56 | | | | | | |

ፒ < 0.05

ከሰንጠረዥ4. የምንረዳው የቁጥጥርና ሙከራ ቡድኖቹ የድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤት የጉልህነት ደረጃ ምን እንደሆነ የሚያሳይ ነው፡፡ በጥነድ ናሙና ቲ,ቴስት ተፈትሾ የተገኘው የሙከራ ቡድኑ አማካይ ውጤት17፣07 መደበኛ ልይይት 1.56 የቁጥጥር ቡድኑ 13.23 መደበኛ ልይይት 2.36 ሲሆን የሙከራ ቡድኑ አንብቦ የመረዳት አማካይ ውጤት

ከቁጥጥር ቡድኑ በ3.84 በልጦ ተገኝቷል። የቲ ዋጋ -8.78፣የነጻነት ደረጃ 41፣ፒ 0.05 ባለሁለት ጫፍ ሲሆን የጉልህነት ደረጃው(.000) ከመቁረጫ ነጥቡ አንሶ በመገኘቱ በቁጥጥርና ሙከራ ቡድኑ መካከል ጉልህ ልዩነት መኖሩን አመላክቷል።

በሰንጠረዡ የተመዘገበው ውጤት የሚያሳየው በቡድኖቹ መካከል ጉልህ የሆነ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ልዩነት መኖሩን ነው። በመሆኑም ከዚህ የሙከራ ቡድኑ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት ከቁጥጥር ቡድኑ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት ጉልህ ልዩነት መረዳት የምንችለው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በቡድናዊ መማር ስልት የአንብቦ መረዳት ትምህርት ይዘትን እየተወያዩና በተሻለ ከሚያነቡ ተማሪዎች ጋር ርስ በርሳቸው በመተጋገዝ ልምምድ ማድረጋቸው ሁሉም ተማሪዎች የበለጠ ግንዛቤ እያገኙ መምጣታቸውንና በተማሪዎቹ ላይ ለውጥ መኖሩን የሚያሳይ ነው።

አስቀድሞ ለማየት የተሞከረው የቁጥጥርና ሙከራ ቡድኖቹን ቅድመና ድህረ  አንብቦ የመረዳት ችሎታ አማካይውጤትና የጉልህነት ደረጃ ሲሆን ከዚህ በማስከተል ደግሞ የየቡድኑ ቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት የጉልህነት ደረጃ ቡድኑ በቅድመውና ድህረ ፈተናው ምን እንደሚመስል (መስመራዊ በሆነ መልኩ)  በጥነድ ናሙና ቲ-ቴስት ተፈትሾ በቅደም ተከተል ይቀርባል።

ሰንጠረዥ5. የሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና የአማካይ ውጤት የጉልህነት ደረጃ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት

| | ፈተና | ብዛት | አማካይ ውጤት | መደበኛ ልይይት | የአማካይ ልዩነት | 95 የስህተት ይሁኝታመጠን CL0f Difference | | የቲ ዋጋ | የነጻነት ደረጃ | የጉልህነትደረጃ (P) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዝቅተኛ | ከተኛ | | | |
| ሙከራ | ቅድመ | 42 | 13.16 | 2.30 | -3.91 | -4.75 | -3.05 | -9.26 | 41 | .000 |
| | ድህረ | 42 | 17.07 | 1.56 | | | | | | |

ፒ < 0.05

ሰንጠረዥ5. የሙከራ ቡድኑ በቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ፈተና አማካይ ውጤት መካከል ያለውን  የጉልህነት ደረጃ ልዩነት በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ስሌት የሚያሳይ ነው። ቡድኑ በቅድመ ፈተና አማካይ ውጤት 13.16 መደበኛ ልይይት 2.30፣በድህረ 17.07 መደበኛ

ልይይት 1.56 ሲሆን የድህረ ፈተናው አማካይ ውጤት  ከቅድመ ፈተናው ውጤት በ 3.91 በልጫ አሳይቶ ተገኝቷል። ከዚህ መገንዘብ የሚቻለው በሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ መካከል ልዩነት መኖሩን ነው።በስታትስቲክስ ስሌትም ስንመለከት የቲ ዋጋ -9.2፣የነጻነት ደረጃ ፒ <0.05 ባለሁለት ጫፍ ነው።የተገኘው የጉልህነት ደረጃም .000 ከመቁረጫ ነጥቡ አንሶ ተገኝቷል።

በመሆኑም ሙከራ ቡድኑ በበቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ውጤት አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት መኖሩን የሚያመላክት ነው። ይህ የአማካይ ውጤት ጉልህ  ልዩነት የሚያመላክተው የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በቡድናዊ መማር ስልት በመማራቸው ሲሆን ከዚህ የምንገነዘበው ቡድናዊ መማር ለአንብቦ መረዳት ከፍተኛ አስተዋጽኦ እንዳለው ነው። በአንፃሩ የቁጥጥር ቡድኑ በቡድናዊ መማር ዘዴ ባለመማሩ በአንብቦ መረዳት አማካይ ውጤት መካከል ጉልህ የአማካይ ውጤት ልዩነት እንደሌለ በስታትስቲክስ ተሰልቶ ተረጋግጧል።

ሰንጠረዥ6. የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት የጉልህነት ደረጃ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስሰት

| ቡድን | ፈተና | ብዛት | አማካይውጤት(M) | መደበኛ ልይይ(S.D) | የአማካይ ልዩነት(MD) | 95%የስህተት ይሁንታCIof Difference | | የቲ ዋጋ (t) | የነጻነት ደረጃ (df) | ጉልህነትደረጃ(P) (Sig-2taild) |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | | | | | ዝቅተኛ | ከፍተኛ | | | |
| ቁጥ ጥር | ቅድመ | 42 | 12.95 | 2.49 | -.28 | -1.38 | .67 | -.699 | 41 | .489 |
| | ድህረ | 42 | 13.23 | 2.43 | | | | | | |

ፒ > 0.05

ከሰንጥዝ6. እንደ ምንገነዘበው የቁጥጥር ቡድኑ በቅድመ ልምምድና ድህረ ልምምድ  አንብቦ የመረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት መካከል ያለውን ልዩነት የሚያሳይ ነው። በመሆኑም በቅድመ ፈተና ውጤት ቡድኑ ያስመዘገበው አማካይ ውጤት 12.95፣መደበኛ ልይይት 2.49 ሲሆን በድህረ አንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት ደግሞ 13.23 መደበኛ ልይይት 2.43 ነው።

ከዚህ የምንገነዘበው በቁጥጥር ቡድኑ ድህረ ፈተናና ቅድመ ፈተናው መካከል .28 ልዩነት ብቻ ወይም የተወሰነ ለውጥ ብቻ ያለው ሲሆን የጉልህነት ደረጃው ምን ያህል እንደሆነ ለመገንዘብ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስትም ሲፈተሽ የቲ ዋጋ .69፣የነጻነት ደረጃ 41፣ የጉልህነት ደረጃው .489 ነው።የፒ ዋጋ ከመቁረጫ ነጥቡ 0.05 በላይ በመሆኑ ቡድኑ በቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ውጤት መካከል ጉልህ የሆነ ልዩነት አለመኖሩን አመላክቷል፡፡

ስለዚህ በቡድናዊ መማር ስልት ያልተማሩት የቁጥጥር ቡድን ተማሪዎች በቅድመና ድህረ አንብቦ በመረዳት ችሎታ ልዩነት ያልመጣው በተለምዷዊ መማራቸው ሲሆን የሙከራ ቡድኑ በቅድመና ድህረ አንብቦ መረዳት ችሎታ አማካይ ውጤት ልዩነት ያመጡት በቡድናዊ መማር ስለተማሩ ነው የሚል ድምዳሜ ላይ ያደርሳል፡፡

### 4.1.2. ከማንበብ ተነሳሽነት የጹሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

2. ቡድናዊ መማር ስልት በኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የማንበበብ ተነሳሽነት ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ምንድነው?

የሚል ጥያቄ በዚህ ጥናትዝርዝር አላማ ላይ ተጠይቋል፡፡ በመሆኑም ለዚህ ጥያቄ ምላሽ ለማግኘት በቅድመና ድህረልምምድ ስልጠና ቡድናዊ መማር የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ለማንበብ ትምህርት ይዘት ያላቸውን የማንበብ ተነሳሽነትምን እንደሚመስል መረጃ ለመሰብሰብ ነው፡፡ ሆኖም በሌሎች ተመሳሳይ የክፍል ደረጃና በጥናቱ በማይካተቱ ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሶት መጠይቆቹ ተሞልተው አስተማማኝነታቸው ተረጋግጧል፡፡ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች አስቀድሞ ለማንበብ ተነሳሶት ለማወቅ ቅድመ የማንበብተነሳሶት የጹሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ በማስከተልም መምህሩ በስልጠና የታገዘ የክፍል ውስጥ ልምምድ እንዲሰጥ ተደርጎ ከተጠናቀቀ በኋላ የሙከራ ቡድኑ ድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡

ሰንጠረዥ7.ከሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመ ቡድናዊ ልምምድ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣምእስማማለሁ 1 | | እስማማለሁ 2 | | አልስማማም 3 | | ፈጽሞአልስማ 4 | |
| | | ብዛት | % | ብዛት | % | ብዛተ | % | ብዛት | % |
| 1 | በቡድን መማርየማንበብ ትምህርት ይዘትንለመማር ያነሳሳኛል። | 8 | 19 | 8 | 19 | 14 | 33.3 | 12 | 28.6 |
| 5 | የምንባቡን ሀሳብ ለመረዳት ስለምችገር ከኔበተሸለከሚያነቡተማሪዎቾጋርበቡድንማንበብለማንበብያነሳሳኛል። | 4 | 9.5 | 14 | 33.3 | 10 | 23.8 | 14 | 33.3 |
| 10 | የአንድን ጽሁፍ ሀሳብ መልዕክት በሚገባ ለመገንዘብ በቡድንእየተወያየን ማንበብ ለማንበብ ይስበኛል። | 7 | 16.6 | 11 | 26.2 | 10 | 28.6 | 14 | 38.9 |
| 13 | ከማንበብ በኂላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ምንባቡን በቡድን ማንበብ ጠቅሞኛል። | 9 | 21.4 | 8 | 19 | 10 | 23.8 | 15 | 35.7 |
| 17 | ከቡድናችን ሞዴል የሆኑ ተማሪዎች ሲያነቡ ለማንበብእንድነሳሳ አድርጎኛል። | 7 | 16.6 | 7 | 16.6 | 17 | 40.5 | 11 | 26.2 |

ሰንጠረዠ 7.የሙከራ ቡድን ተማሪዎች በቅድመ የማንበብ ተነሳሽነት ስልጠና በቁጥሮቹ ለቀረቡት መጠይቆች የሰጡትን ምላሽ ነው።በተራ ቁጥር 1 በቡድንመማር የማንበብ ትምህርት ይዘትንለመማርያነሳሳኛል።ለሚለው መጠይቅ ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ (28.6 %) ቱ ፈጽሞ አልስማማምና (33.3 %)ቱ አልስማማም በጥቅሉ (61.9 %)ቱ አለመስማማታቸውን አመላክቷል፡ በተራቁጥር 5 የምንባቡን ሀሳብ ለመረዳት ስለምቸገር ከኔ በተሸ ለከሚያነቡ ተማሪዎቸ ጋር በቡድን ማንበብ ለማንበብ ያነሳሳኛል። ለሚለው መጠይቅ የሰጡት ምላሽ(28.6)ቱ ፈጽሞ አልስማማም (19 %)ቱ አልስማማም በጥቅሉ (57.1 %) ቱ አለመስማማታቸውን ያሳያል። በተራ ቁጥር 10የአንድን ጽሁፍ ሀሳብ መልዕክት በሚገባ ለመገንዘብ በቡድን እየተወያየን ማንበብ ለማንበብ ይስበኛል። ለሚለው መጠይቅ የሰጡት ምላሽ (38.9%)ቱፈጽሞ አልስማማም

(28.6%)ቱ አልስማማም በድምሩ (67.5%) አለመስማማታቸውን ያሳያል፡፡ በተራ ቁጥር 13ከማንበብ በኋላ የሚቀርቡ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን ለመመለስ ምንባቡን በቡድን ማንበብ ጠቅሞኛል፡፡ ለሚለው መጠይቅ የሰጡት ምላሽ (35.7%)ቱ ፈጽሞ አልስማማም (23.8%) አልስማማም በድምሩ (59.5%) አለመስማማታቸውን ያሳያል፡፡ በተራ ቁጥር17ከቡድናችን ሞዴል የሆኑ ተማሪዎች ሲያነቡ ለማንበብ እንድነሳሳ አድርጎኛል፡፡ ለሚለውመጠይቅ የሰጡት ምላሽ(26.3)ቱ ፈጽሞ አልስማማም (40.5%) አልስማማም በድምሩ(66.8%) አለመስማማትን የሚያሳይ ነው፡፡

አንጻራዊ በሆነ መልኩ ሲታይ ደግሞ ተማሪዎቹ መስማማታቸውን በተራቁጥር 1በቡድን አንብቦ የመረዳት ትምህርት ይዘትን ማንበብ ለማንበብ ያነሳሳኛል፡፡ ለሚለው መጠይቅ የሰጡት ምላሽ(19%)ቱበጣም እስማማለሁ(19%)ቱ እስማማለሁ በድምሩ (38%)ቱ መስማማታቸውን ያመላክታል፡፡ በተራ ቁጥር 5 በተሻለ ከሚያነቡ ተማሪዎች ጋር ማንበብ ለማንበብ ያነሳሳኛል ለሚለው መጠይቅ የሰጡት ምላሽ(9.5%)በጣም እስማማለሁ (33.3%) እስማማለሁ በድምሩ (42.8%)ቱ መስማማታቸውን አሳይቷል፡፡ በተራ ቁጥር 10 ምንባቡን በቡድን እየተወያየን በቡድን ካነበብን የምንባቡን ሀሳብ በቀላሉ እገነዘባለሁ ለሚለው መጠይ (16.6%)ቱ በጣም እስማማለሁ (26.2%) እስማማለሁ በድምሩ(42.8%)ቱ መስማማታቸውን አመላክቷል፡፡ በተራ ቁጥር 13 የማንበብ ትምህርት ይዘትን በግል ከማንበብ ይልቅ በቡድን ማንበብ ለማንበብ ያነሳሳኛል ለሚለው መጠይቅ የሰጡት ምላሽ (21.4%)ቱ በጣም መስማማታቸውን(19%) እስማማለሁ በድምሩ (40.4%) መስማማታቸውን ያመላክታል፡፡ በተራ ቁጥር 17ከቡድናችን በተሻለ የሚያነቡ ተማሪዎች ሲያነቡ ለማንበብ እንድነሳሳ አድርጎኛል፡፡ ለሚለው መጠይቅ (16.6%)ቱ በጣም እስማማለሁ (16.6%)ቱ በድምር(33.2%) መስማማታቸውን አሳይቷል፡፡

በአጠቃላይ በሰንጠረዡ ከቀረበው መረጃ መገንዘብ የሚቻለው ተማሪዎቹ በቅድመ ቡድናዊ መማር የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ የሰጡት ምላሽ ሲታይ ከፍተኛው ፐርሰንት በቡድን መማርን አለመፈለጋቸውን ነው፡፡ በአንጻራዊ ሲታይ ደግሞ አነስተኛ ውፐርሰንት በቡድን ለማንበብ የሚፈልጉ መሆኑን አመላክቷል፡፡

ሰንጠረዥ8. የሙከራ ቡድኑ በድህረ ቡድናዊ ልምምድ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ የተገኘ መረጃ

| ተ.ቁ | ጥያቄዎች | አማራጮች | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | በጣምእስማማለሁ1 | | እስማማለሁ 2 | | አልስማማም 3 | | ፈጽሞ አልስማማም 4 | |
| | | በዛት | % | በዛት | % | በዛት | % | በዛት | % |
| 1 | በቡድንመማር የማንበብ ትምህርት ይዘትን ለመማርያነሳሳኛል። | 18 | 42.9 | 13 | 31 | 5 | 12 | 6 | 14.3 |
| 5 | የምንባቡን ሀሳብ ለመረዳት ስለምቸገር ከኔበተሻለከሚያነቡተማሪዎቸ ጋርበቡድ ንማንበብለማንበብ አነሳስቶኛል። | 14 | 33.3 | 16 | 38.1 | 10 | 23.8 | 2 | 4.8 |
| 10 | የአንድን ጽሁፍ ሀሳብ መልዕክት በሚገባ ለመገንዘብ በቡድንእየተወያየን ማንበብ ለማንበብ ስቦኛል ። | 13 | 31 | 12 | 28.6 | 8 | 19 | 9 | 21.5 |
| 13 | ከማንበብ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ምንባቡን በቡድን ማንበብ ጠቅሞኛል። | 16 | 38.1 | 13 | 31 | 7 | 16.7 | 6 | 14.3 |
| 17 | ከቡድናችን ሞዴል የሆኑ ተማሪዎች ሲያነቡ ለማንበብ እንድነሳሳ አድርጎኛል። | 17 | 40.5 | 11 | 26.2 | 8 | 19 | 6 | 14.3 |

ሰንጠረዠ 8.የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ከድህረ የማንበብ ተነሳሽነት ስልጠና ለቀረቡት መጠይቆች የሰጡትንምላሽነው። በተራቁጥር 1 በቡድን መማር የማንበብ ትምህርት ይዘትን ለመማር ያነሳሳኛል። ለሚለው መጠይቅ ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ (14%)ቱ ፈጽሞ አልስማማምና(12%)ቱ አልስማማም በጥቅሉ (26%)ቱ አለመስማማታቸውን አመላክቷል። በተራቁጥር 5 የምንባቡን ሀሳብ አንብቦ ለመረዳት ስለምቸገር ከኔ በተሸ ለከሚያነቡ ተማሪዎቸ ጋር በቡድን ማንበብ ለማንበብ አነሳስቶኛል። ለሚለው መጠይቅ የሰጡት ምላሽ (4.8%)ቱ ፈጽሞ አልስማማም (23.8 %)ቱ አልስማማም በጥቅሉ(28.6 %) ቱ አለመስማማታቸውን ያሳያል። በተራቁጥር 10 የአንድን ጽሁፍ ሀሳብ መልዕክት በሚገባ ለመገንዘብ በቡድን እየተወያየን ማንበብ ለማንበብ ስቦኛል። ለሚለው መጠይቅ የሰጡት ምላሽ (21.5%) ቱ ፈጽሞ አልስማማም (19%)ቱ አልስማማም በድምሩ(40.5% ) አለመስማማታቸውን ያሳያል። በተራ

ቁጥር 13 ከማንበብ በኋላ የሚቀርቡ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን ለመመለስ ምንባቡን በቡድን ማንበብ ጠቅሞኛል፡፡ ለሚለው መጠይቅ የሰጡት ምላሽ (14.3%)ቱ ፈጽሞ አልስማማም (16.7%) አልስማማም በድምሩ (31%) አለመስማማታቸውን ያሳያል፡፡ በተራ ቁጥር 17 ከቡድናችን ሞዴል የሆኑ ተማሪዎች ሲያነቡ ለማንበብ እንድነሳሳ አድርጎኛል፡፡ (14.3) ቱፈጽሞ አልስማማም(19%) አልስማማም በድምሩ (33.3%) አለመስማማትን የሚያሳይ ሲሆን (26%)ቱ አለመስማማታቸውን ነው፡፡

አንጻራዊ በሆነ መልኩ ሲታይ ደግሞ ተማሪዎቹ በድህረ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ መስማማታቸውን በያንዳንዱ መጠይቅስን መለከት በተራቁጥር 1 በቡድን የማንበብ ትምህርት ይዘትን ማንበብ ለማንበብ ያነሳሳኛል፡፡ ለሚለው መጠይቅ የሰጡትምላሽ (42.9%)ቱ በጣም እስማማለሁ (31%)ቱ እስማማለሁ መስማማታቸውን ያመላክታል፡፡ በድምሩ (73.9%)ቱ መስማማታቸውን አመላክተዋል፡፡ በተራቁጥር 5 የምንባቡን ሀሳብ አንብቦ ለመረዳት ስለምቸገር ከኔ በተሸለ ከሚያነቡ ተማሪዎቸ ጋር በቡድን ማንበብ ለማንበብ አነሳስቶኛል፡፡ ለሚለው መጠይቅ የሰጡት ምላሽ (33.3%)በጣምእስማማለሁ (38.1 %) እስማማለሁበጥቅሉ (71.4%) ቱመስማማታቸውተመላክቷል፡፡ በተራቁጥር 10 የአንድን ጽሁፍ ሀሳብ መልዕክት በሚገባ ለመገንዘብ በቡድን እየተወያየን ማንበብ ለማንበብ ስቦኛል፡፡ ለሚለው መጠይቅ (31%)ቱ በጣም እስማማለሁ(28.6%) እስማማለሁ በድምሩ (59.6%)ቱ መስማማታቸውን አመላክቷል፡፡ በተራ ቁጥር13 የማንበብ ትምህርት ይዘትን በግል ከማንበብ ይልቅ በግል ማንበብ ለማንበብ ያነሳሳኛል ለሚለው መጠይቅ የሰጡት ምላሽ (38.1%)ቱ በጣም መስማማታቸውን (31%)ቱ እስማማለሁ በድምሩ(69.1%) መስማማታቸውን ያመላክታል፡፡ በተራ ቁጥር17 ከቡድናችን በተሻ ለየሚያነቡ ተማሪዎች ሲያነቡ ለማንበብ እንድነሳሳ አድርጎኛል፡፡ ለሚለው መጠይቅ (40.5%)ቱ በጣም እስማማለሁ (26.2%)ቱ በድምር(66.7%) መስማማታቸውን አሳይቷል፡፡ በሰንጠረዡ ከተተነተነው መረጃ መገንዘብ የሚቻለው ተማሪዎቹ በድህረ ልምምድ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ ያስመዘገቡት ምላሽ ከቅድመ ልምምድ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ የሰጡት ምላሽ ጋር ሲነጻጸር ልዩነት ያለው መሆኑን ነው፡፡

ተማሪዎቹ በቅድመ መጠይቅ ከሰጡት ምላሽ መረዳት እንደተቻለው አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በቡድን ለማንበብ ተነሳሽነት የሌላቸውና የማይፈልጉ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ተረጋግጧል፡፡ ነገር ግን መምህሩ የተለያዩ ምሁራንን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ለመምህሩ በተሰጠው ስልጠና

መሰረት ለተማሪዎቹ በየክፍለ ጊዜው ቡድናዊ ግንዛቤ በመስጠት ተማሪዎቹን በቡድን ርስ በርሳቸው እየተጋገዙ የቀረበላቸውን ምንባብ በተደጋጋሚ እየተወያዩ እንዲያነቡ ማድረግ መቻሉ ተማሪዎቹ ስለ ቡድናዊ መማር ጠቀሜታ ግንዛቤ ኖሯቸው በቡድን ለማንበብ ተነሳሶት የፈጠረላቸውና ቡድናዊ መማርን የወደዱት እንደሆነ በመጠይቁ በሰጡት ምላሽ ማወቅ ተችሏል፡፡ ከዚህ የምንረዳው በቅድመውና ድህረ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ መካከል ጉልህ ልዩነት ሊመጣ የቻለው ተማሪዎቹ ከቅድመ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ የበለጠ በድህረ መጠይቁ ስለ ቡድናዊ መማር ግንዛቤ በማግኘታቸው ምክንያት ፈጽሞ አልስማማም ከሚለው ምላሽ ይልቅ በጣም እስማማለሁ ወደሚለው መምጣታቸውን በመጠይቁ የሰጡት ምላሽ በመቶኛ ተሰልቶ ከቅድመው መጠይቁ ብልጫ ማሳየቱ ተረጋግጧል፡፡

### 4.1.3.ከምልከታ የተገኘ መረጃ ትንተና

በጥናቱ ለመረጃ ለመሰብሰብ ተግባራዊ ከሆኑት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች መካከል አንዱ ምልከታ ነው፡፡አስቀድሞ ለመግለጽ እንደተሞከረው አጥኚዋ ምልከታን በመማሪያ ክፍል ውስጥ ለማካሄድ የፈለገችበት ትልቁ ምክንያቷ በክለሳ ድርሳኑ ስለ ቡድናዊ መማርጠቀሜታ፣መመሪያ፣ ተማሪው ከቡድናዊ መማር የሚያገኛቸው ክህሎት፣መኀበራዊ ግንኙነት፣የርዕሰ ጉዳዮች ግንዛቤ፣ የርስበርስ መማማርና የመሳሰሉትን የSlavin (1983)፣ Vygotsky (1978)፣ Dennick & Exley (1998)፣ Burke (2011) ሀሳቦችን መሰረት በማድረግ ለመምህሩ ስልጠና ሰታለች፡፡ ስለዚህ ለጥናቱ አስተማማኝነት መምህሩ በተሰጠው ስልጠና መሰረት በክፍል ውስጥ ምን ያህል ተግባራዊ ሆኗል የሚለውን ለማረጋገጥ ነው፡፡

መምህሩ በሚያስተምርበት ጊዜ በክፍል ውስጥ በቡድን መማር ሂደቱ የተከናወኑትን ነጥቦች በቅደም ተከተል ምልከታ ተካሂዷል፡፡ አጥኚዋ ምልከታ ያካሄደቸው በቁጥጥርና ሙከራ ቡድኑ በሚማሩበት ክፍል በመዘዋወር ነው፡፡

ሰንጠረዥ9.መምህሩ ሙከራ ቡድኑን በክፍል ውስጥ ሲያስተምር የተካሄደ ምልከታ

| ተ.ቁ | የክፍል ውስጥ ክንውን | የክንውኑ ምልከታ ብዛት | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ምልከታ | ምልከታ | ምልከታ | ምልከታ | ምልከታ | |
| 1 | የዕለቱን ትምህርት አላማ ማሳወቅ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | 5 |
| 2 | ስለ ቡድናዊ መማር አላማ  ማስገንዘብ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | 5 |
| 3 | ተማሪዎቹን በቡድን ማስቀመጥ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | 5 |
| 4 | ተማሪዎችን ለማነሳሳት ቡድናዊ መርሆች ተገልጸዋል | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | 5 |
| 5 | ምንባቦቹ ለተማሪዎቹ ቀርበዋል | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | 5 |
| 6 | በተሻለ የሚያነቡ ተማሪዎችን ለይቷል | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | 5 |
| 7 | የቀረበውን ምንባብ በቡድን እንዲወያዩ አድርጓል | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | 5 |
| 8 | ተማሪዎቹ በቡድን መስራታቸውን ተከታትሏል | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | 5 |
| 9 | ተማሪዎቹ ርስ በረስ እንዲተጋገዙ አደርጓል | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | 5 |
| 10 | ከምንባብ በኋላ መልመጃዎችን አሰርቷል | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | 5 |
| 11 | ከማንበብ በኋላ መረዳታቸውን ገምግሟል | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | 5 |
| 12 | አስፈላጊ ሲሆን ከየቡድኑ ጋር ሀሳብ ተለዋውጠዋል | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | 5 |

ሰንጠረዥ 9.የሚያመላክተው መምህሩ የሙከራ ቡድኑን በመማሪያ ክፍል ውስጥ በቡድናዊ መማር ስልት ተግባራዊ ሲያደርግ በአጥኚዋ የተካሄደውን ምልከታ ነው፡፡ ከሰንጠረዡ የምንረዳው መምህሩ በሙከራ ቡድኑ ክፍል የቀረቡትን ቡድን ተኮር ክንውኖች በተሰጠው ስልጠና መሰረት ሙሉ በሙሉ ተግብሮ መገኘቱን ነው፡፡ በጥቅሉ አጥኚዋ በሙከራ ቡድኑ መማሪያ ክፍል ባደረገቸው ምልከታ መምህሩ ቡድናዊ መማር ስልትን ተግባራዊ ማድረጉን አረጋግጣለች፡፡

ሰንጠረዥ10.መምህሩ የቁጥጥር ቡድኑን በክፍል ውስጥ በሚያስተምርበት ጊዜየተካሄደ ምልከታ

| ተ.ቁ | የክፍል ውስጥ ክንውን | የክንውኑ ምልከታብዛት | | | | | ድምር |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | ምልከታ | ምልከታ | ምልከታ | ምልከታ | ምልከታ | |
| 1 | የዕለቱን ትምህርት አላማ ማሳወቅ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | 5 |
| 2 | ስለ ቡድናዊ መማር አላማ ማስገንዘብ | X | X | X | X | X | 0 |
| 3 | ተማሪዎቹን በቡድን ማስቀመጥ | X | X | X | X | X | 0 |
| 4 | ተማሪዎችንለማነሳሳትቡድናዊመርሆችተገልጸዋል | X | X | X | X | X | 0 |
| 5 | ምንባቦቹ ለተማሪዎቹ ቀርበዋል | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | 5 |
| 6 | በተሻለ የሚያነቡ ተማሪዎችን ለይቷል | X | X | X | X | X | 0 |
| 7 | የቀረበውንምንባብ በቡድን እንዲወያዩ አድርጓል | X | X | X | X | X | 0 |
| 8 | ተማሪዎቹ በቡድን መስራታቸውን ተከታትሏል | X | X | X | X | X | 0 |
| 9 | ተማሪዎቹ እርስ በረስ እንዲተጋገዙ አደርጓል | X | X | X | X | X | 0 |
| 10 | ከምንባብ በኋላ መልመጃዎችን አሰርቷል | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | 5 |
| 11 | ከማንበብ በኋላ መረዳታቸውን ገምግሟል | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | ✓ | 5 |
| 12 | አስፈላጊ ሲሆን ከየቡድኑ ጋር ሀሳብ ተለዋውጠዋል | X | X | X | X | X | 0 |

ሰንጠረዥ10.የሚያመለክተው መምህሩ በቁጥጥር ቡድኑ ክፍል ሲያስተምር በአጥኝዋ የተካሄደውን ምልከታ ነው፡፡ ከሰንጠረዡ መረዳት የሚቻለው መምህሩ በቁጥጥር ቡድኑ ማስተማር ከሙከራ ቡድኑ ጋር ሲነጻጸር ከተወሰኑ ክንውኖች በቀር ልዩነት ያለው መሆኑን ነው፡ ያውም መምህሩ በሙከራ ቡድኑ ሁሉንም ቡድናዊ መማር ክንውኖች የተገበር ሲሆን በቁጥጥር ቡድኑ ግን ክንውን 1፣5፣10፣11 ን ብቻ መተግበሩን መመልከት ተችሏል፡፡ ከዚህ የምንገነዘበው መምህሩ የቁጥጥር ቡድኑና ሙከራ ቡድኑን በማስተማር ሂደት ልዩነት የታየው የቁጥጥር ቡድኑ

በቡድናዊ መማር ባለመማራቸው ምክንያት ሁሉንም ዝርዝር ነጥቦች ተግባራዊ አለማድረጉን በተካሄደው ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

### 4.1.4.ከሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ድህረ ቡድናዊ መማር የተሰበሰቡ ቡድን ተኮር ውይይት መረጃዎች ትንተና

ለዚህ ጥናት ከምልከታ በተጨማሪ በአጋዥነት ለመረጃ መሰብሰቢያነት መሳሪያ ተግባራዊ የሆነው ቡድን ተኮር ውይይት ነው፡፡ ሆኖም ከቡድናዊ መማር ድህረ ልምምድና ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና በኋላ በቡድን መማር ስልት ትምህርት ከተከታተሉት 42 ሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል አጠቃላይ ለአምስት ተማሪዎች በክፍለ ትምህርቱ ማረፊያክፍል ውስጥ ቡድን ተኮር ውይይት ተካሂዶ ተማሪዎቹ የሰጡት ምላሽ በቅደም ተከተል እንደሚከተለው ቀርቧል፡፡

1.በቡድን መማር ምን ጠቀሜታ አለው?

ለቀረበላቸው ጥያቄ ከሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል አንዱ የሆነው የሰጠው ምላሽ ቀጥሎ ይቀርባል፡፡

የማንበብ ትምህርትን ስንማር ከመካከላችን በተሻለ ከሚያነቡ ተማሪዎች
ጋር ቡድን መስርቼ በጋራ በመወያየት፣ግልጽ ያልሆነውን ከጓደኞቼ
በመጠየቅ ስናነብ የምንባቡን ሀሳብ በቀላሉ እንድገነዘብ፣እርስበርሳችን
እንድንግባባ፣ያልገባኝን ጠይቄእንድረዳ ጠቅሞኛል፡፡
19/ 09/ 2015

2.በመማሪያ መጽሐፋቸው ከቀረበላቸው ቡድናዊ መማርና በጥናቱ ከታቀፉችሁ በኋላ የታዘባችሁት ነገር ምንድነው?

ለሚለው ጥያቄ ከዚሁ የሙከራ ቡድን ሁለተኛው ተማሪ ለቀረበለት ጥያቄ የሰጠው ምላሽ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

በጋራ እንድንተገብር የሚሰጡን ተግባራት ቢኖሩም ለመስራት የቡድናዊ
መማርን ጠቀሜታ በተመለከተ መምህራን ግንዛቤ ሰተውን ስለማያውቁ
ከቡድናችን የሚችል ተማሪ የቡድን ስራውን በችሎታው ሰርቶ ለመምህሩ
ይሰጥና ውጤታችን ብቻ ይነገረናል እንጂ በያንዳንዱ ሀሳብ ላይ ሁላችንም
ሀሳቡን ለመረዳት ሰርተን አናውቅም፡፡
19 /09 /2015

3. በግል ማንበብና በቡድን ማንበብ ምን ልዩነት አለው? በማለት ለቀረበላቸው ጥያቄ ከሙከራ

ቡድኑ አንዲት ተማሪ ቀጥሎ የቀረበውን ምላሽ ሰታለች፡፡

በግል ማንበብ  በተሻለ ለሚያነቡ ተማሪዎች ብቻ እንጂ  ለሁሉም ተማሪዎች ወይም በማንበብ ደካማ ለሆኑ ተማሪዎች ጠቃሚ አይደለም ይህንያልኩትም አንዱ ሌላውን እያገዘና እርመት እየሰጠ በመተጋገዝ ስናነብ የምንባቡን ሀሳብ እንድረዳለምጠየቀው የአንብቦ መረዳት ጥያቄዎችበቂ ምላሽእሰጣለሁ፡፡

19 /09 /2015

4. ቡድን መስርቶ ማንበብ ለማንበብ ያነሳሳል ወይስ አያነሳሳም?

የሚል ጥያቄ ቀርቦ በሙከራ ቡድኑ ከተሳተፈ ተማሪ አንዲህ በማለት ምላሽ ሰቷል፡፡

አንድ የቀረበልንን ንባብ በቡድን በምናነብበት ጊዜ ከጎናችን በተሸለ የሚያነቡትን ጓደኞችንን በምመልከትበት ጊዜ የማንበብ ችሎታችን ደከም የምንል ተማሪዎችየመፎካከርና ለማንበብ መነሳሳትን ፈጥሮልኛል፡፡

19 /09 /2015

5. በቡድን መማር በመሃበራዊ ግንኙነታቹ ላይ ችግር ፈጥሮባችኋል?

በማለት ለተጠየቀው ጥያቄ በሙከራ ቡድኑ ከተማሩት አንዲት ተማር የሰጠችው ምላሽ እንደሚከተለው ይቀርባል፡፡

በቡድን የቀረበልንን ምንባብ በመወያየት መማራችን ሁላችንም ለማንበብ እንድበረታታ፣ፍረሃትእንዳስወግድ፣በተለይ ከጎበዝ ተማሪዎች ጋር ቡድን ስመሰርት ከነሱ ጋር እንድፎካከርና የነሱን ፈለግ እንድከተል፣ርስ በርሳችን እንድንግባባ፣ችሎታዬ ሌሎችን በማየት እንዲሻሻል አግዞኛል እንጂ ጉዳት የለውም፡፡ በተጨማሪም መምህሬ እርምት ከሚሰጡኝ ይልቅ በጓደኞቼ አማካይነት ማስተካከያ ሲሰጠኝ ያለ ፍረሃት በቀላሉ ሀሳቡን ለመገንዘብና እርምት ለመውሰድ ጠቅሞኛል፡፡

19 /09 / 2015

## 4.2.የጥናቱ ውጤት ማብራሪያ

በጥናቱ መነሻ ላይ እንደተቀመጠው ይህ ጥናት በዋናነት ይዞት የተነሳው አላማ ቡድናዊ መማር ስልት የኢ-አፍፈት ተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ችሎታ  ለማጎልበት

ያለውን ጠቀሜታ መመርመር የሚል ነው፡፡ ጥናቱ ከፊል ሙከራዊ እንደመሆኑ መጠን የሙከራና ቁጥጥር ቡድኖችን ይዟል፡፡ በመሆኑም ቡድናዊ መማር አንብቦ የመረዳትና የማንበብ ተነሳሽነትን ለማጎልበት ያለውን ጠቀሜታ ለመፈተሽም የማንብብ ተነሳሽሽነት፣አንብቦ የመረዳት ፈተና፣ምልከታና ቡድን ተኮር ውይይት መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች አማካይነት መረጃ ተሰብስቧል፡፡ የተሰብሰቡት መረጃዎች ውጤትም እንደየ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎቹና መረጃው ባህሪ በስታትስቲክስተተንትነው ለማሳየት ተሞክሯል፡፡ ከላይ በቀረበው የጥናቱ ውጤት ትንተና መሰረትም ለጥናቱ ጥያቄዎች ቀጥሎ ማብራሪያ ይሰጥባቸዋል፡፡

1.ቡድናዊ መማር አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት ያለው ጠቀሜታ ወይም

አስተዋጽኦ ምንድነው?

በቡድናዊ መማር የኢ-አፍፈት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለውን አስተዋጽኦ መመርመር፡፡ የሚለውንጥናቱ ይዞት የተነሳውን አላማ ለመመርመር ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው በመረጃ መሳሪያዎቹ የተሰበሰቡት መረጃዎች ተተንትነዋል፡፡

ሆኖም አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለመፈተሽ የቁጥጥርና ሙከራ ቡድኖቹ በቡድናዊ መማር ስልት ከመማራቸው አስቀድሞ ቅድመ አንብቦ የመረዳት ፈተና ተፈትነው የተገኘው ውጤት በገላጭ ስታትስቲክስ ስሌት ተሰልቶ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ያለው አማካይ ውጤት ልዩነት እንደሌለው መገንዘብ ተችሏል፡፡ በተጨማሪም በገላጭ ስታትስቲክስ ብቻ ማስላት የአማካይ ውጤት የጉልህነት ደረጃን ማወቅ ስለማይቻል በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ተፈትሾ ውጤቱ ከ(0.05) በልጦ መገኘቱ በቁጥጥርና ሙከራ ቡድኑ መካከል በቅድመ አንብቦ የመረዳት ፈተና የአማካይ ውጤት መካከል ብዙ ልዩነት እንደሌለ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

በማስከተልም በቅድመ ፈተና ያለው ውጤት ከተረጋገጠ በኋላ የቁጥጥር ቡድኑ ያለ ቡድናዊ መማር ዘዴ የሙከራ ቡድኑ ደግሞ ስልጠናን በመታገዝ በቡድናዊ መማር ስልት አንብቦ የመረዳት ትምህርትን በተከታታይ እንዲማሩ ከተደረገ በኋላ ሁለቱም ቡድኖች ተፈትነዋል፡፡ የሙከራና የቁጥጥር ቡድኖቹ በድህረ ፈተናው ያስመዘገቡት አማካይ ውጤትም በገላጭ ስታትስቲክስ (Discribtive) ተሰልቶ የሙከራ ቡድኑ ከቁጥጥር ቡድኑ ውጤት በልጦ ተገኝቷል፡፡ በድጋሜም ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና በገላጭ ስታትስቲክስ ስሌት ብቻ ማወቅ ስለማይቻል በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት (paired sample t-test) ተፈትሾ ከ(0.05) አንሶ ተገኝቷ፡፡

ከዚህ በላይ ለማሳየት የተሞከረው በቁጥጥርና ሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና የአማካይ ውጤትመካከል ያለውን ልዩነት ነው፡፡ ቀጥሎ መስመራዊ በሆነ መንገድ በድህረ ቡድኑ ቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተናና በቁጥጥር ቡድኑ ቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና መካከል ያለውን የአማካይ ውጤት ጉልህነት ደረጃ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ለማሳየት ይሞከራል፡፡

በሙከራ ቡድኑ ቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና የአማካይ ውጤት ልዩነት የጉልህነት ደረጃ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲፈተሽ የተገኘው ውጤት(ፒ<0.05) አንሶ በመገኘቱ ጉልህ ልዩነት መኖሩ ተረጋግጧል፡፡ የቁጥጥር ቡድኑ ቅድመና ድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና የአማካይ ውጤት ልዩነት የጉልህነት ደረጃ በጥንድ ናሙና ቲ-ቴስት ሲፈተሽ የተገኘው ውጤት ($P>0.05$) በልጦ በመገኘቱ በሁለቱ ቡድኖች መካከል ልዩነት አለመኖሩ ተረጋግጧል፡፡

ስለዚህ ቡድናዊ መማር ስልት የኢ-አፍፊት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማጎልበት ያለው ጠቀሜታ(አስተዋጽኦ) ምንድነው? የሚለው ጥያቄ የዚህ ጥናት ውጤት ተገቢውን ምላሽ አስገኝቷል፡፡በተመራማሪዋ እምነት ይህ የተማሪዎቹ የውጤት ልዩነትሊመጣ የቻለበት ምክንያት ኢ-አፍፊት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበት በግል ከማንበብ ይልቅ በቡድናዊ ትግግዝ መማር አንዱ ከሌላው ጋር በመደጋገፍና በመተራረም የቀረበላቸውን የአንብቦ መረዳት ተግባር ማካሄዳቸው አንብቦ የመረዳት ክሂችሎታቸው የበለጠ እንዲጎለብት አድርጎላቸዋል ብላ ታምናለች፡፡

ሆኖም ከጥናቱ ግኝት መገንዘብ የሚቻለውም ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ትምህርት ይዘትን በቡድን መማርተግባራዊ ማድረግ በመካከላቸው ፍኩኩር እንዲኖር፣በጋራ እንደወያዩ፣ርስበርስ እዲተጋገዙ፣ጥልቅ አሳቢ እንዲሆኑ፣ለሚጠየቁት ጥያቄ የተደራጀ ምላሽ እንዲሰጡ፣ጥሩ አድማጭ እንዲሆኑ፣ክሂሎትንእንዲያገኙ፣አንብቦ የመረዳትችሎታቸውን እንዲያጎለብቱ የሚያደርግ መሆኑን ነው፡፡ ተማሪዎች በጋራ በመወያየት ሲማሩ አንዱ ከሌላው በመማር እውቀቱን የበለጠ እያሻሻለ እንዲሄድ የሚያደርግ ነው፡፡

ለዚህ ጥናት ግኝት መምጣት ቡድናዊ መማር ተማሪዎቹ በቡድናዊ መማር እየተጋገዙ አንዱ ያልተረዳውን ግንዛቤ ካለው በመጠየቅ ርስ በርስ የሚማማሩበትና ከግል እውቀታቸው በበለጠ ከሌሎች በመጠየቅ ግንዛቤ የሚያገኙበት፣መሻሻልን የሚያሳዩበት እንዲሁም በቡድን ውይይት ያዳበሩትን እውቀት ለሚጠየቁት ጥያቄ በቂ ምላሽ እንዲሰጡ በማድረግ ረገድ ቡድናዊ መማር ከፍተኛ አስተዋጽኦ ማድረጉን ነው፡፡

ለጥናቱ ግኝት ሌላው አስተዋጽኦ ያደረገው፣ተማሪዎቹ ስለቡድናዊ መማር በየርዕሰ ጉዳዩ ግንዛቤ እንዲያገኙ መደረጉና በክፍል ውስጥ ቡድናዊ ልምምድ ትምህርቱ ተግባራዊ መደረግ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ እስከሚጠናቀቅ ድረስ አንብቦ የመረዳት ትምህርት ይዘትን በመማር ሂደት ርስ በርሳቸው መጠያየቃቸው አንዱ ለሌለው ግንዛቤ መስጠት መቻሉ፣በተሻለ የሚያነቡ ተማሪዎች የማንበብ ችሎታቸው ዝቅተኛ ለሆኑ ተማሪዎች እንዲያግዙና እንዲወያዩ መደረጉ ነው፡፡

በጥናቱ በድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተናው ከቅድመ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተናው በልጦ ወይም ጉልህ ሆኖ ለመገኘቱ ምክንያት ቡድናዊ መማር ተግባራዊ መሆን መቻሉ ከተገኘው ግኝት ማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ሆኖም የዚህ ጥናት ግኝት(ውጤት) በክለሳ ድርሳኑ እንደተገለጸው Kitchen (2012)፣ Brown(2010)፣ Slavin(1983)፣ Burke 2011፣ Johnson Johnson (1994)፣Vygotsky (1978)፣Istifci (2009)፣ Bialystok (1983)፣Hosenfeld (1981) ሀሳብ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡

ይህ ጥናት አስቀድሞ ከተካሄዱ ጥናቶች በላይነሽ (2010)፣እመቤት(2011)፣Boruvkova፣ Emanovsky(2016)Springre፣Stanneና Donovan(1999) ጥናትግኝት ጋር ተቀራራቢነት አለው፡፡ ጥናቱ ከላይ ከተጠቀሱት ጥናቶች ጋር የሚቀራረብ ሲሆን ከዑመር (2000)፣ Girma (2003) ጥናት ውጤት ጋር የሚቃረን ሆኖ ተገኝቷል፡፡

ያውም የነዚህ ጥናቶች ውጤት  መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች በቡድን ለሚከናወኑ ተግባራት ላይ ክትትል አያደርጉም፣ተግባራትን አይገመግሙም መምህራን ቡድናዊ መማርን በተመለከተ ተግባራትን ከመስጠት በዘለለ የቡድናዊ መማርን ውጤታማነትና ጠቀሜታን ፈጽሞ ትኩረት ያልተደረገበትና ቡድናዊ መማር ተማሪዎችን ውጤታማ አያደርግም የሚልና የቡድኑን አባላት ችሎታ፣ተሳትፎ፣ተግባብቶ መስራት፣በቡድኑ ሊከሰቱ የሚችሉ ችግሮችን የመከታተል ሁኔታ አለመኖሩ ነው፡፡

በዚህ ጥናት ውጤት ግን በማንበብ ደከም የሚሉ ተማሪዎች በተሻለ ከሚያነቡ ተማሪዎች ጋር በቡድናዊ መማር ስልት ርስ በርሳቸው እየተጋገዙ አንብቦ የመረዳት ትምህርት ይዘትን እንዲማማሩ በማድረግና በቂ ክትትል ተደርጎላቸው ሲማማሩ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው ይበልጥ መጎልበትን ወይም ለውጥ መኖሩን ተመርምሮ በተገኘው ውጤት ተረጋግጧል፡፡ በአጥኚዋ እምነት የጥናቶቹ ከዚህ ጥናት ውጤት መለየት ምክንያት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ትምህርት ይዘትን በተናጥል እንዲያነቡ መደረጉ በተሸለ ለሚያነቡ ተማሪዎች ብቻ እንጂ ሁሉንም ተማሪዎች አንብበው እንዲረዱ የማያደርግ ሲሆን በዚህ ጥናት ደግሞ በተቃራኒው

ቡድናዊ መማርን ተግባራዊ መደረጉ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታቸው መሻሻሉን መገንዘብ መቻሉ ነው፡፡

2.ቡድናዊ መማር የማንበብ ተነሳሽነት ላይ የሚያሳድረውን ተጽኖ ምንድነው?

በዚህጥናት ዝርዝር አላማ በሁለተኛነት የተጠየቀው ጥያቄ ቡድናዊ መማር በኢ-አፍፊት ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ላይ ያለውን ተጽእኖ ምን እንደሆነ ለማወቅ የተተነተነውን መጠይቅ መረጃን ማብራራት ነው፡፡

በዚህ ጥናት በመነሻ ላይ የተፈተሸው የቁጥጥርና ሙከራ ቡድኖች ቅድመና ድህረ ልምምድ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ ሲሆን የሁለቱ ቡድኖች በቅድመና ድህረ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ በፐርሰንት (በመቶኛ) ሲሰላ ተማሪዎቹ በ1ኛው ጥያቄ በቅድመ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቁ የሰጡት ምላሽ መረጃ ፈጽሞ አልስማማምና አልስማማም በድምሩ (69.9%)ቱ አለመስማማታቸውን ሲያሳይ አንጻራዊ በሆን መልኩ ደግሞ በጣም እስማማለሁና እስማማለሁ (38%)ቱ መስማማቱን ያሳያል፡፡ ከቅድመ መጠይቁ ምላሽ የምንረዳው ተማሪዎቹ በቅድመ ልምምዱ በቡድን ለማንበብ ተነሳሽነት የሌላቸው መሆኑን የሚያሳይ ሲሆን በድህረ ልምምዱ በስልጠና የታገዘ የማንበብ ተነሳሽነት ትምህርት ከተማሩ በኋላ ግን ተማሪዎቹ በመጠይቁ የሰጡት ምላሽበጣም እስማማለሁና እስማማለሁ (73.9%)ቱ መስማማታቸውን ሲያሳይ አንጻራዊ በሆነ መልኩ ደግሞ ፈጽሞ አልስማማምና አልስማማም(26%)ቱ አለመስማማትን ያሳያል፡፡ ከመጠይቁ ምላሽ የምንገነዘበው በቡድናዊ መማር ስልጠና ታግዞ ተማሪዎች የማንበብ ትምህርት ይዘት እንዲማሩ መደረጉ በተማሪዎቹ ላይ አዎንታዊ ለውጥ ያመጣ መሆኑን በሰጡት ምላሽ ተረጋግጧል፡፡

በመሆኑም ተማሪዎቹ በመጠይቁ የሰጡት ምላሽ የሚያመላክተው መምህሩ በቡድናዊ መማር ስልጠና ታግዞ የማንበብ ትምህርት ይዘትን ማስነበብ መቻሉ ለማንበብ ተነሳሶት አስተዋጽኦ እንዳለው ያሳያል፡፡ በስልጠናና ግንዛቤ ያልታገዘ ንባብ በተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ላይ ለውጥ አያመጣም፡፡ ነገርግን መምህራንም ሆኑ ተማሪዎች የቡድናዊ መማር ግንዛቤ ኖሯቸው የመማር ሂደቱ ሲተገበር ይበልጥ ጠቀሜታ እንዳለው ከግኝቱ መገንዘብ ተችሏል፡፡

የዚህ መጠይቅ ግኝትም Dornye & Ema ushoda 2011፣Brown(1992)፣Johnson &Johnsonና Holubec (1994) Dornyei (1998) Krashen (1987)፣Wigfield and Guthrite (1997)ሀሳብ ጋር ተመሳሳይነት አለው፡፡እንዲሁምግኝቱ በምዕራፍ ሁለት ከተጠቀሱት በማንበብ

ተነሳሽነት ላይ ከተሰሩ Barber and Klauda (2019)፣Gthrie &Wigfield (2000) የጥናት ግኝት ጋር ተቀራራቢነት አለው።

የዚህ ጥናት ግኝት ከBehailu (2010) የጥናት ግኝት ጋር ግን ተቃርኖ ያለው ሲሆን ያውም ተማሪዎች ለአገርኛ ቋንቋዎች ትኩረት የማይሰጡና ተነሳሶት የሌላቸውና ይበልጥ በእንግሊዘኛ ቋንቋ ትምህርት ላይ እንደሚያተኩሩ በጥናቱ ግኝት የተረጋገጠ ሲሆን ይህ ጥናት ግን መምህሩ በስልጠና በመታገዝ የክፍል ውስጥ ልምምድ በማድረጉ ምክንያት ለዚህ ጥናት ውጤት መምጣትአሰተዋጽኦ አድርጓል። እንደአጥኚዋ እምነት የBehailu ጥናት ከዚህ ጥናት የሚለየው መምህራንበመማርማስተማር ሂደት ለተማሪዎች ስለ ሀገርኛ ቋንቋ በቂ ግንዛቤ አለመስጠታቸውና በስልጠና በመታገዝ የማንበብ ተግባርን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ አለማድረጋቸው ምክንያት ተማሪዎቹ ለቋንቋው ትምህርት ፍላጎት የሌላቸው እንደሆኑነው።

# ምዕራፍ አምስት

# የጥናቱ ማጠቃለያና አስተያየት

## 5.1.ማጠቃለያ

የጥናቱ ዋና አላማ በቡድን ተከፋፍሎ መማር ስልት የኢ-አፍፈት (አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ውይም አፋቸውን በኦሮምኛ የፈቱ) ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለውን  ጠቀሜታ ከፊል ፍትነታዊና አይነታዊ በሆነ የምርምር ንድፍ መርምሮ ጠቀሜታውን ማረጋገጥ ነው፡፡ ይህ ጥናት ሲካሄድ በዋናው አላማ ስር ምላሽ ለመስጠት ይዟቸው የተነሳው ዝርዝር ዓላማ ጥያቄዎች ሁለት ናቸው፡፡ እነዚህም፡-

1. ቡድናዊ መማር የኢ-አፍፈት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ክሂል ችሎታ ለማጎልበት ያለው አስተዋጽኦ ምንድነው?
2. ቡድናዊ መማር በኢ-አፍፈት ተማሪዎች የማንበብ ተነሳሽነት ላይ ምን አይነት ተጽእኖ ያሳድራል?

ይህ ጥናት የተካሄደው አስቀድሞ ለመግለጽ እንደተሞከረው በኦሮሚያ ክልል በአርሲ ዞን በዶዶታ ወረዳ በዴራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት በ2015 ዓ.ም 9ኛ ክፍል ትምህርታቸውን እየተከታተሉ በሚገኙ ኢ-አፍፈት ተማሪዎች ላይ ነው፡፡ ትምህርት ቤት ከ9ኛ-12ኛ ክፍል ያሉ ተማሪዎችን በማስተማር ላይ የሚገኝ ነው፡፡ ለዚህ ጥናት የተመረጠው የክፍል ደረጃ 4 አፈ-ፈትና 16 ኢ-አፍፈት በድምሩ 20 9ኛ ክፍል ተማሪዎች ውስጥ በመጀመሪያው ፈረቃ ከሚማሩ ኢ-አፍፈት ተማሪዎች መካከል 9ኛሀናለ ክፍልን በቀላል የእጣ ናሙና አመራረጥ ዘዴ በመምረጥ ጥናቱ ተካሂዷል፡፡ ሁለቱ ምድብ ተማሪዎች በየምድባቸው 42 የተመደቡ ሲሆኑ በጥቅሉ 84 ሲሆኑ ምድብ ሀ የሙከራና ለ ደግሞ የቁጥጥር ሆነው ትምህርት ቤቱ እንደ አፍ መፍቻ ቋንቋቸው በመደባቸው ክፍል ትምህርታቸውን በማያቃውስ መልኩ እንዲቀጥሉ ሆኗል፡፡

ለጥናቱ የተመረጡት ተማሪዎች እንዲማሩ የተደረገው ትምህርት ቤቱ ለስረዓተ ትምህርት ማረጋገጫነት እንዲያስተምር በተደረገው ለዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች አማርኛ እንደ ፌደራል ቋንቋ የተዘጋጀውን መጽሃፍ ሲሆን በጥናቱ ለተካተቱት ሁለቱም ቡድን ነው፡፡ በመጽሀፉ በምዕራፍ ስድስት፣ ሰባትና ስምንት የቀረቡ ምንባቦችና አንብቦ የመረዳት መልመጃዎች ለክፍል ውስጥ ልምምድ ተግባራዊ የተደረገ ሲሆን በምዕራፍ ዘጠኝና አስር ላይ የቀረቡት ምንባቦች ተማሪዎቹ

ያልተማሯቸውና ወደፊት ግን የሚማሩት ሆነው ለቅድመና ድህረ ፈተናው መረጃ መሰብሰቢያነት እንዲውሉ ተደርጓል፡፡ እነዚህ ምንባቦች የተመረጡት በተማሪዎቹ ደረጃ የተዘጋጁ በመሆኑ የበለጠ አስተማማኝነት አላቸው የሚለውን አጥኚዋ በማሰቧ ነው፡፡ ለሙከራና ቁጥጥርቡድን ተማሪዎቹ ለክፍል ውስጥ ልምምድ የቀረቡት ምንባቦችና መልመጃዎች ምንም እንኳን አንድ አይነት ቢሆኑም የትምህርቱ አቀራረብ የተለያ ነው፡፡ ማለትም የሙከራ ቡድኑ በቡድናዊ መማር ዘዴ በመታገዝ ሲማሩ የቁጥጥር ቡድኑ ያለ ዘዴው በተለምዷዊ እንዲማሩ ማድረግ ነው፡፡

አስቀድሞ በምዕራፍ ሶስት ለመግለጽ እንደተሞከረው ጥናቱ ሲካሄድ የራሱ ቅደም ተከተላዊ ሂደት ያለው ሲሆን ይህ ሂደትም አጥኚዋ ጥናቷን ለማካሄድ ለጥናቷ አካሄድ ያመቻት ዘንድ በጥናቷ እገዛ ለሚያደርጉላት አካላት የትብብር ጥያቄ አቅርባለች፡፡ ጥያቄው የቀረበላቸው አካልም ጥናቱ በሚካሄድበት ትምህርት ቤት የሚገኙ ርዕሰ መምህራን፣የአማርኛ ቋንቋ መምህራን፣ ተማሪዎች ሲሆኑ አጥኚዋ በመጀመሪያ እነዚህ አካላት ለጥናቱ ለሚየደርጉት እገዛ ፍቃደኛ መሆናቸውን አረጋግጣለች፡፡

ትምህርት ቤቱ ለስረዓተ ትምህርት ማረጋገጫ እንደ ዞኑ የተመረጠ ብቸኛ ትምህረት ቤት በመሆኑ ለስረዓተ ትምህረቱ በተዘጋጀ መማሪያ መጽሀፍ ለማስተማር የተመረጠ ሌላ ትምህርት ቤት እንደ ዞኑ አልተገኘም፡፡በመሆኑም አጥኚዋ ጥናቱን ለማካሄድ የመረጠችው ትምህርት ቤት በ 2015 ዓ.ም በስረዓተ ትምህርቱ አፈጻጸም መሰረት 16 ምድብ ኢ- አፍ ፊት ተማሪዎችንና 4 ምድብ አፍ-ፊት 9ኛ ክፍል ተማሪዎችን ለየብቻ መድቦና ሁለት ቦታ በመክፈል በተለያየ ፈረቃ ለይቶ በማስተማር ላይ የሚገኝ ስለሆነ ለጥናቷ ትክክለኛነትና አስተማማኝነት ለጥናቱ ከተመረጡ ተማሪዎች ተመሳሳይ የክፍል ደረጃና በዚያው የስረዓተ ትምህርት ማረጋገጫ የተዘጋጀውን መማሪያ መጽሀፍ የሚማሩና ጥናቱ ከሚካሄድበት ፈረቃ ተቃራኒ ለሚማሩ ተማሪዎች የፈተናውን አስተማማኝነት አረጋግጣለች፡፡

በማስከተልም ለጥናቱ ለተመረጠው መምህር ትምህርቱ ከመጀመሩ አስቀድሞ ስልጠና ተሰቷል፡፡ ለመምህሩ ስልጠናው የተሰጠው በምዕራፍ ሁለት ላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው የተለያዩ ምሁራን ቡድናዊ መማርን አስመልክቶ የገለጽትን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ነው፡፡ ያውም Dennic፣Exley (1998) & Graffam(2018)፣Burke (2011) እንዲሁም ሌሎች ምሁራን የሰጡትን ሀሳብ መሰረት በማድረግ ለተከታታይ ቀናት ለመምህሩ ስልጠና ተሰቷል፡፡ ስልጠናው ለመምህሩ የተሰጠበት ምክንያት መምህሩ ቡድናዊ መማርን በሚያስተምርበት ጊዜ ለጥናቱ አስተማማኝነት በትክክል መተግበር እንዲችልና የበለጠ ስለቡድናዊ መማር ግንዛቤ እንዲኖረው

ለማድረግ በማሰብ ነው፡፡ ስልጠናው ከተጠናቀቀና ስምምነት ላይ ከተደረሰ በኂላም በአጥኚዋ ቅድመ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተናና የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ ተዘጋጅቶ ከላይ ለመጥቀስ እንደተሞከረው አስቀድሞ በጥናቱለማይካተቱ ፍቃደኛነታቸውን ለገለጹ 40 ተማሪዎች በመምህራኖች እገዛ አንብቦ የመረዳት ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጎ መረጃው ከተሰበሰበ በኂላ በእኩል ክፋይ ዘዴ ስሌት በማስላት አስተማማኝነቱ ተረጋግጧል፡፡ በቀጣዩቹ ቀናትም ተማሪዎቹ ቅድመ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቁን ሞልተዋል፡፡ አንብቦ የማንበብ ተነሳሽነት መጥይቆቹ አስተማማኝነትም በክሮምባኽ አልፋስሌት ተሰልቶ ተረጋግጧል፡፡

የፈተናውና መጠይቁ አስተማማኝነት ከተረጋገጠ በኂላ በጥናቱ ለተካተቱና ለጥናቱ ለተመረጡ 9ኛ ሀናለ ምድብ ተማሪዎች ቅድመ አንብቦ የመረዳት ፈተና እንዲፈተኑ ተደርጓል፡፡ በማስከተልም ከተወሰኑቀናት በኂላ የሙከራ ቡድኑ ቅድመ የማንበብ ተነሳሶት መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል፡፡ ፈተናው በደረጃው መምህር ከታረመና ውጤቱ ከተመዘገበ በኂላ ለሁለቱም ቡድን እኩል እድል በመስጠት በእጣ ናሙና አመራረጥ 9ኛሀየሙከራ ቡድን 9ኛለ የቁጥጥር ቡድን ተደርጎ በጥናቱ እንዲካተቱ ተደርገዋል፡፡

የፈተናው አስተማማኝነት ከተረጋገጠ በኂላ በክለሳ ድርሳኑ ለመጥቀስ እንደተሞከረው ቀጣዩ ተግባር መምህሩ የክፍል ውስጥ ልምምድን ከመጀመሩ በፊት መምህሩ የተሰጠውን ስልጠና መሰረት በማድረግ የ BJHM 2009 ን የቡድን አመሰራራትን እንደ መነሻበማድረግ ሙከራ ቡድኑንቡድን የመመስረት ተግባር ተከናውኗል፡፡ ተማሪዎቹ ቡድን እንዲመሰርቱ ከተደረገ በኂላመምህሩ ትምህርቱን ቀጥሏል፡፡

መምህሩለተማሪዎቹ የሚያስተምረው የክፍል ደረጃ ይመጥናልተብሎ በባለሙያዎች ተዘጋጅተው በ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ ከቀረቡት የትምህርት ይዘቶች መካከል በምዕራፍ ስድስት፣ሰባትና ስምንት ላይ የተሰጡትን ምንባቦችና መልመጃዎች ነው፡፡

ከምዕራፍ ስድስት ጀምሮ ለሁለቱም ቡድኖች በተሰጠው ስልጠና መሰረት ለቡድናዊ ወይም ትብብራዊ መማር ትምህረት የትምህርት ዕቅድ መዘጋጀት እንዳለበት Johnson and Johnson (1999) የተለያዩ ምሁራንን ጠቅሰው የሰጡትን የትምህርት ዕቅድ አዘገጃጀት መሰረት በማድረግ የትምህረት ዕቅድ ተዘጋጅቶ ተማሪዎቹ በመደበኛ ትምህርታቸውን በሚከታተሉበት መደበኛ መማሪያ ክፍል እንዲማሩ ተደርጓል፡፡ አቀማመጣቸውን በተመለከተ የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች በክፍል ውስጥ ስድስት፣አምስት ተማሪዎችን በጋራ በክለሳ ድርሳኑ እንደተገለጸው በማቧደንና

የተለያዩ ቡድናዊ አቀማመጦችን በማስቀመጥ በቡድናዊ መማር ስልት፣የቁጥጥር ቡድኑ ደግሞ በተለምዷዊው ያለ ቡድን ትምህርታቸውን እንዲጀምሩ ተደርጓል።

መምህሩም የክፍል ውስጥ ልምምዱን በመደበኛው ክፍል ሰቷል። በመደበኛው ክፍል እንዲሰጥ የተደረገበት ምክንያት ትምህርት ቤቱ ለስራዓተ ትምህርት ማረጋገጫ የተመረጠ በመሆኑ ተማሪዎቹን በየአፍ መፍቻ ቋንቋቸው መድቦ በማስተማር ላይ የሚገኝ ስለሆነ መደበኛ ትምህረቱን የሚያናጋ ባለመሆኑ ምክንያት ነው።

የክፍል ውስጥ ልምምዱ በተከታታይ ለስድስት ሳምንታት በሳምንት ሁለት ሁለት ክፍለ ጊዜ በየምዕራፉ የቀረቡትን ምንባቦችና መልመጃዎች በአጠቃላይ ለ12 ክፍለ ጊዜ በተከታታይ የክፍል ውስጥ ልምምዱ ተከናውኗል። በክፍል ልምምዱ ሂደትም አጥኚዋ በሁለቱም ቡድኖች ክፍል በመዘዋወር መምህሩ ሲያስተምር ተገቢውን ምልከታ አድርጋለች።

የክፍል ልምምዱ ከተጠናቀቀ በኋላ አንብቦ የመረዳት ፈተናና የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ ተገቢነትናአስተማማኝነት ለማረጋገጥ በደረጃው መምህራን ከተገመገመና አስፈላጊው ማስተካካያ ከተደረገ በኋላ ቀድሞ የፈተናው አስተማማኝነት በተሰጠበት ፈረቃ ፈተናውን እንዲፈተኑና መጠይቁን እንዲሞሉ ተደርጓል።

የአንብቦ መረዳቱና መጠይቁ አስተማማኝነት በቅድመ ፈተናዎቹ አስተማማኝነት ስሌት ተሰልቶ ከተረጋገጠ በኋላ ፈተናውን የሙከራና ቁጥጥር ቡድኖቹ በተመሳሳይ ሰዓት ፍቃደኛ በሆኑ መምህራን አማካይነት ፈተናው ተሰቷል። በቀጣዩ ቀን የሙከራ ቡድኑ የተነሳሽነት መጠይቁን ሞልተዋል። በቀጣዮቹ ጊዜያትምከ42 ሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች መካከል አምስት ተማሪዎችን በመውሰድ ድህረ ልምምድ ቡድን ተኮር ውይይት ከአጥኚዋ ጋር ተካሂዷል።በጥናቱ የተነሱትን ዋና ዋና ጥያቄዎች ምላሽ ለመስጠት በጥናቱ መረጃ መሰብሰቢያመሳሪያዎች የተሰበሰቡትን መረጃዎች በቅደም ተከተል ተተንትነው ቀርበዋል።

ይህ ጥናት ከላይ የተዘረዘሩትን ቅደም ተከተሎች በመከተል ቡድናዊ መማር የኢ-አፍፈት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት ለማጎልበት ያለውን አስተዋጽኦ የሙከራና ቁጥጥር ቡድኖችን በመምረጥና በመመርመር ቡድናዊ መማር ስልት በሙከራ ቡድኑ በኣንብቦ የመረዳት ችሎታና የማንበብ ተነሳሽነት መሻሻሉን በጥናቱ ግኝት መገንዘብ ተችሏል። በመሆኑም ይህ ግኝት የሚያሳየውቡድናዊ መማር ስልት የኢ-አፍ ፈት ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳትና የንባብ ተነሳሽነት ለማጎልበት አስተዋጽኦ ያለው መሆኑን ለማረጋገጥ ተችሏል።

## 5.2. አስተያየት

አጥኚዋ ቡድናዊ መማር አማርኛ ቋንቋ እንደ ሁለተኛ ቋንቋቸው(ኢ-አፍፈት) ለሆኑ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማዳበርና የማንበብ ተነሳሽነትን ለመፍጠር ካለው ጥቅም አኳያ ለወደፊት ለግንዛቤ ይሆን ዘንድ ቀጥሎ የተጠቀሱትን አስተያየቶች ሰታለች፡፡ ቡድናዊ መማር ስልት ለኢ-አፍፈት ተማሪዎች (አማርኛ እንደ ሁለተኛ ቋንቋ) ለሚማሩ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ክሂል ችሎታን ማጎልበትና ለማንበብ ተነሳሽነት መፍጠር መቻሉን የጥናቱ ግኝት አመላክቷል፡፡

- ለመምህራን የበለጠ ግንዛቤያቸው እንዲጎለብት ስለ ቡድናዊ መማር ስልት ስልጠና የሚሰጥበት ሁኔታ ቢመቻች ለቡድናዊ መማር ትኩረት ሰተው ተግባራዊ ለማድረግ ያግዛቸዋል፡፡ ማለትም የቡድናዊ መማርን ምንነትና ጠቀሜታ፣የክፍል ውስጥ ቡድናዊ አቀማመጥ አይነቶችን፣ተማሪዎች በቡድን በሚያነቡበት ጊዜ ወይም አንድን ተግባር በቡድን ሲያከናውኑ ከጓደኞቻቸው የበለጠ መማር የሚችሉ መሆናቸውን፣ከመምህሩ የሚጠበቁ ተግባራትን፣የተማሪዎችን ተግባራት፣ቡድናዊ መማር በተማሪዎች ላይ ስለሚያመጣው ለውጥ የመሳሰሉትን የበለጠ እንዲገነዘቡ ያደርጋል፡፡
- የጥናቱ ግኝት እንዳመላከተው መምህራን አማርኛ ቋንቋ ሁለተኛ ቋንቋቸው የሆኑ ተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ትምህርት ይዘትን በመማር ማስተማር ሂደት ጽንሰ ሀሳብ ለማስገንዘብ ሲባል በራሳቸው ከማንበብ ይልቅ ተማሪዎቹ በቡድን ርስ በርሳቸው እየተጋገዙ እንዲያነቡና በተሻለ የሚያነቡትን እንደ ማሳያነት በመውሰድ እያስነበቡ በማንበብ ደካማ የሆኑ ተማሪዎች ለማንበብ እንዲነሳሱና አንብበው እንዲረዱ ማድረግ ቢችሉ የበለጠ ጠቃሚ ነው፡፡
- መምህራን በመማሪያ መጽሀፉ የቀረቡትን ቡድናዊ ተግባራትን በተመለከተ ለተማሪዎች አንድን ሀሳብ በማቅረብ ብቻ ሰብስቦ ውጤት መስጠት ብቻ ሳይሆን የቡድናዊ መማርን ውጤታማነት አምነው በክፍል ውስጥ ለተማሪዎች የሚሰጡትን ቡድናዊ ተግባራት ተማሪዎችን በተሻለ የሚሰሩ ተማሪዎችን በመለየት ርስ በርሳቸው ተግባራቱን እንዲተገብሩ ቢያደርጉትክሂሎት የበለጠ ይዳብራል፡፡
- አማርኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛ ቋንቋ ለሚማሩ ተማሪዎች የሚዘጋጅ መማሪያ መጽሃፍ ቡድናዊ መማር ስልትን በቂ በሆነ መልኩ በማንኛውም ክህሎት ላይ ተግባራዊ ማድረግ

ቢቻል ተማሪዎቹ አንዳቸው ከሌላው በመማር የበለጠ ክህሎታቸውእየጎለበተና እየተሻሻለ፣ ለተግባራቱም መነሳሳትን እየፈጠረላቸው ለመምጣት ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው፡፡

- ለወደፊት ለኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች የትኛው አንብቦ የመረዳት ስልት ተግባራዊ ቢደረግ ተማሪዎች የማንበብ ክሂል ችሎታቸውን እንደሚያጎለብቱናለማንበብ ተነሳሽነት ሊፈጥርላቸው እንደሚችል ጥናት የሚካሄድ ቢሆን፡፡
- በዚህ ጥናት የተመረመረው ቡድናዊ መማር ምንም ያህል ኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች ርስ በርሳቸውበመተጋገዝ አንብቦ የመረዳት ችሎታቸውን ለማጎልበትና የማንበብ ተነሳሽነትን ለመፍጠር ከፍተኛ ተቀሜታ ያለው ቢሆንም ከሌሎች ለየትያለ ስልት ነው ለማለት አይቻልም፡፡ ሆኖም ሌሎች ስልቶችንም መርምሮ በመረጃ ማረጋገጥ ተገቢ ነው፡፡
- በዚህ ጥናት ግኝት ምንም እንኳን ቡድናዊ መማር ለኢ-አፍ ፈት ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበትና የንባብ ተነሳሽነትን ለመፍጠር ከፍተኛ ጥቅም ያለው ቢሆንም ለአፍ ፈት ተማሪዎች ጠቀሜታ የለውም ማለት አይቻልም፡፡በመሆኑም ለወደፊት ጥናት የሚያካሂዱ አካላት በዚህ ላይ መረጃ በመሰብሰብ መመርመር ተገቢ ነው፡፡
- አማርኛ ቋንቋን በማስተማር ሂደት ተማሪዎችን በቡድናዊ መማር ለማስተማር የተመደበው ክፍለ ጊዜ በቂ አይደለም፡፡ ነገር ግን ተማሪዎችን ርስ በርሳቸው በሚገባ እየተወያዩ አንዳቸው ከሌላው እንዲማማሩ ለማድረግና በቂ በሆነ መልኩ ለማለማመድ እንዲሁም ለውጥ እንዲያመጡ የክፍለ ጊዜ ማስተካከያ ቢደረግ የተሻለ ነው፡፡

# ዋቢ ጽሑፎች

መኮንን ናና፡፡ (2000)፡፡ በኦሮምኛ አፋቸውን የፈቱ የስምንተኛ ክፍል ተማሪዎች በአ ማርኛ አንብቦ የመረዳት ችሎታ ግምገማ" አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ድህረ ምረቃ ትምርት መርሀ ግብር ኤም ኤ ዲግሪ ማሟያነት የቀረበ ጥናት (ያልታተመ)

ማረው አለሙ፡፡ (1998)፡፡ የአማርኛ ቋንቋ ማስተማሪያ ዘዴ፡፡ባህር ዳር፡፡ብርሃንና ሰላም

ማተሚያ ድርጅት፡፡

ማስትዋል ውብቱ፡፡ (1989)፡፡ የከፍተኛ ሁለትኛ ደረጃ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳችሎታ፡፡

ለማስተርስ ቴስስ ማሟያ የቀረበ ጹሁፍ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ምስጋኑ ጉልማ፡፡ (2011)፡፡ ጥልቅ ማንበብ (Reading Critcal):: አዲስአበባ፡፡ ሱቢ

ማተሚያ ድርጅት፡፡

ሰለሞን ሀልፎም፡፡ (1990):: በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በሚሰጠው የቋንቋ የንባብ

ክሂልን እንዴት ማዳበር ይቻላል የቋንቋ የንባብ ክሂልን እንዴት ማዳበር ይቻላል?

"መጽሔት ትምህርት፡፡ በትምህርት ሚኒስቴር የህዝብ ግንኙነት፡፡ 4፣6፡

በላይነሽ ደነቀ፡፡ (2010)፡፡ የቃላትመማር ብለሀቶችን በግልጽ ማሰልጠን ለሁለተኛ

ቋንቋ ተማሪዎች የቃላት ችሎታ መዳበር ያለው አስተዋጽኦ፤ጾታተኮርሙከራዊ

ጥናት (በ9ኛ ክፍል ኦሮምኛ ቋንቋ አፍ-ፈት ተማሪዎች) ተተኳሪነት፡፡ አዲስአበባ

ዩንቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

በረከት ሁሴን፡፡ (2010)፡፡ በሰገን አከባቢ ሕዝቦች ዞን በሰገን ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ

ትምህርት ቤት በአማርኛ ኢ-አፍፈት የሆኑ የ9ኛ ክፈል ተማሪዎች አንብቦ

የመረዳት ችሎታና የንባብ ፍጥነት ተዛምዶ፡፡ ለማስተርስ ማሟያ የቀረበ ጥናት ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

በድሉ ዋቅጅራ፡፡ (1996)፡፡በስነ-ጽሁፋቋንቋንማስተማር፡፡ ባህርዳር ዩኒቨርሲቲ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ ንግድ ማተሚያ ድርጅት፡፡

ብርሃን ስራጅ፡፡ (2003)፡፡ የንባብ ልምምድና የአማርኛ ቋንቋ ትምህርት አንብቦ የመረዳት ችሎታ በውቅርና በነጋሽና አጉላዕ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች ናሙናነት፡፡ ለማስተርስ ማሟያ የቀረበ ጥናት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ተስፋ አከለ፡፡ (2010)፡፡ ትብብራዊ መማር የተማሪዎችን አቀላጥፎ የማንበብና አንብቦ የመረዳት ችሎታ ለማሳደግ ያለው ሚና፡፡ (አክሱም ከተማ ውስጥ አፋቸውን በትግርኛ ቋንቋ በፈቱና አማርኛ ቋንቋን እንደ ሁለተኛነት የሚማሩ (የ7ኛ ክፍል ተማሪዎች ተተኳሪነት)፡፡ ለዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናታዊ ፅሁፍ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

አለም እሸቱ፡፡ (1997)፡፡ መሰረታዊ የምርምርና የዘገባ አፃፃፍ፡፡ አዲስ አበባ፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨሲቲ፡፡ ኮሜርሺያል ኢንተርፕራይስ ማተሚያ ድርጅት፡፡

እመቤት እሸቱ፡፡ (2011)፡፡ አንብቦ የመረዳትና የመጻፍ ክሂል ቅንጅታዊ የይዘት አቀራረብ ትንተና፡፡ ለማስተርስ ማሟያ የቀረበ ጥናት፡፡ ደብረብረሃን ዩኒቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡፡

ዑመር ዳውድ፡፡ (2000)፡፡ የሆሳዕና መምህራን ትምህርት ኮሌጅ የመሰረታ አማርኛ ኮርስ መምህራን የንዑስ ቡድን ማስተማር ዘዴ አተገባበር ጥናት፡፡ ለአማርኛ ማስተማር (TeAm)ኤም.ኤ.ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የተሰናዳ፡፡ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ፡፡ (ያልታተመ)፡

ጌታቸው እንዳላማው፡፡ (2011)፡፡ ቋንቋና ስነልሳን፡፡ አዲስአበባ፡፡ 251116401216፡፡

የኔ ሰው ደሴ፡፡ (1990)፡፡ አበኦሮምኛ ቋንቋ አፋቸውን የፈቱ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ አንብቦ የመረዳትክሂላቸ ማዳበር ተራክቧዊ መካክስ የንባብ ክሂል ማስተማርያ ሞዴል በክፍል

ውስጥ ተጠቅሞ ማስተማር ያለው አስተዋፆ፡፡ አዱስ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ድህረ መምረቃ ትምርት መርሀ ግብር ኤም ኤ ዲግሪ በከፊል ማሟያነት የቀረበ ጥናት፡፡

(ያልታተመ)፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል መዝገበ ቃላት፡፡ (2001) አዲስ አበባ፡፡ አዲስ

አበባ ዩንቨርሲቲ፡፡

ያለው እንዳወቀ፡፡ (2009)፡: የምርምር መሰረታዊ መርሆዎች እና አተገባበር፡፡ አሊፍ

አታሚዎች፡፡፡

ደረጀ ገብሬ፡፡ (2013)፡፡ የማንበብ ክህል ማበልጸጊያ፡፡ አዲስ አበባ ዩንቨርሲቲ፡፡ አፍሪካ ማተሚያ፡፡

Agnihotri, (2018).Small Group Teaching and Learning. Journale Home Page; http://www.aks publication.com/JJmu

Alderson, J. C.(2000).Assessing Reading.Cambridge,UK ; Cambrid University Prss.

Anderson,L. W.&Kratwohl, DR.(2001). Ataxonomy fore Learnig teaching and Assessemnte: Arevision of Blooms Txonomy of educational objectives. New York: Addison Wesley.

Barber, & Klauda, (2019). How Reading Motivation and Engagemente Enable Reading Achievemnte Policy Implications.

Behailu, (2010). Grad 10 and 11 studentes Attitude and Motivation to Words Local Language in education ; The case of bishoftu Secondary school.Addis ababa University. School of Graduate Studies, Adis ababa.(un published).

Beebe, S. A. and Masterson,J.T.(2003).Communicating in Small groups. Pearson Educaton Inc.Boston:Massachusetts.

BJHM,(2009).small group. British Journal of hospital Medicine.vol 70.No 11.

Bloom, B. S. (1956). Taxonomy of educationale objectives, Hand book I;Thecognitive doman. New York: David Mckay.

Brook field, S. D. Preskill, S. (2005). Discussion as a way of teaching. SanFrancisco: Jossey Bass.

Boruvkova and Emanovsky,(2016).small Group Learning Methods and Thire Effect On Learners Relation Ships.Palacky University Olomouc; Czech Republic.vol 70.

Brown, A. L. (1992). Theoretical and Methodologicale Challenges in Creating complex Interventions in class room settings. University of California .Berkeley. Taylor & Francis, Ltd.

Brown, G.(2006).Explaning. In; Hargie O,Hand book of communication skill. london Routledge. PP195-228.

Brown, H.D.(1994). Principles and Practices of Language Learning and TeachingEnglesh word cliffs, N. J. Prentice Hall.

Brown,G. Atkins, M.(1988). Effective Teaching in higher education London: Routledge.

Bligh, D. (2000). What is The Point In discussion? Exeter ,UK: Intellect Books.

Burke,(2011).Group work.How to Use Group Effectively.Journal of effective Teaching. Vol.11. NO.2,87-95.

Cohen, E. G. (1994). Restructuring the class room; condition for Productive Smallgroups. Review of Educational Research , 64(1), 1-35.

Davies, G.B.(1993). ‘Collaborative Learnig ; Group Work and Study Team’’ Teaching Berkelay.Edu/ bgd/ collaborative.

David, E. Gunderson,C. P. C. &Jennifer D.Moore, (2008).Group Learning Pedagogy and Group Selection.International Journal of construction

Education and Research, 4;1,34-35.

Dennick, R. G.&Exley, K.(1998). Teaching and Learnig in Groups and teams 6;111-15

Dewey, J. (1931). The way out of educational Confusion.Cambrige, MA: Harvard University.prss.

Deutsch, M.(1949). Anexperimentale Study of the effects of cooperation and completion up on group process, Human Relation, 2,199-231.

Dickson, D. Hargie O.(2004). Skilled interpersonal communication .London: psychology.press.

Dornyei, Z. and Ushioda,(2011). Teaching and Researching Motivation.Britsh Library.log man Britain.

Donyei, Z. (2001).Teaching and Researching Motivation.HarlowLongman. Acquisition.Honolulu, Hl; University of Hawaii Prss.

Edmunds, S. Brown, G. (2010). Effective Small Group Learning. Amee guide no ;48.Univrsity of Westminster,u. k. Univrsity of Notting UK.

Fisher, B.A.,&Ellis, D.G. (1990). Small group decision making. New York; McGraw Hill, Publishing Co.

Gaudet, A. D. and Ramer, L. M.etal,(2010).small group Learnig in un upper Leve university bio class enhances academic performance and student attitudes to wards group work. Plos one. 5;el 5821.

Gibbons, P. (2002). Scaffolding Language, Scaffolding Learning. Teaching SecondLanguage Learners in the Mainstream Classroom Portsmouth:Heinemann.

Girma Gezehegn. (2003). "In-Service English LanguageTeacherPerception of TheFactorthat Influence The Implement of Group Work Activity IELT Classes."TheJournal of Ethiopian Education, Vol. XXII No 2

Pp103-1.

Graffam, B. (2007).Active Learnig in education;Strategies for Beginni implementation. University of South Florida College of Medicine. U.S.A.

Grellet, F.(1981).DevelopingReading Skills Cambridge:Cambridge Universi Press.

Grellet, F.(1986).New Developments in Teaching Reading Comprehesio Skill ToEf Lerners. New York: Cambridge University Press.

Guthrie, J. T.& Wigfield, A. (2000). Engagement and Motivation in Reading. I.M.L.Kamil,P.B.Mosenthal,P.D.PearsonandR.Barr.(Eds.). Handboo OfReading Research. (Vol. III,pp. 403-22). Mahwah, NJ: Lawrence ErlbaumAssociates.

Hatti, J. Timperley, H. (2007). The Power of Feed back. Rev Educ Res. 77: 8 112.

Heaton, J. B.(1975). Writing Language Tests. Apractical Guide for Teachers OfEnglishas Second Language Foreign Language.London; Log man.

Istifci, I.(2009). Lexical inferencing Strategies of Turkish EFL learners. Jornal of Language & Linguistic studies,s. (1). 97-109.

Hiilya, Kiiciikoglu, (2012).Improving Reading Skill through Effective readingstrategies.Hacettepe University, Ankara, Turkey.Elsvier Ltd.

Jacobs, G.M.(2006). Issues in Implementing Cooperative Learning.In MC Cafferty, S.G Jacob, G.M. and Idding, A.S.D(eds Cooperative Learning and Second LanguadgeTeaching,Cambridg University press.

Johnson, D.W, Johnson,R. T.S.& Holubec, E.J. (1994). Cooperative Learning In Theclass room.Alexandria,V.A. Association for supervision and CurriculumDevelopment.

Kalayci, S.&Humiston,K.R.(2015). Students Attitudes Towards CollaborativeToolsInAvirtual Learning Environment. Educationale Process;Inteternational Journal, 4 (1-2), 71-86.

Kitchen, M.(2012).Facilitating Small groups; how to encourage student learnig.9;3-8

Krashen, Stehpen,(1987). Principles and practice in Secend Language AcquisitionNewYork Prentice Hall Internatinal.Londen, M. polzer, Jtranactive Memory and feed back processe. Human Resource DevelopmentReview,4 (2); 114-135..T.andomoregie, Interpersonale Congruence

Meo, S. A. (2013). Basic Steps in establishing effective small group teaching sessions in schools. Pak J med .29; 1071-6.

Mikulecky, B. S. andJeffries,L. (2004). More reading Power:Reading for Pleasure ,comprehension Skill, thinking skills, reading foaster ($2^{nd}$ ed.) NewYork; Pearson Education.

Nelson (1984). G.L. (1984).“ Readinig Astundet Center a Approach” Englis Teaching forum,2214.2-4

Nuttal, C.(1982).TeachingReading Skills in a ForeignLanguage Practical Language Teaching. London.Edinburgh.

Nuttall, C(1996). Teaching Reading Skill In Aeoreign Language. Oxfod; Mac Millan Publishers.

O’Mellaey, J. M., and Chamot, A. U. (1900). LearningStrategies in Second Language Acquisition. Cambridge: Cambridge University Press.

Oxford, R. L. (1990). Languadge Lerning Strategies. What Every Teacher shouldKnow. New York; New Bury House.

Putnam, J. (19 97). Cooperative Learning In Diverse Classroom. New Jersey;

Prentice. Hall,Inc.

Richards, et .al, (1985).Longman Dictionory of Applied Linguistics.Essex; Longman, Group Limited.

Seid Mohammde.(2012). Effectsofcooperative Learnig on Reading comprehenshnAchieviment in EFL and social skill of grade 10 students.(unpublisheddoctorial dissertation). Addis Ababa University,school of graduate.studies, Addis Ababa.(un Published)

Silbersteins,S.(1994). Techniqueand Resouces in Teaching Reading.ox ford University, prss.

Slavin, K.E. (2011). Instruction based on cooperative Learning.In R.Mayer (Ed.),Hand book of research on Learnig and instruction. London: Tay lorand Francis.

Slavin, K. E.(1983). Cooperative Learnig.New York; Long man.Prss.

Springer, L. stanne, M. E. &Donovan, S.S.(1999). Effects of small group learning on undergraduates in science, maths, engineering, & technologyAmeta-analysis. Review of Educationnal Research,69 (1)21-25.St. Marys University College; (2006).Reading & Study Skills.

Sharan , S. (1990). The Group Inevestigation Approach to Cooperative Learning ;Theoretical Foundation In Brubacher, etal (Eds). Perspective On SmallGroup Learning. (pp. 29-39)

Ontario;Rubicon Publishing Inc.

Vygotsky, L. S. (19 78). Mind in Society.The Developmente of Higher Psychological Process.Cambridge ; Harvard Univers Watt M,

Vygotsky, L. S. & Piaget, (1988).Human Development. Harvard University, Cambridge, mass. , USA. Karger.

Wigfield A. and Guthrite, J. ( 1997). Relation of Children's Motivation for reading to theamount and breadth of their reading. Journal of Educational Pschology,89,437-470

# አባሪዎች

## አባሪ ሀ

## ቅድመ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና አስተማማኝነት በእኩል ክፋይ (split half) ስሌት ለማስላትየተሰበሰቡ ውጤቶች

| ቁጥር | በተጋማሽ ጎዶሎ ቁጥር የተገኙ ትክክለኛ መልሶች | በተጋማሽ ሙሉ ቁጥር የተገኙ ትክክለኛ መልሶች |
|---|---|---|
| 1 | 4 | 6 |
| 2 | 6 | 5 |
| 3 | 5 | 6 |
| 4 | 5 | 7 |
| 5 | 8 | 6 |
| 6 | 6 | 7 |
| 7 | 7 | 8 |
| 8 | 7 | 9 |
| 9 | 9 | 8 |
| 10 | 8 | 10 |
| 11 | 5 | 7 |
| 12 | 5 | 4 |
| 13 | 4 | 6 |
| 14 | 6 | 8 |
| 15 | 6 | 5 |
| 16 | 7 | 6 |
| 17 | 8 | 7 |
| 18 | 6 | 5 |
| 19 | 7 | 9 |
| 20 | 5 | 4 |

| | | |
|---|---|---|
| 21 | 8 | 7 |
| 22 | 9 | 9 |
| 23 | 8 | 9 |
| 24 | 7 | 7 |
| 25 | 6 | 6 |
| 26 | 6 | 5 |
| 27 | 6 | 7 |
| 28 | 8 | 7 |
| 29 | 8 | 8 |
| 30 | 7 | 8 |
| 31 | 7 | 8 |
| 32 | 7 | 7 |
| 33 | 6 | 7 |
| 34 | 7 | 8 |
| 35 | 8 | 7 |
| 36 | 8 | 7 |
| 37 | 6 | 6 |
| 38 | 7 | 6 |
| 39 | 8 | 8 |
| 40 | 5 | 5 |

# አባሪ ለ

## መጠይቅ አንድ የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ አስተማማኝነት በክሮንባሽ አልፋ (cronbach Alpha) ስሌት

| የተማሪ ተ.ቁ | ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 1 | 3 | 4 | 1 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 1 | 3 | 1 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 4 |
| 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 1 | 2 | 1 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 4 | 1 | 3 |
| 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 1 | 4 | 3 | 2 | 1 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 |
| 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 1 | 4 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 |
| 5 | 1 | 3 | 1 | 3 | 3 | 1 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 |
| 6 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 |
| 7 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 2 | 4 | 3 | 1 | 3 | 4 | 1 | 3 | 3 | 3 | 4 | 1 | 4 | 2 | 2 |
| 8 | 3 | 3 | 2 | 1 | 3 | 2 | 2 | 1 | 2 | 3 | 1 | 3 | 2 | 1 | 3 | 3 | 3 | 1 | 2 | 3 |
| 9 | 4 | 2 | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 2 | 1 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 |
| 10 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 1 | 3 | 1 | 3 | 1 | 1 | 1 | 2 | 2 | 4 | 2 | 1 |
| 11 | 1 | 1 | 2 | 4 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 |
| 12 | 4 | 2 | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 4 | 2 | 4 | 2 | 1 |
| 13 | 4 | 4 | 1 | 4 | 3 | 1 | 4 | 2 | 2 | 2 | 4 | 1 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 |
| 14 | 3 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 |
| 15 | 2 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 | 1 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 |
| 16 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 3 | 2 | 1 | 4 |
| 17 | 3 | 3 | 1 | 4 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 1 | 2 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 |
| 18 | 4 | 3 | 1 | 4 | 2 | 4 | 3 | 2 | 4 | 2 | 1 | 1 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 2 |
| 19 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 |
| 20 | 1 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 4 |

## አባሪ ሐ

## ለ9ኛ ክፍል ኢ-አፍፊት ተማሪዎች የቀረበ ቅድመ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና፡፡

# አዲስአበባዩኒቨርሲቲ

# የሂዩማኒቲስት፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን

# ኮሌጅ

# የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎርክፍለ ትምህርት ክፍል

# የድህረ- ምረቃ መርሐ ግብር

ተማሪዎች፡-የዚህ መጠይቅ ዋና አላማው በክፍል ውስጥ በቡድን ተከፋፍሎ የመማር ዘዴ የኢ-አፍ ፊት ተማሪዎችን የማንባብ ተነሳሽነት እና አንብቦ የመረዳት ክሂል ችሎታን ለማጎልበት ያለውን ጠቀሜታ በሚል ርዕስ ጥናት ለሚደረግ በቂ መረጃ ለማግኘት ነው፡፡ ውድ ተማሪዎች፣ አጥኚዋ ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከረችው ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ይሆን ዘንድ ጥናት ለማካሄድ ፈልጋለች፡፡ በመሆኑም ቡድናዊ መማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበትና የንባብ ተነሳሽነትን ለመፍጠር ያለውን ጠቀሜታ በሚል የጥናት ርዕስ ለመመርመር አስባለች፡፡ ሆኖም መረጃ መሰብሰብ ተገቢ ሲሆን ይህን መረጃ ስትሞሉ መረጃው ለዚህ ጥናት ብቻ የሚያገለግልና በናንተ ላይ ምንም ተጽዕኖ የሌለው እንዲሁም ምሥጢራዊነቱ የተጠበቀ መሆኑን ልትገልጽላችሁ ትወዳለች፡፡ መጠይቁ 20 ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን ለያንዳንዱ ጥያቄ የራሳችሁን ሀሳብ ብቻ ሊያሳዩ የሚችሉትን መልሶች እንድትመልሱ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡
ምስጋናዬም ከልብ ነው፡፡

የተፈቀደው ሰዓት 1፡30

አጠቃላይ መመሪያ

ውድ ተማሪዎች፣ ይህ ፈተና አንብቦ የመረዳት ፈተና ነው፡፡ ፈተናው አንብቦ የመረዳትን ችሎታ መለካት ሲሆን ይህንን ምንባብ አንብባችሁ በምንባቡ መሰረት ለተጠየቃችሁት ጥያቄ በሙሉ ምላሽ እንድትሰጡ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

*እናቲቱ*

*ፀጥታ ባረበበት ጎጆ ውስጥ ሁለት ነፍሳት ተፋጥጠው ነበር፡፡ፀጥታው ድንገት ተገሠሠ፡፡ "...ሶስትመቶ አምሣ ብር ባለማግኘትሽ አይንሽ ሊጠፋ ነው!*

*"ይሆናል!*

*"...ለዚህ ሁሉ ተጠያቂው ደመኛሽ የምትን ሰፈ ሰፊለት ልጅሽ ነው!"*

*"በመድኃኒ ዓለም ይዤሻለሁ ልጄ! ወንድምሽ በሌለበት አታሳቅቂው!...እንዲያው*

*በመድኃኒ...."*

*"ኤድያ!...ምነው በማህጸንሽውስጥ ውሃ ሆኖበቀረ!...የሱወንድምነትባፍንጫዬ ይውጣ...ይሄ...*

*ይሄ ...ጭንጋፍ...!"*

*"በ...ፈጠረሽ!"*

*"እሺ አሁን አንቺ ከየት ታመጫለሽ?""...ከእኔ የበለጠ ተንከባከብሽ አሳደግሽው!...አስተማርሽው!...እኔየሱን ጥብቆ እንዳጥብ ለሱ አሻሮእንድቆላ ፈረድሽብኝ...እናምየመጨረሻው ዕጣ ፈንታዬ አመድ ውስጥመገኘት ሆነ...እሱግን ተምሮትልቅቦታደረሰ...መማሩ ግን ለእናቱ የሚሆን ርኅራሄ አልፈጠረለትም...ይኸው ዓይንሽን ስትታመሚእንኳ እግዜር ይማርሽ መች አለሽ?!"*

*"እሱሥ ግድ የለም! አንዴ አምጾብሻል!...እኔአጠገብሽ ያለሁት እድለ ቢስ እንኳ ልታደግሽ አቅምአጣሁ!....ምን ላርግ!..ያንድ መናኛ መሥሪያ ቤት የፅዳት ሠራተኛ!..*

*"እንደድሮው 'ተበደሪ' ብልሽ አሻፈረኝ አልሽ!*

*"እንደምን ሠንብታችኋል!"*

*"ዘሀር ምስጌን ደህና ሰንብተዋል?"*

*"....ተሻለሽ?"*

*"ደህና ነኝ!"*

*"ለመሆኑ ይሄ ልጅ ይደውላል?"*

*"አዎ ይደውላል!"*

*ልጂቱ የወንድሟን ፎቶ በልቧ ረገመች።*

*"ገንዘብስ እየላከ ነው?"*

*"አዎ ይልካል!" እናቲቱ መለሠች።*

*"ታዲያ በወር ሁለት መቶ ባውንድ እየዛቀ ሽራፊ ሣንቲም ብቻ መወርወር ዋጋየለውም! ስትታመሚም መታከሚያ ገንዘብ ዛቅ አድርጎ መላክ ነበረበት።ልጅ የዚህ ጊዜ ያልሆነ ለመቼሊሆንነው?...ውነቴንነው!...እኔወን ድሜነው እንዲህ በስተርጅና እሚያቀማጥለኝ...መታከሚያ መላክ ነበረበት" አሉ የቦርሣቸውን አፍ እያሠፉ።*

*"ልኮልኛልኮ!"መለሰች እናቲቱ*

*"ለመታከሚያ የላከው ብር ትናንት ደረሰኝ...*

*እንዴት ያለ የተባረከ ልጅ መሠሎት! የኔ ነገር አያስችለውም መቼም!..."*

*"ጎሽ...ስንት ላከ ?"*

*"የሚበቃኝን ያህል ልኮልኛል!"ፈገግታዋ ግን ለነፋስ እንደተጋለጠ የጧፍ ብርሃን ዕድሜ አልነበረውም።"በይ እንግዲህ ታከሚው!...ጊዜ ልትሰጭው አይገባም።ተሰናብተው ወጡ።*

*በሩን አልፈው ሲሰወሩ እናቲቱ "እፎይ!..."አለች። በህመሟ ውስጥ ደስታ ተሰማት። የልጅዋ ክርስትናአባት ወደ ሀዘን ቤት እንደሚሄዱ ነግረዋታል።እዚያ ሄደው ስለችሮታቸው ለሰፈርተኛው ሁሉያወራሉ። ችሮታው ከደረሳቸው ያጡ የነጡ ሰዎች መካከል የሷ ስም እንደማይኖር ርግጠኛ ሆናለች። ስለዚህም የልጇ ስም በክፉ አይነሣም። ፈጽሞ!*

*(በዕውቀቱ ስዩም፤ እናቲቱ (1994፤ 66-67) ብሌን መጽሄት ለፈተና እንዲያመች*

*ተደርጎ የተወሰደ)*

**መመሪያ አንድ፡-የሚከተሉትን ጥያቄዎች  በምንባቡ መሰረት“ትክክል” ከሆኑ እውነት “ስህተት “የሆኑትን ደግሞ ሀሰት በማለት በባዶ ቦታላይ መልስ ስጥ/ ስጪ ፡፡**

1.በደሳሳ ጎጆ ፀጥታው ያረበበው እናትና ልጅ ደስተኛ ስለሆኑ ነው፡፡

2.አናቲቱ የልጃቸውን ምስጢር አውጥተው መናግር ይፈልጋሉ፡፡

3.ልጅቱ ከወንድሟ ጋር ቅሬታ የፈጠረቸው እናቲቱን ስላሳከማቸው ነው፡፡

4.የልጅቱ ፊት እንደ እስስት ቆዳ የተቀያረው እናቲቱ በመዋሸታቸው ምክንያት ነው፡፡

**መመሪያ ሁለት፡- በ“ሀ” ስር የተዘረዘሩት ቃላትና ሀረጋት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡ በምንባቡ ያላቸውን አገባባዊ ፍቺ ከ “ለ” ረድፍ ከቀርቡት ውስጥ በመፈለግአዛምዱ፡፡**

| “ሀ” | “ ለ” |
|---|---|
| 6. ተገሰሰ | ሀ.ይቅርብኝ |
| 7. ማመጽ | ለ.ተገፈፈ |
| 8. ባፍንጫዬ ይውጣ | ሐ.እንቢተኛ |
| 9. መቀያየር | መ. መንከባከብ |
| 10. ማቀማጠል | ሠ. መለዋወጥ |
| 11. ችሮታ | ረ. ስጦታ |
| 12. መታደግ | ሰ. ማትረፍ |

**መመሪያ ሶስት፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ፡፡**

13. ምነው በመሀጸነሽ ውሃ ሆኖ በቀረ ሲል፡- ሀ. እንደ ውሃ በፈሰሰ ለ. ውሃ በሆነ

ሐ. ከንቱ በሆነ  መ. ባደገ

14.ለዚህ ሁሉ ተጠያቂ ደመኛሽ የምትንሰፈሰፊለት ልጅሽ ነው፡፡የተሰመረበት ቃል

ፍቺ፡- ሀ. ወዳጅሽ ለ. ዘመድሽ ሐ. ልጅሽ መ. ጠላትሽ

15. ልጅቱ ዝቅተኛ ኑሮ እንድትኖር ያደረጋት ምክንያት ምንድነው?

ሀ. ከወንድሟ ጋር እኩል ስለሆኑ ለ. ቤተሰብ ልጆችን በእኩል ስለማያይ

ሐ.ቤተሰብ ታላቅን ስለሚያከበር መ. ሁሉም

16. ልጅቱ እናቲቱን መታደግ ያልቻለችው ለምንድነው? ሀ.ጉልበት ስለሌላት ለ. በቂ

ጉልበት ስላላት ሐ. ገንዘብ ስለሌላት መ. እናቷን ማገዝ ስለማትፈልግ

17. እናቲቱ እንግዳውን ሸኝተው ሲያበቁ እፎይ…ያሉት ለምንድነው?

ሀ. የልጃቸው ገበና አለመውጣቱን ሲሰሙ ሐ. በእንግዳው መሄድ ስለተደሰቱ

ለ. ልጃቸው ስለማያግዛቸው መከፋታቸ መ.ሁሉም

18. ልጅቱ የወንድሟን ፎቶ በግድግዳ ላይ በመመልከት የረገመችው ለምንድነው?

ሀ.እናቱን ስለሚረዳ ለ. እናቱን ስለጠላቸው ሐ. እናቱን ስለሚወዳቸው መ.

እናቱን ማገዝ ስላቃተው

***መመሪያ አራት፡- ከዚህ ቀጥሎ የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰርትባዶቦታውን አሟልታችሁ ጻፉ፡፡***

19. ወደ እናቲቱ ቤት ጎራ ያለውነው፡፡

20. ልጁ ከሁለት አመት በፊት በተመረቀ፡፡

## አባሪ መ

### ለ9ኛ ክፍል ኢ-አፍፊት ሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ቅድመ የማንበብ ተነሳሽነትን በሚመለከት መረጃ ለማግኘት የቀረበ የጹሁፍ መጠይቅ

# አዲስአበባዩኒቨርሲቲ

# የሂዩማኒቲስት፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን

# ኮሌጅ

# የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎርክፍለ ትምህርት ክፍል

## የድህረ- ምረቃ መርሐ ግብር

ተማሪዎች፡-የዚህ መጠይቅ ዋና አላማው በክፍል ውስጥ በቡድን ተከፋፍሎ የመማር ዘዴ የኢ-አፍ ፊት ተማሪዎችን የማንባብ ተነሳሽነት እና አንብቦ የመረዳት ክሂል ችሎታን ለማጎልበት ያለውን ጠቀሜታ በሚል ርዕስ ጥናት ለሚደረግ በቂ መረጃ ለማግኘት ነው፡፡ ውድ ተማሪዎች፣ አጥኚዋ ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከረችው ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ይሆን ዘንድ ጥናት ለማካሄድ ፈልጋለች፡፡ በመሆኑም ቡድናዊ መማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበትና የንባብ ተነሳሽነትን ለመፍጠር ያለውን ጠቀሜታ በሚል የጥናት ርዕስ ለመመርመር አስባለች፡፡ ሆኖም መረጃ መሰብሰብ ተገቢ ሲሆን ይህን መረጃ ስትሞሉ መረጃው ለዚህ ጥናት ብቻ የሚያገለግልና በናንተ ላይ ምንም ተጽዕኖ የሌለው እንዲሁም ምሥጢራዊነቱ የተጠበቀ መሆኑን ልትገልጽላችሁ ትወዳለች፡፡ መጠይቁ 16 ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን ለያንዳንዱ ጥያቄ የራሳችሁን ሀሳብ ብቻ ሊያሳዩ የሚችሉትን መልሶች እንድትመልሱ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡
ምስጋናዬም ከልብ ነው፡፡

አጠቃላይ መመሪያ

1. መጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግ፡፡

2. የጹሑፍ መጠይቁን በቡድን ተወያቶ መመለስ አያስፈልግም፡፡

3. ቀጥሎ ለተጠየቁት መረጃዎች ምላሽ ሊሆን ይችላል ብላችሁ ያሰባችሁትን በባዶ

ስፍራው ሙላ/ሙዪ። ውድ ተማሪዎች፣ መርሃ ትምህርትን መሰረት አድርጎ በክፍል ደረጃችሁ ተዘጋጅቶ በመማሪያ መጻህፋችሁ የቀረበላችሁን የማንብቦ ትምህርት ይዘት ለማንበብ ያላችሁን ተነሳሶት በተመለከተ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከዚህ በታች በተሰጡት መገለጫ ቁጥሮች አማካይነት በጥያቄዎቹ ፊት ለፊት ላይ የ X ምልክት አስቀምጡ።

1. በጣም እስማማለሁ

2.እስማማለሁ

3. አልስማማም

4.ፈፅሞ አልስማማም

| ተ.ቁ | የመጠይቁ ዝርዝር ነጥቦች | 1 | 2 | 3 | 4 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በቡድን መማር የማንበብ ትምህርት ይዘትንለመማር ያነሳሳኛል። | | | | |
| 2 | የማንበብ ትምህረት ይዘት ከቡድን አባላት ኣንዱ ሲያነብ ጓደኞቼን በማየት ለማንበብ እነሳሳለሁ። | | | | |
| 3 | በማንበብ ትምህርት ይዘት ከጓደኞቼ ጋር በመወያየት በቡድን ባነብ ደስተኛ ነኝ። | | | | |
| 4 | መምህሬ የማንበብ ትምህርት ይዘትን ሲያስተምሩ የከበደኝን ሀሳብ የቡድን አባሉ እንዲያግዙኝ ካደረጉ ለማንበብ እዘጋጃለሁ። | | | | |
| 5 | የምንባቡን ሀሳብ አንብቦ ለመረዳት ስለምቸገር በተሸለ ከሚያነቡ ተማሪዎች ጋር በቡድን ማንበብ ለማንበብ ያነሳሳኛል። | | | | |
| 6 | የምንባቡን ረዕሰ ጉዳይ ተመልክቼ ከጓደኞቼጋር በመወያየት ጹሁፉ ስለምን እንደሚገልጽ መናገር ለንባብ ያነሳሳኛል። | | | | |
| 7 | ከምንባቡ የሚወጡ ቃላትን በቡድን ከተወያየሁ በኂላ ምለሽ ለመስጠት እነሳሳለሁ። | | | | |
| 8 | ምንባብን በቡድን እየተወያየሁ ካነበብኩየምንባቡን ጽንሰ ሀሳብ በቀላሉ እገነዘባለሁ። | | | | |
| 9 | የማንበብ ትምህርት ይዘትን በግል ከማንበብ ይልቅ በቡድን ማንበብለማንበብ የበለጠ ያነሳሳኛል። | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 10 | የአንድን ጽሁፍ ሀሳብ መልዕክት በሚገባ ለመገንዘብ በቡድንእየተወያየን ማንበብ ለማንበብ ይስበኛል፡፡ | | | | |
| 11 | በማንበብ ትምህርት መምህሬ ያልገባኝን ሀሳብ ጓደኞቼን እንድጠይቅ ሲያበረታቱኝ ለማንበብ እነሳሳለሁ፡፡ | | | | |
| 12 | ከማንበብ በኋላ የሚቀርቡ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን ለመመለስ ምንባቡን በተሻለ ከሚያነቡ ተማሪዎች ጋር ማንበብ ጠቅሞኛል፡፡ | | | | |
| 13 | ከማንበብ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ምንባቡን በቡድን ማንበብ ጠቅሞኛል፡፡ | | | | |
| 14 | በቡድን እየተወያየን አንብበን የተገነዘብውን ሀሳብ በግል ለምንጠየቀው ጥያቄ በቂ ምላሽ እሰጣለሁ፡፡ | | | | |
| 15 | በማንበብ ጊዜ የሚከብደኝን ሀሳብ ለመገንዘብ የሚያግዘኝ ካገኘሁለማንበብ ደስተኛ ነኝ፡፡ | | | | |
| 16 | መምህራችን በመማር ሂደት ላይ በየቡድናችን እየተዘዋወሩ የሚያበረታቱን ከሆነ ለማንበብ እነሳሳለሁ፡፡ | | | | |
| 17 | ከቡድናችን ሞዴል የሆኑ ተማሪዎች ሲያነቡ ለማንበብ እነሳሳለሁ፡፡ | | | | |
| 18 | በግል ከማንበብ ይልቅ በቡድን ማንበብ አንድን ሀሳብ ለመገንዘብ ይጠቅማል፡፡ | | | | |
| 19 | በግል አንብቤ የምንባቡን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ ለመገንዘብ አልቸገርም፡፡ | | | | |
| 20 | በቡድን ማንበብ ደስተኛ ያደርገኛል፡፡ | | | | |

## አባሪ ሠ

## ቁጥጥርና ሙከራ ቡድን ቅድመ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት

| የተማሪ | ቁጥጥር ቡድኑ አንብቦ | ሙከራ ቡድኑ አንብብ |
|---|---|---|

| ተ.ቁ | የመረዳት ፈተና ውጤት | የመረዳት ፈተና ውጤት |
|---|---|---|
| 1 | 8 | 13 |
| 2 | 9 | 14 |
| 3 | 11 | 16 |
| 4 | 13 | 12 |
| 5 | 10 | 10 |
| 6 | 12 | 12 |
| 7 | 14 | 12 |
| 8 | 15 | 16 |
| 9 | 10 | 9 |
| 10 | 18 | 13 |
| 11 | 14 | 15 |
| 12 | 12 | 8 |
| 13 | 13 | 15 |
| 14 | 15 | 13 |
| 15 | 14 | 14 |
| 16 | 12 | 15 |
| 17 | 13 | 13 |
| 18 | 14 | 11 |
| 19 | 15 | 11 |
| 20 | 10 | 13 |
| 21 | 13 | 8 |
| 22 | 12 | 9 |
| 23 | 15 | 15 |
| 24 | 16 | 13 |
| 25 | 15 | 14 |
| 26 | 13 | 15 |

| | | |
|---|---|---|
| 27 | 9 | 14 |
| 28 | 10 | 12 |
| 29 | 8 | 10 |
| 30 | 18 | 11 |
| 31 | 12 | 13 |
| 32 | 15 | 14 |
| 33 | 16 | 17 |
| 34 | 14 | 13 |
| 35 | 14 | 14 |
| 36 | 14 | 12 |
| 37 | 9 | 13 |
| 38 | 11 | 17 |
| 39 | 14 | 11 |
| 40 | 15 | 14 |
| 41 | 14 | 18 |
| 42 | 15 | 13 |

## አባሪ ረ

## ሙከራ ቡድኑ በቅድመ ቡድናዊ መማር የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ የሰጡት ምላሽ

| የማሪ ተ.ቁ | ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 1 | 2 | 3 | 4 | 2 | 4 | 1 | 3 | 2 | 4 | 2 | 1 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 1 |
| 2 | 3 | 1 | 1 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 1 | 3 | 1 | 3 | 2 | 4 | 1 | 3 | 4 | 1 | 4 |
| 3 | 1 | 4 | 3 | 4 | 4 | 1 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 1 | 4 | 2 |
| 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 4 | 3 | 1 | 1 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 | 1 | 4 |
| 5 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 3 | 1 | 3 | 1 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 2 | 3 | 3 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 6 | 1 | 4 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 2 | 4 | 3 | 4 | 1 | 4 | 1 | 3 | 3 | 3 | 4 |
| 7 | 2 | 1 | 4 | 2 | 4 | 4 | 3 | 1 | 2 | 4 | 4 | 1 | 4 | 2 | 3 | 4 | 1 | 4 | 4 | 3 |
| 8 | 1 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 1 | 3 | 1 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 1 |
| 9 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 3 | 4 | 3 | 4 | 1 | 2 | 4 |
| 10 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 1 | 2 | 2 | 3 | 3 | 1 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 11 | 1 | 3 | 4 | 2 | 3 | 4 | 1 | 4 | 3 | 1 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 4 | 1 | 4 | 1 | 4 |
| 12 | 2 | 1 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 1 | 1 | 3 | 3 |
| 13 | 1 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 | 4 | 3 | 2 | 1 | 1 | 1 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 1 | 4 |
| 14 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 1 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 4 | 4 | 4 | 3 | 3 | 2 |
| 15 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 4 | 1 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 2 | 4 | 1 | 3 | 2 | 2 | 3 |
| 16 | 4 | 1 | 4 | 2 | 4 | 2 | 3 | 4 | 2 | 1 | 4 | 3 | 2 | 4 | 1 | 4 | 1 | 3 | 4 | 1 |
| 17 | 2 | 3 | 1 | 3 | 4 | 4 | 1 | 2 | 1 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 |
| 18 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 2 | 1 | 3 | 2 | 4 | 2 | 4 | 1 | 3 | 1 | 4 | 3 | 2 | 1 |
| 19 | 4 | 1 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 | 1 | 4 | 4 | 4 |
| 20 | 1 | 3 | 4 | 3 | 1 | 2 | 1 | 4 | 1 | 1 | 3 | 4 | 1 | 3 | 4 | 1 | 1 | 3 | 3 | 2 |
| 21 | 3 | 1 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 2 | 1 |
| 22 | 4 | 4 | 1 | 4 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 1 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 2 | 3 | 3 | 4 |
| 23 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 4 | 3 | 1 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 1 | 4 | 2 |
| 24 | 4 | 4 | 1 | 3 | 2 | 1 | 3 | 3 | 1 | 4 | 3 | 1 | 1 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 2 | 4 |
| 25 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 | 3 | 4 | 1 | 4 | 2 | 4 | 3 | 2 | 4 | 3 | 1 | 2 | 4 | 4 | 3 |
| 26 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 |
| 27 | 4 | 4 | 2 | 4 | 2 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 1 | 3 | 1 | 4 | 3 | 4 | 4 | 1 | 4 | 2 |
| 28 | 4 | 3 | 3 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 3 | 4 | 2 | 1 | 3 | 3 | 3 |
| 29 | 3 | 2 | 3 | 1 | 1 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 | 4 | 1 | 2 | 4 |
| 30 | 3 | 3 | 4 | 3 | 1 | 1 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 1 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 |
| 31 | 3 | 2 | 4 | 4 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 1 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 4 | 3 |
| 32 | 4 | 4 | 3 | 3 | **2** | 4 | 2 | 2 | 2 | 4 | 2 | 3 | 4 | 3 | 4 | 2 | 1 | 2 | 2 | 4 |
| 33 | 3 | 3 | 4 | 4 | 2 | 3 | 3 | 3 | 4 | 1 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 4 | 3 |
| 34 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 1 | 4 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 35 | 4 | 3 | 2 | 4 | 2 | 4 | 4 | 5 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 4 | 4 | 2 | 3 | 2 | 4 | 1 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 36 | 3 | 4 | 4 | 1 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 | 4 | 1 | 3 | 1 | 4 |
| 37 | 4 | 2 | 4 | 4 | 2 | 1 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 2 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 2 |
| 38 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 4 | 1 | 3 | 2 | 1 | 1 | 3 | 4 | 4 | 2 | 2 | 4 | 4 |
| 39 | 1 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 | 1 | 2 | 3 | 1 | 3 |
| 40 | 4 | 4 | 2 | 4 | 2 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 3 | 4 | 4 | 4 | 1 |
| 41 | 2 | 3 | 4 | 1 | 1 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 3 |
| 42 | 1 | 2 | 4 | 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 4 | 1 |

## አባሪ ሰ

## ለመምህሩ የክፍል ውስጥ ልምምድ ትግበራ የተሰጠ ስልጠና፡፡

ጥናቱ ለሚመለከታቸው አካላት ይህን ጥናት የምታካሂደው መምህረት ከዚህ በታች የቀረቡትን ሀሳቦች በመጠቀም ቡድናዊ መማርን በክፍል ለመተግበር ስልጠና ሰታለች፡፡ የዚህ ጥናት ዋና አላማ ቡድናዊ መማር ዘዴ የኢ-አፍፌት ተማሪዎችን የማንበብ ተነሳሽነትና አንብቦ የመረዳት ስሎታ ለማጎልበት ያለው ጠቀሜታ የሚል ነው፡፡ ቡድናዊ መማር ዘዴ ተማሪዎች በመተጋገዝ አንድን ምንባብ አንብበው መልዕክቱን የበለጠ መረዳት እንዲችሉየሚያግዝ ነው፡፡ በመሆኑም በትክክል ማንበብ ለሚቸገሩ ተማሪዎች እገዛ ለማድረግ በቡድናዊ መማር ዘዴን ተጠቅሞ ተማሪዎችን ለማንበብ እንዲነሳሱና በሚገባ አንብበው መረዳት እንዲችሉ በጋራ ማለማመድ ያስፈልጋል፡፡ ቡድናዊ መማር ዘዴ ለማንበብ ተነሳሶትና ማንበብ ለማይደፍሩ ተማሪዎች በተሻለ ከሚያነቡተማሪዎች ጋር በማሳተፍ ለማለማመድ ጠቀመሚ ስልት ነው፡፡ ዘዴው በክፍል ውስጥ በትክክል ተግባራዊ ቢሆን ተማሪዎች ለማንበብ ፍላጎት እያደረባቸውና አንድን ጽሁፍ አንብበው ለመረዳት ይበረታታሉ፡፡

በመሆኑም መምህራን ቡድናዊ መማርን በክፍል ውስጥ ተግባራዊ ለማድረግ እቅድ በማቀድና ተገቢ ትኩረትና ክትትል በማድረግ እነዚህን ተማሪዎች እራሳቸውን እስኪችሉ ልምምድ እንዲያደርጉ ማድረግ አስፈላጊ ነው፡፡ይህም ልምምድ ወደፊት በራሳቸው እንዲያነቡና እንዲነሳሱ ያግዛል፡፡ ዘዴን Chamot (2005) ሲገልጹ ቅደም ተከተል ያለው የመማር ተግባርን የሚያፋጥን ብዙ ጊዜ ሆን ተብሎ የሚጠቀሙብትና አንድ ወደ ተፈለገ አላማ የሚያደርስ ነው፡፡

ክፍል አንድ አጠቃላይ መመሪያ

ውድ መምህር በአንድ ጥናት ሂደት የተሳታፊዎች በክንውኑ ፍቃደኛ መሆን ዋና ጉዳይ ነው፡፡ ስለዚህ መምህር ለዚህ ጥናት መሳካት ፍቃደኛ ስለሆኑ አመሰግናለሁ፡፡ የዚህ ክፍል አላማ

መምህሩ በክፍል ውስጥ ቡድናዊ መማር ዘዴን ተጠቅሞ ማንበብን እና አንብቦ መረዳትን ለማለማመድ  ወይም ለማስተማር ሲሆን የቡድናዊ መማርን ምንነት፣ጠቀሜታ ለማስገንዘብ ነው፡፡ይኸውም፡-

1. የቡድናዊ መማር ምንነት፣ Cohen (1994) ቡድናዊ መማር ዘዴ ማለት ተማሪዎችን በትምህርት ችሎታቸው በክፍል ውስጥ ከፋፍሎ ርስ በርስ አንዱ ከሌላው እንዲማር ማድረግና መቆጣጠርን የሚያመላክት ነው ብለው ይገልጻሉ፡፡

2. የቡድናዊ ዘዴ አከፋፈል፣ የቡድናዊ መማር ዘዴ አከፋፈልን የተለያዩ ምሁራን በተለያ መንገድ የከፈሉት ሲሆን እንደ Oxford (1990) ብለሀቶችን በሁለት መንገድ ይከፈላሉ፡፡ ያውም ቀጥተኛና ኢቀጥተኛ ሲሆኑ ቀጥተኛ ብለሀቶች ስር አእምሮታዊ ማካካስ ወዘተ ሲሆኑ ኢቀጥተኛ የንባብ ብለሀቶች የሚባሉት ልእለ አእምሮታዊ፣ የሚመደቡት ትውስታ፣ ማህበራዊ፣ ስሜታዊ ወዘተ ሲሆኑ በማህበራዊ ብለሀቶች ስር ደግሞ ጥያቄና መልስ፣ ከሌሎች ጋር መተባበር መማር፣ በቡድን ተከፋፍሎ በመተጋገዝ መማር ወዘተ የሚባሉ ይካተታሉ፡፡ከማህበራዊ  ብለሀቶች ውስጥ በቡድን ተከፋፍሎ መማር አንዱ ሲሆኑ ተማሪዎች አንብቦ የመረዳት ትምህርት ይዘትን በተናጥል ከመማር ይልቅ አንዱ ሌላውን በማገዝ ወይም ርስ በርስ በመተጋገዝ መማር የሚል እሳቤን የሚያመላክት ነው፡፡

O'Mellaey (1900)በበኩላቸው ዘዴ አእምሮአዊ፣ማህበራዊና ልእለ አእምሮአዊ በማለት ሲከፋፍሉ አእምሮታዊ ተማሪዎች ተምረው የተገነዘቡትን አንዱ ለሌላው የሚያስገነዝብበት ሲሆን ማህበራዊ ዘዴ ደግሞ አንዱ ከሌላው እርስ በርስ የሚማማሩበትን ሂደት እና ቋንቋን ትምህርት ለመማር የሌላ ሰዎችን ተሳትፎ አስፈላጊ እንደሆነ ሁሉ ለአንብቦ መረዳት ውጤታማነትም ተማሪዎች በቡድን እየተወያዩ የምንባቡን ሀሳብ መረዳት ተመራጭ ነው፡፡ልእለአእምሮአዊ ዘዴዎችተማሪዎችትምህርታቸውን በትክክል በዕቅድ ለመምራትና ለመፈተሽ፣ አጠቃላይ ያመጡትን ለውጥ እንዲሁም ውጤት ለመገምገም የሚያስችል ስልት ነው፡

3. የቡድናዊ መማር ጠቀሜታ Agnihotri፣Ngorosha (2018) ቋንቋን በመማር ማስተማር ሂደት መምህር መራሽ በሆነ መንገድ ብቻ ማስተማር ተማሪውን ፍዝ አድማጭ ማድረግ በመሆኑ ከዚህ ተቃራኒ በሆነ ሁኔታ ቡድናዊ መማር በተለየ አይነት ሳቢና ከፍተኛ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል፡፡ ምክንያቱም ዘዴው ሙሉ ትምህርታዊ እና ሳይንሳዊ የመማር ዘዴን የሚቀበል ነው፡፡

በትናንሽ ቡድን መማር ሀሳብን ማበረታቻና ትምህርታዊ ችግሮችን መፍቻ ነው፡፡ Meo (2013)ን ጠቅሰው በቡድን መማር ወይም ማስተማር ዘዴ ውጤታማ አቀራረብ መሆኑን በተለያዩ ትምህርት ቤቶች የተገመገመ እንደሆነ ያስረዳሉ፡፡ አክለውም በቡድን ማስተማር ተማሪ ተኮር የሆነ አቀራረብና ሁሉም ተማሪዎች በአንድ ላይ በአንድ ርዕሰ ጉዳይ ላይ በመወያየትና በንቃት መማር ውስጥ እንዲገቡ የሚያግዛቸው ነው፡፡

4.በቡድን መማር የመምህርና ተማሪዎች ሚና፡-

በቡድናዊ መማር የመምህር ሚና ክፍሉን ማደራጀትና ቡድኑን መቆጣጠር፣ ክትትል ማድረግ ነው፡፡ የተማሪዎች ሚና ደግሞ እርስ በርስ በመተጋገዝ ማንበብ እና መገንዘብ፣ መጠያየቅና ምላሽ መስጠት፣ መተጋገዝ፣ አንብቦ መረዳት የመሳሰሉት ናቸው፡፡

ክፍል ሁለት፡- የዚህ ክፍል አላማ መምህሩ የቡድናዊ መማር ዘዴን በመጠቀም ልምምዱን

በቅደም ተከተል መተግበር ነው፡፡

የቡድናዊ መማር ዘዴ አተገባበር ቅደም ተከተላዊ ሂደት

1. ስለ ቡድናዊ መማር ዘዴ ማስተዋወቅና መግለጽ፡-
   መምህሩ ተማሪዎችን ከብለሀቱ ጋር የሚያስተዋውቅበት እና የትኛውን ስለት፣ እንዴት እንደሚጠቀሙ እንዲለዩ የሚያደርግበት ነው፡፡
2. በቡድን ማስቀመጥ፡-ተማሪዎችን በምን አይነት ስለት እንደሚያነቡ ካሳወቁ በኋላ ቡድን መስርተው እንዲቀመጡና እርስ በርሳቸው እተጋገዙ እንዲያነቡ ማድረግ፡፡
3. በቡድን ማለማመድ፡-ተማሪዎች የቀረቡላቸውን የንባብ ተግባራት በቅደም ተከተል በቡድን የማለማመዱን ሁኔታ ተግባራዊ ሲሆን ነው፡፡
4. ክፍሉን ማደራጀት
5. መከታተል
6. ማበረታታት

ክፍል ሶስት ማለማመድ

ተማሪዎች በቡድን እየተወያዩ የቀረቡላቸውን ምንባቦችን እንዲያነቡና መልእክቱን እንዲረዱ በማድረግ ከምንባቡ ምን ተረዳችሁ የሚለውን በመጠየቅ በቡድን እየተወያዩ እንዲመልሱ የሚደረግበት ነው

ክፍል አራት ግምገማ

መምህሩ በቡድን መማር ዘዴን ሲተገብሩ እያንዳንዱን ጉዳይ ማከናወናቸውን ራሳቸውን የሚጠይቁበት እና ተማሪዎችም ዘዴው ምን እንደጠቀማቸው መገምገም አለበት፡፡

## አባሪ ሸ

### ለሙከራ ቡድኑ የክፍል ውስጥ ልምምድ የተዘጋጀ የትምህርት እቅድ

የትምህርት ቤቱ ስም ዴራ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት

የመምህሩ ስም፡-

የትምህርት አይነት አማርኛ

ክፍል 9ኛ

ርዕስ የተራቆተ አከባቢን ማልማት

ክፍለ ጊዜ 40 ቀን

ማንበብ

የትምህርት አላማ

- ተማሪዎች ምንባብን ርስ በርሳቸው በመተጋገዝ ለማንበብ ይነሳሳሉ፡፡
- በቡድን እየተጋገዙ ያነባሉ፡፡
- የምንባቡን ሀሳብ በተመለከተ በቡድን ይወያያሉ፡፡
- አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ላይ ይወያያሉ፡፡
- ለአንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ፡፡
- የቃላትን አውዳዊ ፍቺ ይሰጣሉ፡፡

- ለቃላት አገባባዊ ፍች ይሰጣሉ።

የትምህርቱ ይዘት

ቡድናዊ ማንበብ መምህሩ፣ ክፍሉን ማቀናጀት፣ ተማሪዎችን በቡድን ማደራጀት፣ ለንባብ ማነሳሳት፣ መቆጣጠር መከታተል፣ እርምት መስጠት

ተማሪው፣ በቡድን መቀመጥ፣ መተጋገዝ፣ እንደ ቡድን ሀሳብ መስጠት፣ በጋራ መስራት

አቀራረብ፣ ተማሪዎችን ለንባብ ማነሳሳት፣ ቅድመ ንባብ ጥያቄዎችን መጠየቅ፣ ተማሪዎች

በቡድን እየተጋገዙ እንዲያነቡ ማድረግ፣ መቆጣጠር፣ መምራት

የማስተማሪያ ስልት ተማሪዎች በቡድን እየተጋገዙ እንዲያነብ ማድረግ፣ በቡድን

ማስነበብ።

ማጠቃለያ ሁሉም ተማሪዎች የምንባቡን ሀሳብ መረዳታቸውንና አንብቦ የመረዳት

ጥያቄ መስራታቸውን ማረጋገጥ እንዲሁም በትክክል ላልመለሱት በድጋሜ እርመት

መስጠትና አቅጣጫ መስጠት።

የመምህሩ ስም---------------------------ፍርማ----------ቀን

የክፍለ ትምህርቱ ተጠሪ ስም -----------------ፍርማ ---------ቀን------------

የርዕሰ መምህሩ ስም ---------------------ፍርማ -------------ቀን-----------------

## አባሪ ቀ

## ለጥናቱ በክፍል ውስጥ ማንበብና አንብቦ የመረዳት ክህልን ለማለማመድ ከ9ኛ ክፍል መማሪያ መጽሀፍ የተወሰዱ ምንባቦችና መልመጃዎች

### ክፍለ ትምህርት አንድ

### የተራቆተአካባቢንማልማት

በአንድ በተራቆ ተ የገጠር ተራራማ ክፍል የሚኖሩ ማህበረሰቦች አካባቢያቸው ለረጅም ጊዜ በመታረሱና ለምነቱ በመቀነሱ ምክንያት ምርት አልሰጥስላላቸው አርሶ አደሮች ተቸግረዋል፡፡ የሚዘሩት እህል አልፎ አልፎ በሚጥለው ዝናብ በጐርፍ ይወሰድባቸዋል፡፡ በበጋ ወቅት እንስሶቻቸው የሚጠጡት ውኃ አያገኙም፡፡ የሙቀት መጠኑም ከለመዱት የተለየ ሆኖባቸዋል በአካባቢያቸው የሚገኘው የምንጭ ውኃመጠኑ እየቀነሰ መጥቷል፡፡ በዚህ ም ምክንያት የመንደሩ ሰዎች ውኃ ለመቅዳት በማለዳሄደው የሚመለሱት ቀትርላይ ነው፡፡ በአጠቃላይ የነዋሪዎቹ ችግሮች ከዕለት ወደ ዕለት እየተበራከቱ ናቸው፡፡ ነዋሪዎቹ ም ችግሩን መፍታት ባለመቻላቸው እንዲሁፈጣሪያቸውን እያማረሩይኖራሉ፡፡ ይህጉዳይ የአካባቢ እንክብካቤና ጥበቃ ባለሙያ የሆነችውን ሠራተኛ እያሳሰባት መጣ፡፡አንድ ቀን የአካባቢውን ነዋሪዎች ለማወያየት ስብስባጠራች፡፡ ነዋሪዎቹም የስብሰባውን ሰዓት አክብረውተገኙ፡፡ ባለሙያዋ የመወያያው ርዕሰ ጉዳይ የአካባቢ ልማት መሆኑንአስተዋወቀች፡፡

ከዚያም ንግግሯን እንዲህ በማለትቀጠለች፡፡ "እንደምታዩት በአካባቢ የሚታይ ሳርም ሆነቅጠል የለም፡፡የአንዳንድ አርሶ አደሮች ከብቶች የሚግጡትሳርየለም፡፡ እኛም የመጠጥ ውኃ እንደልባችን ማግኘት አልቻልንም፡፡ በአጠቃላይ የአካባቢው የድሮው ልምላሜ አሁንየለም፡፡ የችግሩ ፈጣሪዎች እኛ ውራሳችን ስለሆንን መፍትሔውንም ራሳችን መፈለግ አለብን፡፡ስለዚህ አካባቢውን ወደ ነበረበት ይዞ ታለመመለስ የራሳችን ንጥረት ማድረግ ይኖርብናል"በማለት ገለጸች፡፡

ተሰብሳቢዎች ምየየራሳቸውን ሀሳብ አንጸባረቁ፡፡ ሀሳባቸውን ከተለዋወጡ በኋላ የመጀመሪያ ሥራቸው በዝናብ እየታጠ በ የሚሄደውን አፈርሰብስቦ ለመያዝና ርጥበትን ጠብቆ ለማቆ የት ችግኝ አፍል ተው መትከል እንዳለባቸው ተስማሙ፡፡ በዚህ ሥራም ሁሉም የማኅበረሰቡ አባላት መሳተፍ እንዳለባቸው ተነጋገሩ፡፡ በመጨረሻም ሥራውን ለመጀመር ቀጠሮ ይዘው ተለያዩ፡፡

በቀጠሮው ቀን ዕድሜው ለሥራ የደረሰ ሁሉ ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ እንደ አካፋ፣ዶማ፣ወዘተ ያሉትን መሣሪያዎች ይዘው በቦታው ተገኙ። በመጀመሪያ ምን አይነት ችግኝ ማፍላት እንዳለባቸው ከባለሙያዋ ትምህርት ወሠዱ።ለችግኝ ማፍያ የሚሆን  ቦታና መደብ አዘጋጁ። ችግኙ እንዳይደርቅ በአቅራቢያው ያለችውን የምንጭ ውሃ ለመጠቀም በጥልቀት ቆፈሩ ናበዙሪያዋ ካብካቡ፤ተራ በተራ ችግኙን መንከባከብ እንዳለባቸው ተመካከሩ። በተራራው ላይም አልፎ አልፎ እርከን አዘጋጁ፤ይህንን ሁሉ አድርገው የችግኝ መንከባ ከብ ተግባርና ሃላፊነት ተከፋፍለው ተለያዩ።

ችግኝ ተከላው ከመካሄዱ ቀደም ብሎ የተወሰኑት ነዋሪዎች ለችግኝ መትከያ ጉድጓድ ቆፈሩ። በቀጠሯቸው መሠረት ክረምት በገባበ ሁለተኛው ሳምንት ለነዋሪዎቹ በጥሩም ባጥሪተላለፈ። በስምምነታቸው መሠረት ሁሉም ነዋሪዎች ከችግኝ ጣቢያው የሚችሉትን ያህል ችግኝ በመያዝ ወደተራራው አመሩ። ከተራራው ላይ እንደደረሱም በአስተባባሪዎች አማካይነት የሥራ ክፍፍል አደረጉ። የተወሰኑ ትችግኝ ሲያቀርቡ ሌሎቹ ተቆፍሮ በተዘጋጀው ጉድጓድ ውስጥ ችግኝ መትከል ጀመሩ። በዚህ ሁኔታ ተረዳድተው ያለምንም ድካም የተለያዩ ችግኞችን ተከሉ። በመጨረሻው ቀን የችግኝ ተከላው ሥራ እንደተጠናቀቀ ለአጭር ጊዜ በመወያየት “ችግኝና ሕጻን እንክብካቤን ይወዳል”በሚለው አባባል መሠረት ተራ ገብተው ችግኞችን ለመንከባከብ ወሰኑ።

ችግር አስተምሯቸዋልና ሁሉም የተሰጣቸውን ኃላፊነት ለመወጣት ጥረት  አደረጉ።በአካባቢ የሚገኙ የቤት እንስሳትም ወደችግኙ እንዳይሄዱ ለማድረግ እንዲሁም ጭፍጨፋ እንዳይካሄድ የመተዳደሪያደን  ብአወጡ። የአካባቢ እንክብካቤና ጥበቃ ባለሙያዋ ችግኞቹ ከተተከሉ በኋላ ክትትል ማድረጓን አላቋረጠችም።

በዚህም መሠረት ችግኙ አድጎ ጥብቅ ደን ሆነ። ካመታት በኋላ አካባቢ ውለም ቶለ ዓይን ማረፊያ ሆኗል። በአካባቢው ይከሰት የነበረው ጐርፍ ቀንሷል። አፈሩም ለምነቱን ጨምሯል። ውኃም እንደል ብማግኘት ተችሏል።እንስሳትም ከቤት እየዋሉ የሚዘጋጅላቸውን መኖ እንደልብ ማግኘት ችለዋል።  የአካባቢው ነዋሪዎችም የእርከን ሥራንና የችግኝ ተከላን ጥቅም በመረዳት በየጓሯቸውና በየእርሻቸው ተግባራዊ እያደረጉትይገኛሉ።

(አብክመ አካባቢና ደን ጥበቃ ባለስልጣን፣ስኬታማየደንልማትናጥበቃተሞክሮ፣የካቲት፣2013። ማሻሻያ ተደርጎበት የተወሰደ)

**አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች**

ሀ. ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት አብራሩ፡፡

1. ከላይ የቀረበው ጽሑፍ የሚያስተላልፈው መልዕክትን መልዕክት ባጭሩ ግለጹ፡፡
2. ነዋሪዎች ውሃ ለመቅዳት በማለዳ ሄደው ቀትር ላይ የሚመለሱት ለምንድነው?
3. የአርሶ አደሮቹ ምርት የቀነሰው በምን ምክንያት ነው??
4. የአከባቢ ጥበቃ ባለሞያዎች የችግሩ ፈጣሪዎች እኛው ራሳችን ነን ስትል ምን ማለት ነው?
5. ነዋሪዎቹ ባደረጉት ስብሰባ በመጀመሪያ የተስማሙት ምን ለማድረግ ነው፡፡
6. ነዋሪዎቹ በተራራ ላይ እርከን የሰሩት ልምን ይመስላችኋል?
7. ችግኝና ህፃን እንክብካቤ ይወዳሉ የሚለውን አባባል አብራሩ፡፡

ለ. ከዚህ በታች ከምንባቡ የተወሰዱ ልዩ ልዩ ሀሳቦች ተዘርዝረዋል፡፡ በምሳሌው መሰረት

ስሩ፡፡ምሳሌ 1. የግብርና ምርት መቀነስ ለልማት መነሻ ምክንያት ነው፡፡

2.ችግኝ ማፍያ ስፍራ ማዘጋጀት ችግኝ ለመትከል ቅድመ ዝግጅት ነው፡፡

ሀ. የመሬት መራቆት፡፡

ለ. ችግኝ መትከያ ጉድጓድ መቆፈር፡፡

ሐ. መተዳደሪያ ድንብ ማውጣት፡፡

መ.የእንሰሳት መኖ መጨመር፡፡

ሠ.የእርከን ስራ ማከናወን ፡፡

ረ.የግጦሽ ሳር እጥረት ፡፡

ሰ. ችግኝ ማፍላት፡፡

ሸ. ጥብቅ ደን መፍጠር ፡፡

ቀ. የአፈር ለምነት መጨመር ፡፡

በ. እንሰሳት ወደ ችግኙ እንዳይሄዱ ማድረግ፡፡

ተ. ችግኙ እንዳይደርቅ መንከባከብ፡፡

ቸ. የአፈር ለምነት መቀነስ፡፡

ሐ. በምንባቡ መሰረት ለቀረቡት ቃላት አገባባዊ ፍቺ ስጡ፡፡

1. የሚግጡት
2. አንፀባረቁ
3. ማፍላት
4. ካብ
5. እርከን
6. ጥሩምባ
7. አመሩ
8. ደንብ
9.መኖ

## ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ተበቺሳ

የተፈጥሮ ልምላሜ የታደለ አካባቢ ነው፡፡ "ስምን መላክ ያወጣዋል" እንዲሉ ስሙም ለሚ ይሰኛል፡፡ በደቡብ ወሎ ዞን በከለላ ወረዳ የሚገኝ ገጠር ነው፡፡የዚህ አካባቢ ሴቶች መልከ መልካሞች ናቸው፡፡በተለይ የልጃገረዶቹ ውበት ልብ ይሰርቃል፡፡የሚያጌጡት በተፈጥሮ ውበታቸው ነው፡፡ዞማ ፀጉራቸው ጋሜ፣ሳዱላ፣ኮልኮሎ፣ወዘተበሚባሉ የአሰራርና የአለጫጨ ስልቶ ይበጃጃል፡፡አልፎ አልፎ ቅቤ በአደስ ይቀባል እንጂ ሌላ ዘመን አመጣሽ ቅባትና ተኩስ አያውቅም፡፡ ብዙዎ ኮረዳዎችጠያይሞችና ወዛሞችናቸው፡፡በአካባቢው አገላለጽ«እርጥብ ልምጭይመስላሉ፡፡በጠይም ፊታቸው ላይ እንደፈርጥ የሚያንፀባርቀው ውብ አይናቸው ትዳር ከመያዛቸው በፊት ኩል አያዘወትሩም፡፡ከብርና ከነሀስ የተሰሩ መስቀሎች ድምብሎዎች በጥቁር የሐር ክር ለክተው መለል ባለው አንገታቸው ላይ ያስራሉ፡፡ማርዳ ተጨምሮባቸው በደረታቸው ላይ ደረጃ በደረጃ የሚኮለኩሉት መስቀሎችና ድንብሎዎች ጎንበስ ቀና ባሉ ቁጥር በጡታቸው መሀል ድብብቆሽ ሲጫወቱ ይውላሉ፡፡ብዙውን ጊዜ የሚለብሱት ቀሚስ በሰፈርጥበበኛ የተሸመነ ሽብሽቦ ነው፡፡ትዳር ከመመስረታቸው በፊት ግን መቀነት አይታጠቁም፡፡

የለሚማህበረሰብ እነዚህ ኮረዳዎች የተፈጥሮ ውበታቸውን እንዲጠቀሙበት የሚያደርግና በጉ ጉት የላቀ ወንዝ በቀል ባህል አለው፡፡የአካባቢው ኮረዳዎች ትዳር ከመያዛቸው በፊት ከመረጡትትጉብልጋር የከንፈር ወዳጅነት ግንኙት የመመስረት ሙሉ ነፃነት አላቸው፡፡ከከንፈር ወዳጃቻቸው ጋር የሚገናኙባቸው በርካታ አጋጣሚዎች አሉ፡፡ከነዚህም መካከልአክርማቀጨታ፣ እንጨትሰበራ፣ኩበትለቀማ፣ልብስአጠባ፣ጥምቀት፣እንቁጣጣሽና "ተበቺሳ" ጥቂቶቹ ናቸው፡፡ከነዚህ የመገናኛ አጋጣሚዎች ግጥም የማይደረደርበት ወይም የማይዜምበት፣ እንጉርጉሮ ወይ ዘፈን የሌለበት አይገኝም፡፡ለለሚ ኮረዳዎች ሙዚቃ ሕይወታቸው ነው፡፡የአካባቢው ማሕበራዊ ሕይወት

በሙዚቃ ኃይል የሚንቀሳቀስ ነው፡፡ኮረዳዎቹ በየአጋጣሚው የሚጫወቷቸው አጥንት ሰርስረው ዘልቀው ሥሜትን የሚሞግቱ ውብ ዜማዎች አሏቸው፡፡

የአንድ ሰፈር ኮረዳዎች ተጠራርተው አክርማ ቀጨታ ወይ እንጨት ሰብራ ወይ ኩበት ለቀማ በሚሄድበት ጊዜ በዚያ አውላላ ሜዳ ላይ ድምፃቸውን ከፍ አድርገው በሕብረት ሲያዜ እንኳን የከንፈር ወዳጃቻቸውን ወፎችን ይጠራሉ፡፡በነዚህ አጋጣሚዎች ብዙውን ጊዜ የከንፈር ወዳጃቻቸውን የሚያሞግሱ ግጥሞችን ነው የሚያዜሙት እንደሚከተለው ያሉትን፡-

አይኑን በቀጫጭን የተኳኳለው፣

ጥርሱን ጕራማይሌ የተወቀረው፣

እንደነብር ጅራት የሚወራጨው፣

እንዴት ነው ጠይም ልጅ ለሚ ላይ ያለው?

ኧረ ጠይም ጠይም ጠይም እትውደዱ፣

እኔን አታዩም ወይ ሲጠፋኝ መንገዱ፣

ይሄ ወንዛወንዙ ያበቅላል እንዶድ ፣

ያካል መጨረሻ ጠይም ልጅ መውደድ፣

ጠይም ወዶ ወዶ በቀይ ሲመለሱ ፣

ሆድ ይበረብራል ጠጅ እንደቀመሰ፡፡

የከንፈር ወዳጅ ከሚገናኙበት አጋጣሚ ሁሉ የተለየ ግምት የሚሰጠው ለተበቺሳ ነው፡፡ (ተበቺሳ ከኦሮሚኛ የተወሰደ ቃል ሲሆን ትርጉሙም አጫውት ማለ ነው፡፡) ተበቺሳ የሚባለው ድግስ ከሚጀመርበት ዕለት ጀምሮ የአካባቢው ኮረዳዎችና ጎረምሳዎች ማታ ማታ እየተሰባሰቡ ሲጨፍሩ የሚያድሩበት አጋጣሚ ነው፡፡ልዩ የሚያደርገው ቤተሰብ “እባካችሁ ልጃችንን ታጫውትልን” የሚልመልእክት አስይዞ በየሰፈሩ ልጅ በመላክ ኮረዳዎችን ይለምናል፡፡የኮረዳዎቹ ወለጆ ያለማመንታት ይፈቅዱላቸዋል፡፡ኮረዳዎቹም ሲዘገጃጁ ውለው ምሽት ላይ ለጫወታቸው ማድመቂያ የምትሆን አታሞ እየያዙ ወደ ደጋሾቹ ቤት ይሄዳሉ፡፡ጫወታው ሲጀምር ኮረዳዎቹ

ክብ ሰርተው አታሟቸውን እየመቱ በሚስረቀረቅ ድምጽ በሕብረት ያዜማሉ፣እስክስታም ይወርዳሉ፡፡ የአታሞ ድምጽ ሰምተው ከየመንደሩየመጡትጎረምሳዎችደግሞራሳቸውን ላለማስለየት ለአይናቸው ብቻ ቀዳዳ በመተው በጋቢያቸው ተሸፋፍነው ዱላቸውን ትከሻቸው ላይ አንግሰው ከኮረዳዎቹ ጀርባ በቡድን በቡድን ይቆማሉ፡፡ ከዚያም ኮረዳዎቹ የሚያዜሙት ግጥም ቤት በደፋ ቁጥር በጕርናና በሚያስገመግም የአንበሳ ድምጽ በህብረት ያገሳሉ፡፡ በዚህ አኳኋን አንድዙር ጭፈራ እንዳለቀ ጎረምሳዎቹ የከንፈር ወዳጃቻቸውን እጅ በመያዝ እየጎተቱ ወደዳር ካወጧቸው በኃላ በጋቢያቸው ይሸፍኑናየፍቅር ጫወታ ይጫወታሉ፡፡ ይህ አይነቱ የጭፈራ አጋጣሚ የዳንስ ምሽት (ፖርቲ) የሚባለውን አይነት መሆኑ ነው፡፡ ነገር ግን የዱባናየቅል አበቃቀሉ ለየቅል እንደሚባለው ሁለቱ የወጣቶች የመገናኛ አጋጣሚዎች በባህሪያቸው እጅግ የተለያዩ ናቸው፡፡ በተበቺሳ ከከንፈር ያለፈ ጫወታ ፈጽሞ የለም፡፡ ወጣቶች የከንፈር ወዳጅነትግንኙነት የመመስረት ነፃነት እንዳላቸው ሁሉ በህብረተሰቡ የተጣለባቸውን ራሳቸውንየመጠበቅ ኃላፊነት በሚገባ ይወጣሉ፡፡

በተበቺሳ የከንፈር ወዳጃቻቸው የመጣላቸው ኮረዳዎች የሚያዜሟቸው ግጥሞች የሙገሳ ግጥሞች ናቸው፡፡ የሚከተሉትን ለአብነት ማየት ይቻላል፡-

እኔስ ከቅድሙ አሁን ተሻለኝ ፣

የንትን ሰፈር ልጆች መጡ መሰለኝ፣

አይናማ በኔሞት እኔ አፈር ስሆን፣

አንዴ ሳቅና ልየው ጥርስህን፣

አየ ጉድ ዋ ሆዩ ወገብ አቀጣጠን፣

አያበቅለው የለ ክረምትና ማጠን፣

የጣዝማ ወለላ የሸጉ ከንፈር፣

አዙሮ ይጥላል እንደምች አደር፡፡

በተበቺሳ የከንፈር ወዳጃቸው ያልተገኙላቸው ኮረዳዎች የሚከተለውን አይነት ግጥም ያዜማሉ፣

አሁን ይህን ጊዜ ያልመጣ ወዳጅ ፣

እናቱ ገርድፋ ይሰልቃል ልጅ፡፡

ጎረምሳዎቹ ለከንፈር ወዳጆቻቸው ግጥሞችን የማያዜሙት እንደ ከብት ጥበቃ፣እርሻ፣አረምና አጨዳ ባሉ የግብርናተግባራት ላይ በሚሰማሩበት ጊዜ ነው፡፡በተበቺሳ አጋጣሚ በአስገምጋሚው የአንበሳ ድምፃቸው የኮረዳዎቹን ዜማ ከማድመቅ ሌላ የሚጠበቅባቸው ድርሻ የለም፡፡በሥራ ላይ እያሉ የሚያዜሟቸው የፍቅር ግጥሞች የሚከተሉትን የመሳሰሉ ናቸው፡፡

ቱሉ ለሚ ሆኖ ይታያል ወለቃ፣

አንገቷ የሚመስለው የማሽላ መቃ፣

የትዝታዬ እሸት የልቤ መብራት፣

ላገኘሽ ነው መሰል መታኝ እንቅፋት፣

የሹምን በረሃ ስትሄድ ብቻዋን፣

ምነው ባደረገኝ ያንን ድምብሿን፣

ሳንቃ ደረቷ ላይ የሚዘለውን፡፡

የከንፈር ወዳጆች በነፃነት የሚገናኙበት መልካም አጋጣሚ ሆኖ ሳለ ተበቺሳ አንድ ጉልህጎጂገጽታአለው፡፡ ይሄውም አንዳንድ ጊዜ በጥቃቅን ምክንያት የሰው ሕይወት የሚያልፍበት አጋጣሚ መሆኑ ነው፡፡ጎረምሳዎቹ ከተለያዩ መንደሮች የሚሰባሰቡ እንደመሆናቸው በቡድን እየተከፋፈሉ ጠብ በመፍጠር ርስበርስ ይደባደባሉ፡፡ የጠቡ መንስኤ በሌላ አጋጣሚ የተፈጠረና የቆየ ቁርሾ ሊሆን ይችላል፡፡ወይም ደግሞ የአንደኛውን ጎረምሳ የከንፈር ወዳጅ ያለፍላጎቷ አስገድዶ ለመወዳጀት የሚደረግሙከራሊሆንይችላል፡፡ ሰበቡ ምንም ይሁን ምን ጠብ እየተፈጠረ የሰው ደም በከንቱ የሚፈስበት የተበቺሳ አጋጣሚ ብዙ ነው፡፡

ይህ አይነቱ ጎጂ ጎኑ ቀስ በቀስ ከተወገደ ተበቺሳ ነፃነት የተሞላበትና ሕብረተሰቡ በአወንታ የተቀበለውባህል ስለሆነ ለወጣቶች ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡

*(መስፍን መሰለ፣ የቦረና ወሎ ከንፈር ወዳጆችና ግጥሞቻቸው፤ 1985፡፡ ለማስተማር እንዲመች ተደርጎ የተወሰደ)*

**አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች**

*ሀ. ምንባቡን መሰረት በማድረግ የሚከተሉትን ጥያቄዎች መልሱ፡፡*

1. የለሚ ኮረዳዎች አንገታቸው ላይ የሚያስሯቸው ማጌጫዎች ምን ምን ናቸው?
2. በሁሉም አጋጣሚዎች የከንፈር ወዳጆች ሲገናኙ ግጥም የሚደረድሩይመስላችኋል?
3. ተበቺሳ ምንድነው?
4. በተበቺሳ አጋጣሚ ወጣቶች የሚገናኙት እንዴት ነው?
5. የለሚ ጎሮምሳዎች ጋቢ የሚሸፋፈኑት ለምንድነው?
6. በከተማ የዳንስ ምሽትና በተበቺሳ መካከል ያለው ልዩነት ምንድነው?
7. ተበቺሳ ጎጂ ገጽታ አለው ትላላችሁ ለምን?
8. የምንባቡ መልዕክት ምንድን ነው?

ለ. ቀጥሎ በቀረቡት ዐ.ነገሮች ውስጥ የተሰመረባቸውን ቃላት ፍቺ በምንባቡ ሃሳብ መሰረት በቃል አስረዱ፡፡

1.የልጃገረዶቹ ውበት ልብ ይሰርቃል፡፡

2. ብዝዎቹ ኮረዳዎች ጠያይሞችና ወዛሞች ናቸው፡፡

3. ከከንፈር ያለፈ ጫወታ ፈጽሞ የለም፡፡

4. ራሳቸውን ላለማስለየት ይጥራሉ፡፡

5. ሕይወት በሙዚቃ ኃይል የሚንቀሳቀስ ነው፡፡

6. በህብረተሰቡ የተጣለባቸውን ኃላፊነት በሚገባ ይወጣሉ፡፡

7.ለወጣቶች ያለው ፋይዳ ከፍተኛ ነው፡፡

ሐ. በምንባቡ መሰረት በ ሀ ክፍል የቀረቡትን ቃላትና ሐረጋት በ ለ ክፍል ከተዘረዘሩት ተመሳሳያቸው ጋር አዛምዱ፡፡

| *ሀ* | ለ |
|---|---|
| 1. የሚኮሎኮሉት | ሀ.መንከራተቴ |
| 2. አታሞ | ለ. እንዳላበላሽብህ |
| 3. በሚስረቀረቅ | ሐ. ልውደቅልህ |
| 4. አንግበው | መ. ከበሮ |

5. በሚያስገመግም ሠ. ሲሰወርብኝ

6. በቅምጫና ረ. የሚደረደሩት

7. እንዳልጎሸብህ ሰ. ነጎድጓድ

8. መባከኔን ሸ.መጠጫ

9. ልንኮትኮትልህ ቀ. በሚመስጥ

10. ሲጠፋኝ በ. የሚያንቀጠቅጥ

ተ.ይዘው

መ.ቀጥሎ ከምንባቡ የወጡ ቃላት ናቸው። ተቃራኒ ፍቻቸውን ስጡ።

1.ልምላሜ 6.ጠፋ

2. ተበጀ 7.አምንታ

3. ለካ 8. ሰበሰበ

4.ጉብል 9.ሕብረት

5. ጠራ 10. ደመቀ

## ክፍለ ትምህርት ሶስት

## ግብር መክፈል

አንዲት ሀገር ሁለንተናዊ የኢኮኖሚያዊ፣ የማህበራዊና የፖለቲካዊ እድገቶቿን ለማቀላጠፍ ያልተቋረጠ ገቢ መሰብሰብ ያስፈልጋታል። የገቢ ምንጮች በመሆን ከሚያገለግሉ መካከል ደግሞ ግብር ዋነኛው መሆኑ ይታወቃል። ለዚህም ነው ግብር ወይም ታክስዋናው የመንግስት የፋይናንስምንጭ በመሆን የአንድ ሀገር የምጣኔ ሀብት፣ የልማትና የእድገት የጀርባ አጥንትነው የሚባለው። ዜጎች ህይወታቸው፣ ነጻነታቸውና ንብረታቸው ላይ ሊደርስ ከሚችለው ማንኛውም ጉዳት እንዲ ከላከልላቸው መንግስት የሚባለውን አካል ፈጥረው ይኖራሉ። ይህ መንግስት የሚባለው አካልም የተጣለበትን አደራ ለማሳካትና የገባውን ቃል ለማስፈጸሚያነት ከዜጎች ግብር የመሰብሰብና ስራ ላይ የማዋል ሀላፊነት አለበት። ዜጎች መንግስታቸው እንዲሰጣቸው የሚፈልጓቸውን አገልግሎቶች ባግባቡያገኙ ዘንድ ግብር መክፈልን ግዴታቸውን እንደመወጣት በመቁጠር በወቅቱ ተፈጻሚ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ድሮ ድሮ የመንግስት ሀላፊነት ነው ተብሎ የሚታሰበው ነዋሪዎችን ወይም ዜጎችን ከጥቃት በመከላከል ደህንነታቸውን ማስጠበቅ ብቻ ነበር፡፡ በዘመናዊው አለም ግን የመንግስት ሚና ጥንታዊ ከሆነው የዜጎችን ሰላምና ደህንነት ከማስከበር አልፎ መሰረታዊ ፍላጎታቸውን ማሟላት፣ እንዲሁም መሰረታዊ ልማቶችን ማስፋፋትና ሁለንተናዊ እድገትን ለማፋጠን የሚያስፈልጉ ስራዎችን እንዲያከናውኑና ማህበራዊ ፍትህን እንዲያሰፍን ይጠበቃል፡፡ እነዚህን ሰፊተግባራት ለመከወን ነው እንግዲህመንግስት ወጪውን የሚሸፍንበት የገቢ ምንጭ ያስፈልገዋል የሚባለው፡፡ ከላይ እንደ ተጠቀሰው ምግብር ዋነኛው የገቢ ምነጭ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ከመንግስት አገልግሎት የሚሰበሰብ ክፍያ፣ ከተለያዩ አካላት የሚገኝ እርዳታና የመሳሰሉት ደግሞ ከግብር በተጨማሪ ለመንግስት በገቢ ምንጭነት የሚያገለግሉ ናቸው፡፡

ጠቅለል አድርገን ስናየው ግብር ወይም ታክስ ማለት መንግስት ለዜጎች ለሚሰጣቸው አገልግሎቶች የሚያወጣቸውን ወጪዎች ለመሸፈን እንዲችል በህግ የተጣል አስገዳጅነት ያለው ክፍያ ነው ማለት ይቻላል፡፡ ይህ ብያኔ የሚጣመላክተውም ግብር በህግ የሚጣል ግዴታ መሆኑንና አስቀድሞ በተደነገገው የህግ ማዕቀፍ መሰረትም ተፈጻሚ እንደሚደረግ ነው፡፡ ማንኛውም ግብር ከፋይ በተለየ ሁኔታ ለከፈለው ግብር በግሉ ቀጥተኛ የግብር ጥያቄ ሳያነሳ ግብሩን መክፈል ይጠበቅበታል፡፡ ነገር ግን የሚጠበቅበትን ግብር ሳይከፍል ቢቀር በአስተዳደራዊና በወንጀል ህጎች ተጠያቂ የሚሆን ይሆናል ማለት ነው፡፡ በነገራችን ላይ ግብር የሚጣለውም ሆነ የሚሰበሰበው በመንግስት ብቻ ነው፡፡ግለሰቦች ግብር የመጣል እና የመሰብሰብ ስልጣን የላቸውም፡፡

ስለግብር ሲነሳ አብረው የሚነሱ ሁለት መሰረታዊ ነገሮች አሉ፡፡ እነሱም ግብር የሚጣልበት የገቢ ምንጭና የሚጣለው ግብር ወይም ታክስ መጠን ናቸው፡፡ ግብር የሚጣልባቸው የገቢ ምንጮች ገቢ የሚያስገኙ ማናቸውም የምረት፣ የአገልግሎትና የንግድ ወይም የስራ ዘርፎች ሲሆኑ የግብር መጠን ደግሞ በነዚሁ ገቢዎች የሚጣለው የገንዘብ መጠን ነው፡፡ በዚህም ግብር ከፋዮች በገቢያጨው ልክ ግብር እንዲከፍሉ ይደረጋል፡፡ በዚሁ መሰረት ዝቅተኛ ገቢ ያላቸውግብር ከፋዮች አነስተኛ ግብር የሚከፍሉ ሲሆን፣ በአንጻሩ ከፍተኛ ገቢ ያላቸው ግብር ከፋዮች ደግሞ ከፍ ያለ ግብር ይከፍላሉ ማለት ነው፡፡ ይሕም የግብርን አፈጻጸም ፍትሀዊነት ያሳያል፡፡

ምንጭ፡- ከ9ኛ ክፍል አማርኛ ቋንቋ መጽሀፍ የተወሰደ፡፡

**አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎች**

ሀ. የሚከተሉትን ጥያቄዎች  በምንባቡ መሰረት “ትክክል”ከሆኑ እውነት “ስህተት “የሆኑትን ደግሞ ሀሰት በማለት መልሱ ።

1.ግብር መንግስት ዜጎቹ በአግባቡ ኑሯቸውን እንዲመሩ የሚከፈላቸው ክፍያ ነው።

2. አንድ ግብር ከፋይ ለከፈለው ግብር ቀጥተኛ የጥቅም ጥያቄ ማንሳት ይችላል።

3. ከፍ ያለ ግበር ከፋዮች የሚባሉት ገቢ ያላቸው የህብረተሰብ ክፍሎች ናቸው።

4. በአሁኑና በጥንታዊው ዘመን የነበረው የመንግሰት ሚና ተመሳሳይአይደለም።

ሐ. ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከልበምንባቡ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።

1. አንድ ሀገር ግብር የሚሰበስበው ለምንድነው?

   ሀ.ኢኮኖሚውን ለማሳደግ  ለ.ማህበራዊ እድገትን ለማፋጠን

   ሐ.ፖለቲካዊ እድገትን ለማፋጠን  መ.ሁሉም

2. ከሚከተሉት ውስጥ የአንድ ሀገር ዋና የገቢ ምንጭ የሆነው የጡቱ ነው?

   ሀ.ግብር እና ታስክ  ለ.መንግስታዊ ያልሆኑ ድርጅቶየሚሰጡት እርዳታ

   ሐ.የወጪና ገቢ ንግድ  ሐ.ሁሉም

3. ዜጎች መንግሰት የተባለውን የፈጠሩት ለምንድነው

   ሀ.ህይወታቸውን ከአደጋ እንዲጠብቅላቸው  ለ.ነጻነታቸውን እንዲያስከብርላቸው

   ሐ.ንብረታቸውን ከማንኛውም አደጋ እንዲጠብቅላቸው  መ.ሁሉም

4. የአንድ ሀገር ህዝቦች ከመንግስት የሚፈልጉትን ነገር ለማግኘት ምን ማድረግ

ይጠበቅባቸዋል

ሀ.ጠንክረው ሰርተው ሀብታም መሆን ለ.ልጆቻቸውን ማስተማር

ሐ. የተጣለባቸውን ግብር መክፈል መ.በመከላከያ ሰራዊት ውስጥ መሳተፍ

5. ድሮ ድሮ የመንግሰት ሀላፊነት የነበረው ምን ነበር

ሀ.የዜጎችን መሰረታዊ ፍላጎት ማሟለት ለ.ዜጎችን ከጥቃት መከላከል

ሐ.መሰረተ ልማቶችን ማስፋፋት መ.ንግድና ቱሪዝምን ማስፋፋት

6. ዜጎች የሚከፍሉት የግብር መጠን መሰረት የሚያደርገው ምንድነው

ሀ. የዜጎች ግዴታና መብት ለ.የሰራተኞችን የስራ ዘርፍ

ሐ.የግብር ከፋዮችን የገቢ ምንጭ መ.ቀደም ሲል የከፈሉትን የግብር መጠን

ለ. በምንባቡ ያላቸውን አገባባዊ ፍቺ ከ "ለ" ረድፍ ከቀርቡት ውስጥ በመፈለግአዛምዱ፡፡

| "ሀ" | " ለ" |
|---|---|
| 1.ዘርፎች | ሀ.ጥፋተኛ በአግባቡ ለማስኬድ |
| 2. ለማቀላጠፍ | ለ.ሁሉን አቀፍ |
| 3.የጆረባ አጥነት | ሐ.መስኮች ፣አይነቶች |
| 4.ሁለንተናዊነት | መ.የመቆጣጠሪያ መርሆች |
| 5.ተጠያቂ | ሠ.ሀላፊነት |
| 6.የሚጣለው | ረ.ተገቢነት፣አለማዳላት |
| 7. በአንጻሩ | ሰ.ለማፋጠን፣በአግባቡ ለማስኬድ |

8. ፍትሀዊነት ሸ.ወሳኝ፣መሰረታዊ

9. ስልጣን ቀ. የሚወሰነው፣የሚተመነው

10. የህግ ማዕቀፍ በ. ተቃራኒው

**አባሪ በ**

**መምህሩ በጥናቱ የተካተቱ የቁጥጥርና የሙከራ ቡድኖችን ሲያስተምር መከታተያ**

**ቅጽ፡፡**

| | |
|---|---|
| | የክፍል ውስጥ ክንውን |
| 1 | የዕለቱን ትምህርት አላማ ማሳወቅ |
| 2 | ስለ ቡድናዊ መማር አላማ ማስገንዘብ |
| 3 | ተማሪዎቹን በቡድን ማስቀመጥ |
| 4 | ተማሪዎችን ለማነሳሳት ቡድናዊ መርሆች ተገልጸዋል |
| 5 | ምንባቦቹ ለተማሪዎቹ ቀርበዋል |
| 6 | በተሻለ የሚያነቡ ተማሪዎችን ለይቷል |
| 7<br>8 | የቀረበውን ምንባብ በቡድን እንዲወያዩ አድርጓል<br>ተማሪዎቹ በቡድን መስራታቸውን ተከታትሏል |
| 9 | ተማሪዎቹ እርስ በረስ እንዲተጋገዙ አደርጓል |
| 10 | ከምንባብ በኋላ መልመጃዎችን አሰርቷል |
| 11 | ከማንበብ በኋላ መረዳታቸውን ገምግሟል |
| 12 | አስፈላጊ ሲሆን ከየቡድኑ ጋር ሀሳብ ተለዋውጠዋል |

# አባሪ ተ

## ድህረ ልምምድ አንንብቦ የመረዳት ፈተና አስተማማኝነት በእኩል ክፋይ (splithalf) ስሌት ለማስላት የተሰበሰቡ ውጤቶች

| ቁጥር | በተጋማሽ ጎዶሎ ቁጥር በትክክል የተመለሱ ትክክለኛ መልሶች | በተጋማሽ ሙሉ ቁጥሮች የተመለሱ ትክክለኛ መልሶች |
|---|---|---|
| 1 | 7 | 5 |
| 2 | 4 | 5 |
| 3 | 7 | 6 |
| 4 | 5 | 7 |
| 5 | 5 | 6 |
| 6 | 9 | 7 |
| 7 | 5 | 7 |
| 8 | 7 | 9 |
| 9 | 8 | 7 |
| 10 | 8 | 9 |
| 11 | 7 | 5 |
| 12 | 7 | 7 |
| 13 | 7 | 8 |
| 14 | 9 | 8 |
| 15 | 6 | 5 |
| 16 | 8 | 9 |
| 17 | 8 | 9 |
| 18 | 7 | 6 |
| 19 | 8 | 7 |
| 20 | 8 | 9 |
| 21 | 7 | 8 |
| 22 | 7 | 6 |
| 23 | 5 | 6 |
| 24 | 7 | 7 |
| 25 | 6 | 7 |
| 26 | 7 | 8 |
| 27 | 7 | 9 |

| | | |
|---|---|---|
| 28 | 6 | 5 |
| 29 | 8 | 7 |
| 30 | 7 | 7 |
| 31 | 9 | 9 |
| 32 | 8 | 7 |
| 33 | 9 | 7 |
| 34 | 9 | 8 |
| 35 | 7 | 6 |
| 36 | 8 | 9 |
| 37 | 8 | 7 |
| 38 | 8 | 9 |
| 39 | 9 | 9 |
| 40 | 8 | 9 |

---

**አባሪ ቸ**

**ለ9ኛ ክፍል ኢ-አፍፊት ተማሪዎች የቀረበ ድህረ ልምምድ አንብቦ**

**የመረዳትፈተና፡፡**

## አዲስአበባዩኒቨርሲቲ

## የሂዩማኒቲስት፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን

## ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎርክፍለ ትምህርት ክፍል

## የድህረ- ምረቃ መርሐ ግብር

ተማሪዎች፡-የዚህመጠይቅ ዋና አላማው በክፍል ውስጥ በቡድን ተከፋፍሎ የመማር ዘዴ የኢ-አፍ ፊት ተማሪዎችን የማንባብ ተነሳሽነት እና አንብቦ የመረዳት ክሂል ችሎታን ለማጎልበት ያለውን ጠቀሜታ በሚል ርዕስ ጥናት ለሚደረግ በቂ መረጃ ለማግኘት ነው፡፡ ውድ ተማሪዎች፣ አጥኚዋ ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከረችው ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ይሆን ዘንድ ጥናት ለማካሄድ

ፈልጋለች፡፡ በመሆኑም ቡድናዊ መማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበትና የንባብ ተነሳሽነትን ለመፍጠር ያለውን ጠቀሜታ በሚል የጥናት ርዕስ ለመመርመር አስባለች፡፡ ሆኖም መረጃ መሰብሰብ ተገቢ ሲሆን ይህን መረጃ ስትሞሉ መረጃው ለዚህ ጥናት ብቻ የሚያገለግልና በናንተ ላይ ምንም ተጽዕኖ የሌለው እንዲሁም ምሥጢራዊነቱ የተጠበቀ መሆኑን ልትገልጽላችሁ ትወዳለች፡፡ መጠይቁ 20 ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን ለያንዳንዱ ጥያቄ የራሳችሁን ሀሳብ ብቻ ሊያሳዩ የሚችሉትን መልሶች እንድትመልሱ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

ምስጋናዬም ከልብ ነው፡፡

የተፈቀደው ሰዓት 1:30

አጠቃላይ መመሪያ

ውድ ተማሪዎች፣ ይህ ፈተና አንብቦ የመረዳት ፈተና ነው፡፡ ፈተናው አንብቦ መረዳትን ችሎታ መለካት ሲሆን ይህንን ምንባብ አንብባችሁ በምንባቡ መሰረት ለተጠየቃችሁት ጥያቄ በሙሉ ምላሽ እንድትሰጡ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡

## የልማት አርበኛው ጄኔራል

ተወልደውበትና ለሚኖሩበት አከባቢ በከፍተኛ ሁኔታ የደከሙ ዜጎች መኖራቸው ጥርጥር የለውም፡፡ ለአገርና ወገን ሲታገሉ ያለፉቱ፣ የድካሙና የእንግልቱ ክብደትና ቅለት እንደየሰዎቹ ፣ እንደየ አከባቢያቸውና እንደየ አየር ንብረቱ ቀላልና ከባድ ሊሆን ይችላል፡፡ ጥቂት ሰዎች አቅደው፣አውጥተና አውርደው ለብዙኀን አለኝታና መከታ፣ እነርሱ ቀልጠው ለወገኖቻቸው ብርሀን፣ ለአገራቸው ቤዛ ይሆናሉ፡፡ ምን ጊዜም የትም ቦታ ለበጎ ስራ ዕውን መሆን መሰዋዓት የሆኑ ወይም የሚሆኑ አይጠፉም፡፡ ጥቂቶች በነደፉትና ተግባራዊ ባደረጉት ስራ በርካቶች ይጠቀማሉ፡፡ በማህበራዊም ሆነ በፖለቲካ ተሳትፎ በጎ ሰዎች ለአንድ ድርጅት መቀጠል ወይም አለመቀጠል ምክንያት ይሆናሉ፡፡ ይህንን እውነታ በተጨባጭ አብነት አስደግፎ መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡

በጉራጌ፣ በልማት ፋና ወጊነታቸው አንቱ ከተባሉ ተወላጆች መካከል የልማትና የጦር ሜዳ አርበኛ የነበሩት ሌተናል ጄኔራል ወልደስላሴ በረካ አንዱ ናቸው፡፡ ጄኔራሉ በ1950ዎቹ መጀመሪያ ላይ ታቅዶ ደረጃ በደረጃ ተግባራዊ የተደረገው የጉራጌ መንገዶች ስራ ድርጅትን

በመምራት ለውጤት አብቅተዋል። ለረጅም ጊዜ የጉራጌ ብሄረሰብ ራስ ምታት ሆኖ የቆየውን የመንገድ ችግር ለመፍታት ጄኔራሉና አጋሮቻቸው ያደረጉት ውጣ ውረድ እጅግ ከባድ ነበር። በዚያ የጨለማ ወቅት (1943 ዓ.ም ጀምሮ)ሰባት ቤትን በመኪና መንገድ መገናኘት እልህ አስጨራሽና ፈታኝ ትግል እንደነበር በወቅቱ በስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውስጥ የነበሩ ወገኖች ያስታውሳሉ። የጉራጌ መንገዶች ስራ ድርጅት አሃዱ ተብሎ ስራው የተጀመረው ከወልቂጤ ወደ ሆሳዕና በሚዘልቀውና 132 ኪሎ ሜትር ርዝመት ባለው መንገድ በ1956 ዓ.ም.ነበር።

በከተማም ሆነ በገጠር በግንባር በመገኘት የመንገድን አስፈላጊነት በማሳመን ህብረተሰቡ ሳያሰልስ ድጋፍ እንዲያደርግ የማግባባትና የውትወታ ስራ ተሰርቷል። በዚህም ሂደት ጥቅማቸው የሚነካባቸው የሚነካባቸው የመሰላቸው አንዳንድ ሰዎች የመንገዱ ስራ እንዳይሳካ እንቅፋት በመሆን ሁከት እስከመፍጠር ደርሰው ነበር። ይሁን እንጂ ሌተናል ጄነራል ወልደ ስላሴ በረካና የልማቱ ደጋፊዎች ፈተናውን ተቋቁመው የጀመሩትን የመንገድ ስራ የሰባት ቤት ወልረዳዎችን በማስተሳሰር አለመግባባቶቹን በብሔረሰቡ ባህል መሰረት ፈተዋል፣ እውነትና ንጋት እያደር ይጠራል እንዲሉ። የታሰበውንና የታቀደውን የልማት ስራም እውን በማድረግ ለውጤት ማብቃት ችለዋል።

የጄኔራሉ የልማት ገደቡ ውስን አልነበረም። የጉራጌ መንገዶች ሥራ ድርጅት፣ ሰባት ቤትን በአጭር ጊዜ ውስጥ በማገናኘት በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካም ጭምር ግምባር ቀደም ድርጅት ለመሆን ችሎ እንደነበረ በወቅቱ የወጡ ዘገባዎች ያስረዳሉ። የዚህ ድርጅት ጥረትና ትጋት ሌሎች ኢትዮጵያውያነም በየአከባቢያቸው ልማት እንዲያለሙ  ሆኗል። ለአብነት ያህል የአለም ገና ወላይታ ሶዶ መንገድ ተጠቃሽ ነው። የአገር መከላከያ ሚንስቴር፣ የአውራ ጎዳና ባለስልጣንና ሌሎችም ያደረጉት ድጋፍ እንደዘበት የሚረሳ አይደለም ሥራ በህብረት ለሀገር ልማት በሚል ብለሃት በወቅቱ ዋናውን የወልቂጤ ሆሳዕና መንገድ በማስቀደም ሌሎችንም ከ500 ኪሎ ሜትር በላይ የክረምትና በጋ መንገድ ለመስራት ተችሏል።

በዚህ ሁሉ ፈታኝና እልህ አስጨራስ የመንገድ ስራ፣ የኔተናል ጄኔራል ወልደ ስላሴ በረካ ሚና እጅግ ከፍ ያለ ነበር። ዛሬ፣ ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ የሚደበዝዝ ሳይሆን ፍሬው እጅግ ደምቆ የሚያበራና የሚንቦጎቦግ ሥራ ሰርተውና አሻራ አሳርፈው አልፈዋል። ይህም በመሆኑ ለልፋታቸው፣ ለውጣውረዳቸው፣ ለትጋታቸውና ለጥንካሬያቸው መታሰቢያ ይሆን ዘንድ የብሔረሰቡ ተወላጆች ባደረጉት ድጋፍ በወለወቂጤ ከተማ ላይ ሀውልት ቆሞላቸዋል። መንገድ

የልማት ሁሉ በር ከፋች እነዚህ የቁርጥ ቀን ልጅ የህዝብን ተነሳሽነት ያሰሩት መንገድ፣ ከኢትዮጵያ አልፎ በአፍሪካም ጭምር አቻ ያልተገኘለት አኩሪ የራስ አገዝ ልማት ሥራ በመሆኑ የተለየ ሥፍራ ይሰጣቸዋል፤ አርአያነታቸውም ለዘለዓለም ሲወሳ ይኖራል፡፡

ምንጭ ፡-ብረሃን ዓለሙ ሪፖርተር ጋዜጣ፡፡(ከ9ኛ ክፍል አማርኛ መጽሐፍ

የተወሰደ፡፡)

**መመሪያ አንድ፡-የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰረት“ትክክል” ከሆኑ እውነት “ስህተት “የሆኑትን ደግሞ ሀሰት በማለት በባዶ ቦታላይ መልስ ስጥ/ ስጪ ፡፡**

1. የውራጌ መንገድ ስራ ድርጅት አሃዱ ብሎ የጀመረው በ1950 ዓ.ም ነው፡፡

2. ሌተናል ወልደ ስላሴ በረካ በመንገድ ስራ የገጠማቸውን ፈተና ተቋቁመዋል፡፡

3. በጉራጌ የልማት ፋና ወጊ ጀነራል ታደስ ብሩ ናቸው፡፡

4. ለወገን አሌኝታና መከታ ለመሆን ቆርጠውና እነርሱ ቀልጠው ለወገኖቻቸው

ብርሃን የሚሆኑ ዜጎች ቁጥራቸው ብዙ ነው፡፡

5.ለአገራቸውና ወገናቸው የሚታገሉ ዜጎች ሲታገሉ የእንግልታቸው ክብደትና

እንግለትይለያያል፡፡

**መመሪያ ሁለት፡- በ“ሀ” ስር የተዘረዘሩት ቃላት ከምንባቡ የወጡ ናቸው፡፡በምንባቡ ያላቸውን አገባባዊ ፍቺ ከ “ለ” ረድፍ ከቀርቡት ውስጥበመፈለግአዛምዱ፡፡**

| “ሀ” | “ ለ” |
|---|---|
| 6. አሻራ | ሀ.አርአያ |
| 7.ፋናወጊ | ለ.ምልክት |
| 8. ደንቃራ | ሐ.እንቅፋት |
| 9.ሚና | መ.ምክንያት |

10.መንስኤ ሠ.ድርሻ

11.እልህ አስጨራ ረ.ጥረት

12. ትጋት ሰ.አድካሚ

**መመሪያ ሶስት፡- ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ከተሰጡት አማራጮች መካከል በምንባቡ መሰረት ትክክለኛ መልስ የያዘውን ፊደል ምረጡ።**

13.ሌተናል ጄኔራል ወልደ ስላሴ በረካ ላበረከቱት አስተዋጽኦ መታሰቢያ ይሆን

ዘንድ በብሄረሰቡ ተወላጆች ዘንድ ምን ተደርጎላቸዋል?

ሀ. ኒሻን ተሸልመዋል። ለ.የገንዘብ ስጦታ ተበርክቶላቸዋል።

ሐ. ሀውልት ቆሞላቸዋል። መ.በስማቸው መንገድ ተሰይሞላቸዋል

14.የልማት አርበኛ፣ሌተናል ወልደስላሴ፣በልማት ፋና ወጊነታቸው ይበልጥ አንቱ

የተባሉት ከሚከተሉት በየትኛው አከባቢ ነው?

ሀ.በምራቡ ቤተ ጉራጌ አከባቢ ለ.በአዲስ አበባና አከባቢው

ሐ. በጉራጌ ዞን ትልልቅ ከተሞች መ.በሁሉም የጉራጌ አከባቢዎች

15.በምንባቡ መሰረት የጉራጌ መንገድ ሥራ ድርጅት ውጤታማ እንዳይሆን

እንቅፋት በመሆን ሁከት እስከመፍጠር የደረሱት እነማን ናቸው?

ሀ. የመንገድን ጥቅም በውል ያልተረዱ ሰዎች

ለ.ጥቅማቸው የሚነካባቸው የመሰላቸው ሰዎች

ሐ.ስንፍና የተጠናወታጥቂት ግለሰቦች

መ.በስራው ለመሳተፍ ጊዜ ያጠራቸው ሰዎች

16. ከሚከተሉት መካከል በጉራጌ መንገዶች ስራ ድርጅት ጥረትና ትጋት የለማው

የትኛው ነው?

ሀ.የአዲስ አበባ ወልቂጤ መንገድ ለ.የዝዋይ ቡታ ጅራ መንገድ

ሐ.የአዲስ አበባ ጅማ መንገድ መ.የአለም ገና ሶዶ መንገድ

17.የተለያዩ የልማት አጋሮች ከጉራጌ የመንገድ ስራ ጋር ተባብረው በርካታ መንገዶችን በሰሩበት ወቅት ይከተሉት የነበረው መርሆ ምን የሚል ነው?

ሀ. ድር ቢያብር አንበሳ ያስር ለ.እውነት እናንጋት እያደር ይጠራል

ሐ.የጥቂቶች ጥረት ለብዙኂኑ ርካታ መ.ስራ በህብረት ለአገር ልማት

18. ለረዥም ጊዜ የጉራጌ ብሔረሰብ ራስ ምታት ሆኖ የቆየው ምን ነበር?

ሀ.የንጹህ ውሃ ተደራሽነት ለ. የባለሙያ እጥረት

ሐ.የመንገድ ችግር መ.የኑሮ ውድነት

***መመሪያ አራት፡- ከዚህ ቀጥሎየቀረቡትን ጥያቄዎች በምንባቡ መሰርትባዶቦታውንአሟልታችሁ ጻፉ፡፡***

19. ከወልቂጤ ወደ ሆዕሳና በሚዘልቀውናኪሎ ሜትር ርዝመት ነው፡፡

20. ጄኔራሉ በሰሩት ታላቅ ስራ ከኢትዮጵያም ውጪ በ______የተለየ ስፍራ ይሰጣቸዋል፡፡

## አባሪ ጎ

**መጠይቅ ሁለት የማንበብ ተነሳሽነት አስተማማኝነት በክሮንባኽ አልፋ (cronbachAlpha) ስሌት**

| የማሪ ተ.ቁ | ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |
| 1 | 4 | 4 | 1 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 1 | 3 | 1 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 2 | 3 | 2 | 4 |
| 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 1 | 3 | 1 | 3 |
| 3 | 4 | 4 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 2 | 1 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 |
| 4 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 1 | 4 | 4 | 1 | 4 | 4 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 |
| 5 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 1 | 3 | 1 | 3 | 1 | 3 | 1 | 3 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 |
| 6 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 |
| 7 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 2 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 | 4 |
| 8 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 1 | 1 | 1 | 1 | 3 | 3 | 3 | 1 | 2 | 2 |
| 9 | 4 | 3 | 3 | 4 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 | 2 | 4 | 3 | 3 | 1 | 4 | 4 | 3 | 3 | 4 |
| 10 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 1 | 3 | 1 | 3 | 3 | 1 | 1 | 2 | 3 | 2 | 2 | 1 |
| 11 | 3 | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 4 | 3 | 2 | 2 | 2 | 3 |
| 12 | 4 | 2 | 4 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 2 | 4 | 2 | 4 | 2 |
| 13 | 4 | 4 | 1 | 4 | 2 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 |
| 14 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 |
| 15 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 | 4 | 3 | 3 | 4 | 3 | 2 | 3 |
| 16 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 |
| 17 | 4 | 3 | 4 | 2 | 4 | 2 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 | 4 |
| 18 | 3 | 3 | 2 | 3 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 1 | 4 | 1 | 3 |
| 19 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 |
| 20 | 4 | 4 | 1 | 4 | 2 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 | 3 | 3 | 3 | 4 | 3 | 3 | 2 | 4 |

# አባሪ ነ

## ለ9ኛ ክፍል ኢ-አፍ-ፈት የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች ድህረ የማንበብ ተነሳሽነትን በሚመለከት መረጃ ለማግኘት የቀረበ የጹሁፍ መጠይቅ

## አዲስአበባዩኒቨርሲቲ

# የሂዩማኒቲስት፣የቋንቋዎች ጥናት፣የጋዜጠኝነትና ኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

# የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎርክፍለ ትምህርት ክፍል

## የድህረ- ምረቃ መርሐ ግብር

ተማሪዎች፡-የዚህ መጠይቅ ዋና አላማው በክፍል ውስጥ  በቡድን ተከፋፍሎ የመማር ዘዴ የኢ-አፍ ፊት ተማሪዎችን የማንባብ ተነሳሽነት እና አንብቦ የመረዳት ክሂል ችሎታን ለማጎልበት ያለውን ጠቀሜታ በሚል ርዕስ ጥናት ለሚደረግ  በቂ መረጃ ለማግኘት ነው፡፡ ውድ ተማሪዎች፣ አጥኚዋ ከላይ ለመጥቀስ እንደሞከረችው ለሁለተኛ ድግሪ ማሟያ ይሆን ዘንድ ጥናት ለማካሄድ ፈልጋለች፡፡ በመሆኑም ቡድናዊ መማር የተማሪዎችን አንብቦ የመረዳት ችሎታን ለማጎልበትና የንባብ ተነሳሽነትን ለመፍጠር ያለውን ጠቀሜታ በሚል የጥናት ርዕስ ለመመርመር አስባለች፡፡ ሆኖም መረጃ መሰብሰብ ተገቢ ሲሆን ይህን መረጃ ስትሞሉ መረጃው ለዚህ ጥናት ብቻ የሚያገለግልና  በናንተ ላይ ምንም ተጽዕኖ የሌለው እንዲሁም ምሥጢራዊነቱ የተጠበቀ መሆኑን ልትገልጽላችሁ ትወዳለች፡፡ መጠይቁ 16 ጥያቄዎችን ያካተተ ሲሆን ለያንዳንዱ ጥያቄ የራሳችሁን ሀሳብ ብቻ ሊያሳዩ የሚችሉትን መልሶች እንድትመልሱ በትህትና እጠይቃለሁ፡፡ ምስጋናዬም ከልብ ነው፡፡

አጠቃላይ መመሪያ

1. መጠይቁ ላይ ስም መፃፍ አያስፈልግም፡፡

2.የጹሑፍ መጠይቁን በቡድን ተወያዩ መመለስ አያስፈልግም፡፡

3. ቀጥሎ ለተጠየቁት መረጃዎች ምላሽ ሊሆን ይችላል ብላችሁ ያሰባችሁትን በባዶ ስፍራው ሙላ/ሙዪ፡፡

ውድ ተማሪዎች፣ መርሃ ትምህርትን መሰረት አድርጎ በክፍል ደረጃችሁ ተዘጋጅቶ በመማሪያ መጻህፋችሁ የቀረበላችሁን የማንበቦ ትምህርት ይዘት ለማንበብ ያላችሁን ተነሳሶት በተመለከተ ለቀረቡት ጥያቄዎች ከዚህ በታች በተሰጡት መገለጫ ቁጥሮች አማካይነት በጥያቄዎቹ ፊት ለፊት ላይ የ X ምልክት አስቀምጡ፡፡

1. በጣም እስማማለሁ3. አልስማማም

2.እስማማለሁ 4.ፈፅሞ አልስማማም

| ተ.ቀ | የመጠይቁ ዝርዝር ነጥቦች | 1 | 2 | 3 | 4 |
|---|---|---|---|---|---|
| 1 | በቡድንመማር የማንበብ ትምህርት ይዘትን ለመማርያነሳሳኛል፡፡ | | | | |
| 2 | መምህሬ ንባብን ከቡድን አባላት ለኣንዱ በመስጠት ሲያስነብቡ ጓደኞቼን በማየት ለማንበብ እንድነሳሳ አድርጎኛል፡፡ | | | | |
| 3 | በማንበብ ትምህርት ይዘት ከጓደኞቼ ጋር በመወያየት በቡድን ማንበብደስተኛ እንድሆን አድርጎኛል፡፡ | | | | |
| 4 | መምህሬ የማንበብ ትምህርት ይዘትን ሲያስተምሩ የከበደኝን ሀሳብ የቡድን አባሉ እንዲያግዙኝ ካደረጉ ለማንበብ ዝግጁ አድርጎኛል፡፡ | | | | |
| 5 | የምንባቡን ሀሳብ አንብቦ ለመረዳት ስለምቸገር በተሸለ ከሚያነቡ ተማሪዎች ጋር በቡድን ማንበብ ለማንበብ አነሳስቶኛል፡፡ | | | | |
| 6 | የምንባቡን ሪዕሰ ጉዳይ ተመልክቼ ከጓደኞቼ ጋር በመወያየት ጹሁፉ ስለምን እንደሚገልጽ መናገር ለንባብ መነሳሳትን ፈጥሮልኛል፡፡ | | | | |
| 7 | ከምንባቡ የሚወጡ ቃላትን በቡድን ከተወያየሁ በኋላ ምለሽ ለመስጠት አነሳስቶኛል፡፡ | | | | |
| 8 | ምንባብን በቡድን እየተወያየሁ ካነበብኩየምንባቡን ጽንሰ ሀሳብ በቀላሉ ተገንዝቤያለሁ፡፡ | | | | |
| 9 | የማንበብ ትምህርት ይዘትን በግል ከማንበብ ይልቅ በቡድን ማንበብ ለማንበብ የበለጠ አነሳስቶኛል፡፡ | | | | |
| 10 | የአንድን ጽሁፍ ሀሳብ መልዕክት በሚገባ ለመገንዘብ በቡድንእየተወያየን ማንበብ ለማንበብ ይስበኛል፡፡ | | | | |
| 11 | በማንበብ ትምህርት መምህሬ ያልገባኝን ሀሳብ ጓደኞቼን እንድጠይቅ ሲያበረታቱኝ ለማንበብ አነሳስቶኛል፡፡ | | | | |
| 12 | ከማንበብ በኋላ የሚቀርቡ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን ለመመለስ ምንባቡን በተሻለ ከሚያነቡ ተማሪዎች ጋር ማንበብ ጠቅሞኛል፡፡ | | | | |
| 13 | ከማንበብ በኋላ የሚቀርቡ ጥያቄዎችን ለመመለስ ምንባቡን በቡድን ማንበብ ጠቅሞኛል፡፡ | | | | |
| 14 | ከቡድናችን በተሻለ የሚያነቡ ተማሪዎች ሲያነቡ ለማንበብ እንድነሳሳ አድርጎኛ፡፡ | | | | |
| 15 | በማንበብ ጊዜ የሚከብደኝን ሀሳብ ለመገንዘብ የሚያግዘኝ ካገኘሁለማንበብ ደስተኛ አድርጎኛል፡፡ | | | | |
| 16 | መምህራችን በመማር ሂደት ላይ በየቡድናች እየተዘዋወሩ የሚያበረታቱን ከሆነ ለማንበብ አነሳስቶኛል፡፡ | | | | |
| | ከቡድናችን ሞዴል የሆኑ ተማሪዎች ሲያነቡ ለማንበብ | | | | |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| 17 | እነሳሳለሁ፡፡ | | | | |
| 18 | በግል ከማንበብ ይልቅ በቡድን ማንበብ አንድን ሀሳብ ለመገንዘብ ይጠቅማል፡፡ | | | | |
| 19 | በግል አንብቤ የምንባቡን ሀሳብ ሙሉ በሙሉ ለመገንዘብ አልቸገርም፡፡ | | | | |
| 20 | በቡድን ማንበብ ደስተኛ ያደርገኛል፡፡ | | | | |

## አባሪ ኘ

## የቁጥጥር ቡድኑ ተማሪዎች የቅድመና ድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤቶች

| የተማሪ ተ.ቁ | ቅድመ ጥናት አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት | ድህረ ጥናት አንብቦ የመረዳት ፈተናውጤት |
|---|---|---|
| 1 | 8 | 13 |
| 2 | 9 | 11 |
| 3 | 11 | 9 |
| 4 | 13 | 13 |
| 5 | 10 | 10 |
| 6 | 12 | 14 |
| 7 | 14 | 13 |
| 8 | 15 | 11 |
| 9 | 10 | 14 |
| 10 | 18 | 17 |
| 11 | 14 | 12 |
| 12 | 12 | 13 |
| 13 | 13 | 16 |
| 14 | 15 | 9 |
| 15 | 14 | 12 |

| | | |
|---|---|---|
| 16 | 12 | 14 |
| 17 | 13 | 13 |
| 18 | 14 | 9 |
| 19 | 15 | 13 |
| 20 | 10 | 14 |
| 21 | 13 | 9 |
| 22 | 12 | 18 |
| 23 | 15 | 15 |
| 24 | 16 | 12 |
| 25 | 15 | 12 |
| 26 | 13 | 15 |
| 27 | 9 | 11 |
| 28 | 10 | 9 |
| 29 | 8 | 18 |
| 30 | 18 | 15 |
| 31 | 12 | 15 |
| 32 | 15 | 13 |
| 33 | 16 | 15 |
| 34 | 14 | 14 |
| 35 | 14 | 16 |
| 36 | 14 | 15 |
| 37 | 9 | 14 |
| 38 | 11 | 13 |
| 39 | 14 | 15 |
| 40 | 15 | 15 |
| 41 | 14 | 12 |
| 42 | 15 | 15 |

## አባሪ አ

### የሙከራ ቡድኑ ተማሪዎች የቅድመና ድህረ ልምምድ አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት

| የተማሪ ተ.ቁ | ቅድመ ጥናት አንብቦ የመረዳት ፈተና ውጤት | ድህረ ጥናት አንብቦ የመረዳት ፈተናውጤት |
|---|---|---|
| 1 | 13 | 14 |
| 2 | 14 | 15 |
| 3 | 16 | 17 |
| 4 | 12 | 18 |
| 5 | 10 | 19 |
| 6 | 12 | 16 |
| 7 | 12 | 20 |
| 8 | 15 | 16 |
| 9 | 9 | 14 |
| 10 | 13 | 18 |
| 11 | 15 | 16 |
| 12 | 8 | 17 |
| 13 | 15 | 14 |
| 14 | 13 | 15 |
| 15 | 14 | 19 |
| 16 | 15 | 16 |
| 17 | 13 | 18 |
| 18 | 14 | 20 |
| 19 | 15 | 17 |
| 20 | 13 | 15 |
| 21 | 8 | 18 |
| 22 | 9 | 18 |

| | | |
|---|---|---|
| 23 | 15 | 17 |
| 24 | 13 | 16 |
| 25 | 14 | 17 |
| 26 | 15 | 18 |
| 27 | 14 | 19 |
| 27 | 12 | 15 |
| 29 | 10 | 18 |
| 30 | 11 | 16 |
| 31 | 13 | 17 |
| 32 | 14 | 16 |
| 33 | 17 | 18 |
| 34 | 13 | 17 |
| 35 | 14 | 18 |
| 36 | 12 | 18 |
| 37 | 13 | 19 |
| 38 | 17 | 19 |
| 39 | 11 | 17 |
| 40 | 14 | 16 |
| 41 | 18 | 18 |
| 42 | 15 | 18 |

## አባሪ ከ

## ሙከራ ቡድኑ በድህረ ቡድናዊ መማር የማንበብ ተነሳሽነት መጠይቅ የሰጡት ምላሽ

| የማሪ ተ.ቁ | ጥያቄዎች | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 | 4 | 5 | 6 | 7 | 8 | 9 | 10 | 11 | 12 | 13 | 14 | 15 | 16 | 17 | 18 | 19 | 20 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 1 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 2 | 1 | 2 | 3 | 2 | 1 | 2 | 4 | 3 |
| 2 | 1 | 2 | 3 | 2 | 2 | 1 | 2 | 3 | 2 | 3 | 2 | 1 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 3 | 1 | 2 |
| 3 | 4 | 3 | 1 | 1 | 3 | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 3 | 1 | 2 | 2 | 3 | 3 |
| 4 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 3 | 3 | 2 | 1 | 4 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 1 |
| 5 | 2 | 2 | 1 | 2 | 1 | 3 | 2 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 3 | 3 | 1 | 2 | 3 | 4 |
| 6 | 3 | 4 | 2 | 1 | 2 | 1 | 1 | 3 | 1 | 3 | 2 | 1 | 1 | 2 | 3 | 2 | 4 | 4 | 3 | 2 |
| 7 | 4 | 2 | 3 | 1 | 2 | 2 | 3 | 3 | 1 | 4 | 2 | 3 | 2 | 1 | 3 | 2 | 2 | 1 | 2 | 3 |
| 8 | 1 | 2 | 3 | 2 | 1 | 2 | 2 | 4 | 1 | 2 | 4 | 2 | 4 | 2 | 1 | 3 | 1 | 2 | 1 | 2 |
| 9 | 2 | 1 | 3 | 2 | 3 | 3 | 1 | 2 | 3 | 4 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 4 | 2 | 4 | 3 |
| 10 | 4 | 2 | 2 | 1 | 4 | 1 | 4 | 2 | 3 | 1 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 |
| 11 | 3 | 3 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 1 | 3 | 2 | 1 | 1 | 4 |
| 12 | 4 | 3 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 3 |
| 13 | 1 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 4 | 1 | 3 | 4 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 |
| 14 | 2 | 3 | 1 | 1 | 3 | 3 | 2 | 1 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 4 | 1 |
| 15 | 1 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 1 | 2 | 3 | 2 | 1 | 3 | 2 | 4 | 2 | 3 | 3 |
| 16 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 2 |
| 17 | 1 | 1 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 3 | 2 | 2 | 4 | 2 | 1 | 3 | 3 | 2 | 4 | 2 | 2 | 3 |
| 18 | 2 | 2 | 3 | 1 | 2 | 3 | 2 | 3 | 1 | 1 | 2 | 3 | 4 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 1 | 1 |
| 19 | 2 | 3 | 2 | 2 | 2 | 2 | 3 | 1 | 2 | 3 | 2 | 1 | 1 | 2 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 4 |
| 20 | 1 | 2 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 |
| 21 | 4 | 2 | 3 | 2 | 1 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 1 | 3 | 3 | 4 | 1 | 2 | 3 |
| 22 | 1 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 1 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 1 |
| 23 | 1 | 2 | 2 | 3 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 1 | 1 | 4 | 2 | 4 |
| 24 | 1 | 1 | 2 | 4 | 3 | 2 | 3 | 2 | 3 | 4 | 3 | 2 | 1 | 1 | 3 | 3 | 4 | 3 | 1 | 2 |
| 25 | 3 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 4 | 3 | 3 |
| 26 | 2 | 3 | 2 | 4 | 1 | 1 | 1 | 3 | 2 | 1 | 2 | 2 | 1 | 1 | 3 | 2 | 1 | 2 | 2 | 2 |
| 27 | 1 | 2 | 1 | 1 | 3 | 2 | 4 | 3 | 2 | 2 | 2 | 1 | 4 | 2 | 2 | 1 | 3 | 3 | 2 | 1 |
| 28 | 2 | 1 | 2 | 4 | 1 | 1 | 2 | 2 | 1 | 1 | 1 | 2 | 1 | 2 | 3 | 4 | 1 | 1 | 3 | 3 |
| 29 | 1 | 2 | 3 | 3 | 3 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 2 | 2 | 3 | 4 | 4 |
| 30 | 1 | 1 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 2 | 2 | 1 | 3 | 2 | 2 | 1 | 3 | 1 | 1 | 4 | 2 | 2 |

| | | | | | | | | | | | | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| 31 | 1 | 2 | 2 | 3 | 1 | 1 | 4 | 1 | 2 | 2 | 2 | 1 | 2 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 3 | 1 |
| 32 | 3 | 2 | 2 | 4 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 4 | 3 | 2 | 1 | 3 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 3 |
| 33 | 2 | 3 | 4 | 1 | 2 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 2 | 4 | 3 | 3 | 3 | 4 | 1 | 2 |
| 34 | 4 | 4 | 3 | 3 | 1 | 1 | 2 | 3 | 2 | 4 | 1 | 3 | 1 | 3 | 1 | 1 | 1 | 2 | 3 | 3 |
| 35 | 2 | 2 | 3 | 1 | 3 | 3 | 1 | 2 | 3 | 3 | 1 | 3 | 4 | 4 | 2 | 3 | 2 | 4 | 2 | 1 |
| 36 | 2 | 1 | 2 | 3 | 1 | 3 | 1 | 1 | 3 | 3 | 4 | 1 | 1 | 3 | 2 | 1 | 3 | 3 | 3 | 3 |
| 37 | 2 | 2 | 1 | 2 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 1 | 1 | 2 | 4 | 2 | 3 | 2 | 1 | 2 | 4 | 4 |
| 38 | 1 | 1 | 2 | 4 | 3 | 2 | 1 | 2 | 2 | 4 | 3 | 2 | 1 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 1 | 2 |
| 39 | 1 | 4 | 4 | 1 | 1 | 2 | 2 | 1 | 1 | 2 | 2 | 2 | 3 | 2 | 1 | 2 | 1 | 3 | 2 | 3 |
| 40 | 1 | 2 | 1 | 4 | 2 | 3 | 2 | 3 | 3 | 2 | 3 | 2 | 1 | 1 | 2 | 1 | 3 | 1 | 2 | 2 |
| 41 | 2 | 1 | 2 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 | 3 | 4 | 2 | 3 | 4 | 4 | 1 | 3 | 1 | 1 | 1 | 2 |
| 42 | 1 | 4 | 3 | 4 | 3 | 1 | 3 | 4 | 3 | 4 | 1 | 3 | 4 | 3 | 4 | 3 | 1 | 3 | 3 | 1 |

## አባሪ ኸ

## ለሙከራ ቡድኑ በድህረ ቡድናዊ መማር የቀረቡቡድን ተኮር ውይይት ጥያቄዎች

| | |
|---|---|
| 1 | በቡድን መማር ምን ጠቀሜታ አለው፡፡ |
| 2 | በግል ከማንበብና በቡድን ከማንበብ የትኛው ይሻላል |
| 3 | አስቀድሞ የነበረው ቡድናዊ መማርና በጥናቱ ከታቀፋችሁ በኋላ ያለው ቡድናዊ መማር ልዩነት አለው |
| 4 | በተሻለ የሚያነቡ ተማሪዎችን በመመልከት ለማንበብ አበረታታችኋል |
| 5 | በቡድን መማር በማንበብ ደከም ለሚሉ ተማሪዎች እገዛ ያደርጋል |
| 6 | በቡድናዊ መማር በማኅበራዊ ግንኙነታችሁ ላይ ችግር ፈጥሮባችኋል |
| 7 | በቡድን ርስ በርስ በመተጋገዝ አንድን ምንባብ ማንበብ ሊተላለፍ የተፈለገውን መልዕክት ሙሉ በሙሉ ለመገንዘብ ይጠቅማል |
| 8 | በቡድን በመወያየት የምንባቡን ሀሳብ መገንዘብ አንብቦ የመረዳት ጥያቄዎችን በቀላሉ ለመመለስ አግዟችኋል |

## አባሪ ወ



ምስል 3፡ ቁጥጥር ቡድኑ በድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና

አባሪ ዐ



ምስል 4፡ የሙከራ ቡድኑ በድህረ አንብቦ የመረዳት ፈተና

## አባሪ ዘ



**ምስል 5፡ መምህሩ የሙከራ ቡድኑን በቡድናዊ መማር ስልት ሲያስተምር**

## አባሪ ዠ



**ምስል 6፡ መምህሩ የሙከራ ቡድኑን ሲያስተምር የተደረገ ምልከታ**